ጋዜጠኝነትና አክቲቪስት፤ የሚጋጩ ሁለት ሙያዎች!

የጀነራል ደምሴ ቡልቶና የምርጦቹ አዋጊዎች መጨረሻ

ደረጀ ደምሴ ቡልቱ



"ሕወሓትና ሻዕቢያን ከማጥፋት፤ ወደ ዕርቅ መውሰዱ ሰላምን ያመጣል"

አቶ አብርሃም ገ/ሊባኖስ


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 57 ግንቦት 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




## ከሞኝ የግጭት አያያዝ ወጥተን እንዴት በጥበብ እንራመድ?

## ፕ/ር ሕዝቅያስ አሰፋ

በዓለም አቀፍ ደረጃ በግጭት አፈታት አያያዝ ባለሙያ




## አቧራ ወይስ አሻራ?!

እራቱ እና ከተማዋ

ግዮን





ቁጥር 56 ዕትም

ግዮን
ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ
ግንቦት 18
ይጠብቁን!

3 ከሞኝ የግጭት አያያዝ ወጥተን እንዴት በጥበብ እንራመድ?
ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ

በአክቲቪስት መር የኢትዮጵያ ፖለቲካ!
ጋዜጠኝነት ቦታው የት ነው?
መላክ ቢ. 5

ጋዜጠኝነትና አክቲቪስት፤ የሚጋጩ ሁለት ሙያዎች! 8

ዕድሜና አስተሳሰብ
አሸናፊ ዘደቡብ 9

በዜጎች ለዜጎች
ፍቅርተ ተሾመ 10

ከወጡበት ማህበረሰብ ይልቅ ኢትዮጵያዊነትን የሚያስቀድሙት፤
የደርግ ጀነራሎችና የሽንፈቶቻቸው ምክንያቶች!
ነዓምን ዘለቀ 11

ለዛ 13

አቧራ ወይስ አሻራ?! 16

በማስተዋል እንራመድ
ብሩክ አስቻለው 18

ያላስተዋልናቸው ለውጦች!
ወ/ጊዮርጊስ ይሁኔ 21

እራቱ እና ከተማዋ
ፍቅርተ ተሾመ 23

"ሕወሓትና ሻዕቢያን ከማጥፋት፤ ወደ ዕርቅ መውሰዱ ሰላምን ያመጣል"
አቶ አብርሃም ገ/ሊባኖስ 14

ኢዜማ ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገቡ 6 ወሳኝ ነጥቦች
ጃፈር ሰዑም 19

የጀነራል ደምሴ ቡልቶና የምርጦቹ አዋጊዎች መጨረሻ ከ30 አመት በኋላ ሲታሰብ! 25
ደረጀ ደምሴ ቡልቱ

በጠ/ሚ/ር ዐቢይ ዘመን የተጀመረው የወንዝ ዳር ልማት ባለሥልጣን ቢቋቋምለትስ?
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት 28

# ታማኝ በየነ የጌዶኦ ተፈናቃዮችን ጎበኘ፤

## አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ስራውን አወደሱ



ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት (ግሎባል አልያንስ) ለጌዶኦና ጉጂ ዞን ተፈናቃዮች መልሶ ማቋቋሚያ እንዲሆን በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያሰባሰበውን ገንዘብ፣ በስራ ላይ የሚያውልበትን እንዲሁም ተጎጂዎች ወገኖች የሚገኙበትን ቦታ በድርጅቱ ሊቀ መንበር አርቲስት ታማኝ በየነ የሚመራው ቡድን ጉብኝት አድርጎ ተመልሷል።

ግሎባል አልያንስ በታማኝ በየነ በኩል ለእዚሁ ፕሮጀክት የሚውል ከ31 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን ገንዘብ ሰብስቦ ማስረከቡንና ለፕሮጀክቱ ፍፃሜም ከወርልድ ቪዥን ጋር ስምምነት መፈራረሙን ባለፈው ሳምንት መዘገባችን ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግሎባል አልያንስ የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን ለመታደግ ላበረከተው አስተዋፅኦ ምስጋና አቅርቧል። ሚኒስትሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ሊ/መንበር ከአርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ ጋር በተነጋገሩበት ወቅት፤ ድርጅቱ በጌዶኦ ጉጂ ዞን ለተፈናቀሉ ዜጎች ላደረገው ድጋፍና ተፈናቃዮቹን ወደ ቀዬአቸው ለመመለስ ላሳየው ከፍተኛ አጋርነት፤ ምስጋናቸውን የገለፁ ሲሆን አርቲስት ታማኝ በበኩሉ ግሎባል አልያንስ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር ያላቸው ቁርኝት እንዲቀጥል ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አስታውቋል።

# ጠ/ሚር ዐቢይ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤና በሙስሊሞች የኢፍጣር ፕሮግራም ላይ ተገኙ!

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የአብሮነትና የምስጋና የኢፍጣር ፕሮግራም ሲካሄድ፤ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች በፕሮግራሙ ላይ ተገኝተዋል።

በዕለቱ በተከናወነው የጋራ የኢፍጣር ስነ ስርዓት ላይ የተለያዩ ኃይማኖታዊ ስነስርዓቶች፣ መንዙማና ግጥሞች የቀረቡ ሲሆን፤ ፕሮግራሙንም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት እንዳዘጋጀው ታውቋል።

" እስልምና በሰዎች የሚታመን ነው" ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ዑመር እድሪስ አንድነት፣ ሰላም፣ መከባበር ለሰው፣ ለመንግስት ብሎም ለሀገር አስፈላጊ መሆኑን ገልፀው መለያየትና መከፋፈል ለማንም እንደማይጠቅም ተናግረዋል።

ሙስሊሙ ማህበረሰብ በአንድነት ሲያፈጥር መመልከታቸው በእጅጉ እንዳስደሰታቸው የተናገሩት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ "የረመዳን ወር በፆም ሲያሳልፉ በፍቅር፣ በአንድነትና በቅንነት መሆን ይኖርበታል። በረመዳን ከውሸትና ከማሳበቅ በመራቅ ፍሬያማ ጾም ማድረግም ይገባል" ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በተያያዘ ዜና ጠ/ሚር ዐቢይ አህመድ እየተካሄደ ባለው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ አዳራሽ በመገኘት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያላቸውን መልካም ምኞት ገልፀዋል።

ቤተክህነት ጠንካራ፣ ከሙስና የፀዳና ግልፅነት ያለው ተቋም እንዲሆን መልዕክታቸውን ያስተላለፉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሐይማኖት አባቶች በየአካባቢው ከሚገኙ የመስተዳድር አካላት ጋር በመሆን ሕዝብን ስለ ሰላም ፍቅርና ዕርቅ እንዲያስተምሩ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ በረመዳን ጾም የመጨረሻዎቹ ቀናት መስጊዶችንና አካባቢውን በማፅዳት አንድነቱን እንዲያሳይ ጭምር መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# "ዘረኛነት ይብቃ" በሚል መርህ፤ በአ/አ እሁድ የስፖርት እንቅስቃሴ ይካሄዳል

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የመጣውን የዘረኝነት መንፈስ ለማርገብ፤ ከ60 ሺህ በላይ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚሳተፉበት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ እሁድ ግንቦት 18 ቀን 2011 ዓ.ም ከማለዳው 12 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል ተብሏል።

በከተማዋ ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠርና ማስ ስፖርት ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውና፤ በልዩ ንቅናቄ የኦሎምፒክ ሳምንትን አስመልክቶ የሚደረገው የስፖርት እንቅስቃሴ፣ የስፖርት ኮሚሽን፣ የአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፤ እንዲህ ዓይነቱን ብዙኃኑን ሕብረተሰብ ያቀፈ የስፖርት ትዕይንት በዘለቄታዊነት ለማካሄድ ወደፊት ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራበት ገልፀው፤ የእሁዱን ፕሮግራም ለማሳካት ግን በቂ ዝግጅት መደረጉን አረጋግጠዋል።

# ቤስት ዌስተርን ፕላስ አዲስ ሆቴል 1ኛ ዓመቱን አከበረ


በአዲስ አበባ ቦሌ መድሀኔዓለም አካባቢ የሚገኘው ቤስት ዌስተርን ፕላስ አዲስ ሆቴል፤ ተመርቆ ስራ የጀመረበትን አንደኛ ዓመት ክብረ በዓል በልዩ ልዩ ዝግቶች እያከበረ ይገኛል።

የሆቴሉ ስራ መሪዎች ማክሰኞ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም ለጋዜጠኞች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሳወቁት ሆቴሉ በይፋ ስራ ከጀመረ ድፍን የአንድ ዓመት ዕድሜን ያስቆጠረ ሲሆን፣ ይህንኑ በማስመልከትም ሆቴሉ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ነድፎ ለበዓሉ ድምቀት የሚሰጡ ተግባራትን ማከናወን ጀምሯል።

"ባለፉት አንድ ዓመታት ጊዜ ውስጥ እንግዶችን ተቀብሎ ምቾታቸውን የጠበቀ፣ ሁሉን አቀፍ የሆቴል አገልግሎት ከመስጠት በተጓዳኝ ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት በሚያስችሉ የበጎ ምግባር ተግባራትም ውስጥ ስንሳተፍ ነበር" ያሉት የሆቴሉ የማርኬቲንግና ሴልስ ሥራ አስኪያጅ አቶ በሱፍቃድ አባይ "እነዚህ ችግረኞችን በመርዳት ላይ ያተኮሩ በጎ ተግባራት ለሚዲያ ፍጆታ እንዲውሉ ባለመፈለጋችን ያን ያህል ጎልተው አልተሰሙም ነበር" ብለዋል።

የአንደኛ ዓመት የምስረታ ክብረ በዓሉ ለችግረኛ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁን ከመለገስ ጀምሮ በእርዳታ ድርጅቶች ሥር የታቀፉ ዜጎችንም በመርዳት ጭምር የሚቀጥል መሆኑን የተናገረችው የማርኬቲንግና ህዝብ ግንኙነት ኃላፊዋ ወ/ሪት መርዓዊት ፀጋዬ በበኩሏ ሆቴሉ ሲሰጥ ለቆየው መደበኛ የሆቴል አገልግሎት በተጓዳኝ በየሣምንቱ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እቅድ አውጥተው ወደ ተግባር መሰማራታቸውን ገልፃለች።

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ የተገኙ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የሆቴሉን አጠቃላይ ሁኔታ የተረዱበት፣ የጉብኝት መርሃ ግብር የተከናወነ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊ ስያሜ ያላቸው የምግብ፣ የስብሰባና የመዝናኛ አዳራሾች፣ ለነጠላና ጥንድ ማደሪያ ታስበው የተሰሩ ምቹና ማራኪ መኝታ ክፍሎች፣ የስፖርት ጂም እና የስፓ ማዕከሎች በሙሉ በጋዜጠኞች እንዲጎበኙ ተደርገዋል።



ፕ/ር ሕዝቅኤል አሰፋ

# ከሞኝ የግጭት አያያዝ ወጥተን እንዴት በጥበብ እንራመድ?

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ

ሁላችንም እንደምንገነዘበው የሰላምንና የዕርቅን ውይይት ጥቂት አስቸጋሪ የሚያደርገው ሰላምና ዕርቅ የሚሉት ቃሎች ተራ ቃሎች ስለሆኑ፣ በቃሎቹ ስር የተደበቁትን ጽንሰ ሐሳቦች፣ ሁላችንም እናውቃቸዋለን። ከዚያም አልፎ እንስማማባቸዋለን የሚል እሳቤ ስላለ ነው፡፡ ነገር ግን የምንጠቀምባቸው ቃላት ተመሳሳይ ይሁኑ እንጂ፤ የምንሰጣቸው ትርጉሞች ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ። እንዲያውም፣ አንዱ የሰላም ሁኔታ ነው ብሎ የሚቆጥረው ለሌላው የጦርነት ሀኔታ ሆኖ ሊታያው ይችላል። ለምሳሌ ላንዱ ወገን ረባሽ ሰውን ኃይል ተጠቅሞ ዝም ማሰኘት የሰላም ማስከበር ስራ ሲመስለው፣ ዝም እንዲሰኝ ለተገደደው ወገን ከሰላም ይልቅ ጦርነት፣ የአምባ ገነንና የጉልበተኛ ሥራ ሆኖ ሊታየው ይችላል። አሁን ባገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ አንዱ አከራካር ሆኖ የቀረበው ጥያቄ ይህ ነው። ላንዱ ወገን መብቴንና ሰላሜን አስጠብቅበታለሁ የሚልበት መንገድ ለሌለው ደግሞ ሰላም የጎደለው በአመጽ የተሞላ መንገድ ሆኖ ሊታየው ይችላል፤፤ላንዱ አንድነት የሚለው ሐሳብ ሰላማዊ የግጭት መፍትሄ ሲሆን፣ ለሌላው ደግሞ የግጭት መንስኤ ሆኖ ሊታየው ይችላል።

ነገር ግን፣ በተለይ ዘላቂ ሰላምን ስንመለከትና ስንመረምር ዘላቂ ሰላም በሚባለው ሁኔታ ውስጥ የተደበቁ እሴቶች አንዳሉ መረዳትና እነሱንም ትንሽ ገለጥለጥ አድርገን በመነጋገር መጀመሩ ሊጠቅም ይችላል ብዬ እገምታለሁ።

የመጀመሪያው፤ ብጥብጥ፣ ረብሻ፣ ግድያ፣ ማፈናቀል አመጽና ወንጀለኝነት ባሉበት ሁኔታዎች ውስጥ ሰላም ሊሰፍን አይችልም፡፡ ስለዚህ ሰላምን ለመፍጠር አንዳንድ ጊዜ እነዚህን ብጥብጦች ለማቆም ተመጣጣኝና ሕጋዊ ኃይል መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ አሁን በአገራችን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚሰማው “የሕግ የበላይነት ይከበር“ የሚለው ጩኸት ከዚህ ዓይነቱ የሰላም ግንዛቤ የመነጨ ይመስላል።

እርግጥም ነው። በአንድ አገር ውስጥ በእንግሊዝኛ ሞኖፖሊ ኦፍ ቫዮለንስ የምንለው (ማለት በኃይል የማስገደድ የብቸኛ መብት) የመንግስት ነው። ይህንን ጥሰው ግለ ሰቦችና ቡድኖች ኃይልን ተጠቅመው ሌላ ወገን ላይ ፍላጎታቸውን ለመጫን ሲሞክሩ፣ ወይም ጉዳት ሲያደርሱ ይህንን ማቆም የሰላም ሥራ ነው። ይህንን ትርጓሜ ብዙ ሰው ይረዳዋል።

ብዙ ሰው የማይረዳው ግን ይህ የሰላም ሥራ አንዱ ንዑስ አካል እንጂ ሙሉ በሙሉ ሰላም እንዳልሆነ ነው። ይህ ኃይልን ተጠቅሞ አመጽን መስበርና ግጭትንም ማቆም ራሱ ብቻ ዘላቂ ሰላምን አያመጣም። አመጽና ረብሻ ያሉበት ሁኔታ ውስጥ ሕግና ሥርዓትን ማስከበር ለዘላቂ ሰላም መምጣት አስፈላጊ እንጂ ብቁ ሁኔታ አይደለም። በእንግሊዝኛ -- necessary condition እንጂ sufficient condition አይደለም።

እንግዲህ ሰላም ዘላቂ እንዲሆን ከተፈለገ ምን መደረግ አለበት? ብለን ስንጠይቅ፣ ብዙ ሰው የማይገነዘባቸው ጽንሰ ሐሳቦችና እሳቤዎች ብቅ ይላሉ።

አንዱ፤ “ሰላም ማለት ብጥብጥን፣ አመጽንና ረብሻን፣ ግጭትን ከማቆም አልፎ በግጭቱ ስር ላሉት ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማግኘት ነው” የሚለው ነጥብ ነው። ይህንን ሐሳብ ትንሽ በተን አድርገን ስንመለከተው፣ ወደ ሚከተሉት ግንዛቤዎች ይመራናል።

ሀ/ ግጭት ከሰማይ አይወርድም፣ ከመሬትም አይፈላም። ግጭት በሰዎች መካከል የሚፈጠረው በሰዎቹ ግንኙነቶች ውስጥ መልስ/ መፍትሄ የሚፈልጉ ችግሮች ስላሉ ነው፡፡ አለዚያ አንድ ሰው እብድ ወይም የአእምሮ ጤና የጎደለው ካልሆነ በቀር ከመሬት ተነስቶ ከሌላ ጋር አይጣላም። ስለዚህ ሰላም ማለት ይህንን ከስር ያለ ችግር ፈልፍሎ አውጥቶ ለነዚያ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ነው የሚለው ሀሳብ ነው።

ይህ ድምዳሜ ወደ ሁለት ትምህርታዊ ወደ ሆኑ ግንዛቤዎች ይወስደናል።

አንደኛው/ ግጭት ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነቶች ወይም ዝምድና፣ መሻሻል አለበት ወይም መፍትሄ ማግኘት የሚገባው ችግር እንዳለ ጠቋሚ እድል ነው፤ ማለት ነው። ለውጥ፣ እድገት፣ መበልጸግ የሚመጣው እንደዚህ ዓይነቱ መሻሻል ወይም መፍትሄ ሲፈጠር ነው፡፡ ስለዚህ ግጭት በአዋቂዎችና በጠቢባን ከተያዘ የመጠላለያ፣ የመገዳደያ፣ የመወዳደሚያ መንገድ ከመሆን ይልቅ የማደጊያ፣ የመሻሻያ እድል ፈጣሪ ሲሆን የሰላም ስራ ደግሞ ይህንን ተገንዝቦ መፍትሄ የማግኛዎቹን መንገዶች መጥረግና ማመቻቸት ነው ማለት ነው።

በሌላ አነጋገር፣ ግጭት መፍትሄ የሚፈልግ ችግር እንጂ ሰዎች እርስ በራሳቸው የሚያሸናነፉበት ትግል አይደለም። ሰላምም ማለት ከዚህ ግጭት ስር ላለው ችግር ዘላቂ መፍትሄ መፈለግያ መንገድ ነው። ከዚያም አልፎ፣ ብዙ ሰው የማይረዳው፣ ግጭትን ጎጂ የሚደርገው ግጭቱ ራሱ ሳይሆን አያያዙ ነው። ይሄ ማለት፣ ግጭት ወደድንም ጠላንም በሰዎች መካከል ሁል ጊዜ አለ፣ ይኖራል፡፡ ግን ግጭት በሞኞች ሲያዝ በገለባ ላይ ክብሪት የመጫር ያህል ነው። ይቀጣጠላል፣ ይፋፋማል፣ ተፋላሚዎቹ የመጎዳዳት ፉክክር ውስጥ ይገቡና ለእነሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚተርፍ ጉዳትና ስቃይ ያተርፋሉ። ነገር ግን ግጭትን ብልህ ሰው ሲይዘው ወደ መጎዳዳት ፉክክር፣ ወደ መገናተር፣ እልህ፣ ከመሄድ ፋንታ በግንኙነቶቸ ውሰጥ ወደ ጠብ የመሩትን ሁኔታዎች ወደ መመርምር፣ ወደ መማማርና ወደ ጋራ መፍትሄ ፍለጋ ስለሚወስድ ግጭት የመሻሻያ፣ የመለወጫ፣ የማደጊያ ፣ የመጎልመሻ እድል ፈጣሪ ሆኖ ሊገኝ ይችላል ማለት ነው። በጥበብ ከተያዘ።

እንግዲህ በአገራችን ውስጥ ስለ ሰላምና ግጭት ልንማረው የሚገባው ትልቅ ትምህርት አንዱ ይህ ነው። ግጭት አይቀሬ ከሆነ፣ እንደ ሕብረተሰብና፣ እንደ ግለሰብ ግጭትን እንዴት ነው የምንይዘው? በአገራችን ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ የታዘብነው የግጭት አያያዛችን ይበልጥ የሚያገናትርና ደም የሚያፋስስ እንጂ ወደ መፍትሄ የሚመራ ሆኖ አላገኘነውም። ለወደፊት በሕብረተ ሰብ፣ በቡድን እንዲያውም በግለሰበብ ደረጃ የሚያጋጥሙን ስቃዮች ለመቀነስ የምንሻ ከሆነ፣ ታሪካችንንም ለመማሻሻል የምንፈልግ ከሆነ የግጭት አያያዛችንን ስልት መቀየር ይኖርብናል።የዚህ ፕሬዜንቴሽን አንዱ ዓላማ፣ እንደ አገርና ሕዝብ፣ ከሞኝ የግጭት አያያዝ ዝንባሌ ወጥተን ወደጠቢብ አያያዝ እንድንሸጋገር ለመማጸን ነው።

እንግዲህ ዘላቂ ሰላም ከግጭቶች ስር ላሉ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማግኘት ነው ካልን፣ እንደዚህ ዓይነቱ ሰላም እንዲመሠረት ከዚህ ግንዛቤ ባሻገር ሌሎችስ ምን መደረግ አለባቸው?

ይህ እንዲሆን ከተፈለገ የሰላም መፈለጊያው ሂደት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል። በጊዜ እጥረት ምክንያት ሁሉንም ሳይሆን ዋና ዋና ከምላቸው ሶስቱን ብቻ እጠቅሳለሁ።

መጀመሪያ ሂደቱ ያገባናል የሚሉትን ሁሉ ወገኖች ማሳተፍ አለበት። ይህ እንግዲህ ዲሞክራሲ የምንለው ጽንሰ ሐሳብ እንደሆነና ከሰላም ጋር ስላለው ግንኙነት በቀጣይ እንደምንወያይበት ተስፋ አለኝ።

ሁለተኛ፣ የሚፈለገው መፍትሄ ከላይ ከላይ ለሚታዩት የችግሩ ምክንያቶች ብቻ ሳይሆን የግጭቱ ስረ ምክንያቶቹን ፈልፍሎ አወጥቶ ለነሱም መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል። አንዳንድ ጊዜ ከላይ ከላይ ለሚታዩት ምክንያቶች ብቻ መልስ መስጠት፣ ከሥር ያሉትን ችግሮች ይበልጥ እንዲባባሱ ላያደርጋቸው ይችላል።

ሶስተኛ፣ የሚፈጠረው መፍትሄ በግጭቱ▶

ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑት ወገኖች ሁሉ መፍትሄ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ መፍትሄው ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ አይሆንም፡፡ ያ ችግሩ ያልተፈታለት ወገን አሁን ፈርቶ ወይም ተሸንፎ ዝም ቢልም፣ ያ ወደ ግጭት የወሰደው ችግር እስካለ ድረስ፣ ተፈጠረ የተባለውን ሰላም መልሶ መበጥበጡ አይቀርም፡፡ ሰላሙ ፈርሶ አንደገና ወደ አመጽና ጦርነት ይኬዳል፡፡ ስለዚህ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ ሊሆን አይገባውም፡፡ ሁሉም አሸንፈናል ብለው ማመን አለባቸው፡፡

ይህም ሊሆን የሚችለው ሂደቱ ሁለት በጣም ቁልፍ የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች ላይ የተመሰረተ ሲሆን ነው፡፡

### ሀ/ መግባባት፤

መግባባት ስንል ምን ማለታችን ነው? መግባባት ብዙ ሚስጥሮችን ያዘለ ቃል ነው፡፡ መግባባት የሚለው ቃል መግባት ከሚለው ስረ ቃል የመነጨ ነው፡፡ ቃል በቃል ስንተረጉመው አንዱ ሌላ ውስጥ ሲገባና ሌላውም በመጀመሪያው ውስጥ ሲገባ ማለት ነው፡፡ በሰላም አንጻር ስንመለከተው መግባባት ማለት አንድ ሰው በሌላ ሰው ልብ (መንፈስ) ውስጥ ሲገባና መልካም ቦታ ሲያገኝ፣ ሌላውም በመጀመሪያው ሰው ልብ ወይም መንፈስ ተመሳሳይ ቦታ ሲያገኝ እውነተኛ መግባባት ተገኘ ሊባል ይቻላል፡፡ በልብ ወይም በመንፈስ ውስጥ መልካም ቦታ ማግኘት፣ ማለትም ሌላውን መቀበል፣ ሳይወነጅሉና ሳይኮንኑ የሌላውን ችግር በተቸገረው ሰው ዓይን መመልከት፣ የሚሰማውንም ስሜት እንዲሰማን ልብንና አዕምሮን መክፈት  ማለት ነው፡፡

የመግባባት መሣሪያ ጥልቅ መደማመጥ ነው፡፡ ይህም ማለት በጆሮ ሳይሆን፣ በልብና በመንፈስ መደማመጥ ማለት ነው፡፡  የሚያስደንቀው፣ እንደዚህ ዓይነቱ መደማመጥ እራሱ ብቻ ብዙ ግጭት ካስከተለው የመቆራረጥ ስሜትና ውስጣዊ ስቃይ ትልቅ ፈውስ ያመጣል፡፡ ይህንን በሥራዬና በሕይወት ተሞክሮዬ አይቼዋለሁ፡፡ ለዚህ ምስክር ነኝ፡፡ አሁን በአገራችን ደረጃ እንደዚህ ያለ መደማመጥና መግባባት ያስፈልገናል፡፡ ብሔራዊ መግባባት የሚባለው ይህ ነው፡፡

### ለ/ የሕይወት ትስስር

ሁለተኛው የሰላም ሂደት መሰረት የሕይወት ትስስር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ነው፣ ይህም ማለት ማንም ሰው የራሱን ደኅንነትና ጥቅም ዘላቂ በሆነ መንገድ ሊጠብቅና ሊያጎለምስ የሚችለው የሌሎችን ደኅንነትና ጥቅም ሲጠብቅ ብቻ መሆኑን መረዳት ነው፡፡ ይህም ማለት እኔ ጥቅም የሚመጣው ወይም የሚጠበቀው፣ በሌሎች መጎዳትና መጎሳቆል ከሆነ ውሎ አድሮ የተጎዱት፣ የተዋረዱትና የተጎሳቆሉት የእኔን ጥቅም ለመጉዳትና ለማጥፋት መንገድ እንደሚፈልጉ ጥርጥር የለውም፡፡ በሌላ አነጋገር የሰው ሕይወትና ደኅንነት የተሳሰረ ነው፡፡ ስለዚህ ሁላችንም የምንፈልገው የግል ደኅንነት የሚጎለምሰው ለሌሎች ደኅንነትና ጥቅም መጎልመሻ መንገድ ሲከፍት መሆኑን ይህ መሠረተ ሐሳብ ያመለክተናል፡፡

የዚህም ጽንሰ ሐሳብ አንዱ መገለጫ ሰጥቶ መቀበል የሚለው መርህ ነው፡፡ ህም ማለት፣ ሰጥተን ስንቀበል ነው ማግኘታችን ዘላቂ የሚሆነው፡፡ መከበርን የምናገኘው ለሌላው ክብር ስንሰጥ ነው፡፡ ፍቅርን የምናገኘው ፍቅርን ስንሰጥ ነው፡፡ ጸጥታን የምናገኘው ሌሎችን ስንረብሽ ሳይሆን ጸጥታን ስንሰጥ ነው፡፡ በተመሳሳይም ኃይላችንንና ብልጽግናችንንም ዘላቂ በሆነ መንገድ የምንገነባው ለሌሎች የኃይል ማግኘትና መበልጸግ መሣሪያ ስንሆን ነው፡፡  ይህ ነው የሰጥቶ መቀበል እንቆቅልሽ፡፡

ልብ ብለን የተመለከትነው ከሆነ ሰጥቶ መቀበል በሰዎች መካከል የማንኛውም ትርጉም ያለውና የበሰለ የግንኙነትና የዝምድን መገለጫ ከመሆኑም በላይ እንዲያውም የተፈጥሮ ሕግ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንግዲህ በዚህ ግንዛቤ መሠረት ዘላቂ ሰላም ማለት፡ በሰዎች መካከል በሕይወት መተሳሰርና በሰጥቶ መቀበል መሠረተ ሐሳብ ላይ የተገነቡ ግንኙነቶችን መፍጠርና ማጎልመስ ነው፡፡ በአገር ደረጃ ስንመለከተው ዘላቂ ሰላም ማለት በሕይወት መተሳሰርና ሰጥቶ መቀበል ለይ የተመሰረቱ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ኑሮ ሥርዓቶችን መፍጠር ማለት ነው፡፡የሰላም ግንባታ ማለትም በሰዎች መካከል እንደዚህ እርስ በርስ የሚያከባብር፣ የሚያጠቃቅም፣ አንዱ ለሌላው የእድገት ምንጭ የሚሆንበትን አስተሳሰቦች፣ ዝንባሌዎችና ርዕዮተ ዓለሞችን ማስተማርና መኮትኮት፣ ተፈጻሚም እንዲሆኑ የሚረዱ ያሠራር ዘዴዎችን፣ ሂደቶችን፣ ስርአቶችንና መዋቅሮችን መፍጠርና ማጎልመስ ነው፡፡ የሰላም ምንነት የሚለውን ርዕስ ልተውና ወደ ሁለተኛው ርዕሴ ልዙር፡፡

### የባለድርሻዎች ሚና

ሰላም ብዙ ባለድርሻዎች አሉዋት፤፤ አሁን ባለችን አጭር ጊዜ ሁሉን መጥቀስ ስለማይቻል የሶስቱን ብቻ እጠቁማለሁ፡፡ የመንግስትን፣ የምሁራንና፣ የሐይማኖት መሪዎችን ብቻ፡፡

### 1. መንግስት

የመንግስት ሚና የታወቀ ነው፡፡ እንዲያውም ለብዙ ሰዎች ሰላም የመንግስት ብቻ ስራ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ አስተያየት ሙሉ በሙሉ ትክክልም ባይሆን እርግጥ መንግስት ታላቅና ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሕግና ስርዓትን ማስከበር ፣ ከዚያም የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማሕበረሰባዊ መዋቅሮቹን ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን የሰላም እሴቶች እንዲያጸባርቁ አድርጎ ማዋቀርና መምራትዋናው ነው፡፡

### 2. የምሁራንና የልሂቃን ሚና፡

እዚህ አዳራሽ ከተሰበሰብነው ሰዎች ብዙዎቻችን ምሁራን ነን የሚል ጭምጭምታ ስለሰማሁኝ የምሁሮች ሚና ላይ ጥቂት ለማተኮር እፈልጋለሁ፡፡

እስካሁን ካቀረብኩት እንደተመለከታችሁት ባንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ለሰላም ያለው ግንዛቤና ዝንባሌ በሕዝቡ ዘንድ ከሚታየው ንቃተ ሕሊና ጋር ይዛመዳል፡፡ እንደ ግለሰብና ማሕበረሰብ በስነ ልቦና እያደግንና እየጎለመስን ስንሄድ ከላይ የጠቀስናቸው የሰላም እሴቶች ከሕይወታችን ጋር ይዋሃዳሉ፡፡ እርስ በርስ የመከባበር፣ የመደማመጥ፣ የመተሳሰብ፣ “ለኔ ብቻ” ያለማለት፣ የመተባበር፣ የቀናነት ዝንባሌን እናሳድጋለን፡፡ እነዚህ ከንቃተ ሕሊና ማደግ ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡

የንቃተ ሕሊና ማደግ አንዱ መሰረቱ፤ ሕይወት የተሳሰረች መሆንዋን መረዳትና በዚህ ርእዮተ ዓለም ላይ የተገነቡ ዝምድናዎችን መፍጠር ነው፡፡ አንተ/አንቺ ለኔ ታስፈልጉኛላችሁ፣ እኔም ለናንተ አስፈልጋችሁዋለሁ -- ይህ ነው ትልቁን ስእል ማየትና ማሳየት ማለት፡፡ እነዚህን ርዕዮተ አለሞች ማስተማርና በምሳሌነት ማሳየት፣ ጉዞውንና መንገዱን መንደፍ የልሂቃንና የምሁራንና ሚና ነው፡፡     በጽሁፋቸው፣ በንግግራቸው፣ በድርጊታቸው፣ በምሳሌነታቸው ምሁራን የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና እንዲያድግ ወይም እንዲሳከርና እንዲቀጭጭ ለማድረግ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

በተለይ የኢትዮጵያ ምሁሮችና ልሂቃን ባለፉት አስርተ አመታት ከሰላም ይልቅ የግጭት ብጥብጥና የመተላለቅ ምንጭ ነበርን የሚል ክስ ስላለ ይህ ዝንባሌ ተለውጦ በሰላም፣ በመተባበር፣ በመደማመጥና መከባበር ዝንባሌ እንዲቀየር፣ ማለትም በአገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን አስተዋጽኦ የማድረግ ግዴታ አለብን፡፡

### 3. የሐይማኖት መሪዎች

አገራችን ውስጥ ያሉ የብዙ ግጭቶች መነሻዎች የመንፈሳዊነት ጉድለት ምልክቶች  ናቸው፡፡ ስርቆሽ፣ ጉቦኝነት፣ ወሰን የሌለው ስግብግበነት፣ ዘረኝነትና በፈጣሪ አምሳል የተፈጠረውን ሰው ዝቅ ማድረግ፣ መጠየፍ፣ ክብሩን ማዋረድ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የፈጣሪን ሕግ የሚጥሱ ተግባሮችና ባሕሪዮች ናቸው፤፤ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚሁ ድርጊቶች ናቸው በሕዝብና ሕዝብ ግጭትን፣ አለመተማመንን፣ ጥላቻን፣ የሰላም መደፍረስን የሚፈጥሩ፡፡

እንግዲህ የሐይማኖት ቤቶችና መሪዎች፤ ተከታዮቻቸውን እንደዚህ ከመሰሉት የፈጣሪ ሕግ ጥሰቶች እንዲጸዱ ቢያስተምሩ፣ ቢያሳምኑ፣ በተከታዮቻቸው ሕይወት ውስጥ እንዲሰርጹ ቢያደርጉ፤ በህብረተሰብ ደረጃ ብዙ ሰላም ልናገኝ እንችላለን፡፡ ሌላ ቢቀር ብዙ ግጭቶች ሊቀረፉ ይችላሉ፡፡  በተመሳሳይ ስለ ቤተሰብ፤ መምሕራንና ትምህርት ቤቶች፣ ጋዜጠኞች፣ ነጋዴዎች፣ የሲቪል ሕብረተሰብ ተቋሞች፣ የፖለቲካ መሪዎችና ድርጅቶች ሚና ብዙ ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁሉ ውስጥ ለመግባት ግን ዛሬ ጊዜ የለንም፡፡

### ለማጠቃለል ያህል

1. ሰላም ያንድ ሰው፣ ያንድ ድርጅት
ወይም አካል ሐላፊነት አይደለም፤፤ የሁላችን 1
ግዴታ ነው፡፡ ስለዚህ ለሰላም መጥፋት ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን፡፡ ለሰላም መስፈንም ሁላችን አስተዋጽኦ አለን፡፡

2. ሰላም ምንም ሚስጥር የለውም፡፡ ሰላም ማለት

ሀ. አብሮ መስራት፣ መተባበር፣ መደጋገፍ፣ አብሮ የጋራ ችግርን መፍታት፣ ነው

ለ. ሰላም ማለት አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ መባባል ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ካለ ለሁላችን የሚበቃ መከበር፣ ሐብት፣ ኃይልና ሥልጣን አለ፡፡

ሐ. ሰላም ማለት ከሚለያዩን ነገሮች ላይ ብቻ ከማተኮር የሚያገናኙንም ላይ ማተኮር ማለት ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህን ጥቂት ሐሳቦች እንኩዋን ይዘን ብንንቀሳቀስ በአገራችን ውስጥ የሰላምን ፋና ማየት እንደምንችል ጥርጣሬ የለውም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህን ጽሁፍ ፕ/ር ሕዝቅያስ አሰፋ በኤሲኤ አዳራሽ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድን ጨምሮ ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለስልጣናትና ምሁራን በተገኙበት አቅርበውት ነበር፡፡ ጽሁፉ ለተቀረው የህብረተሰብ ክፍል ቢደርስ የሚኖረውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥናታዊ ጽሁፋቸውን ለግዮን መጽሄት ዝግጅት ክፍል በአሁኑ ወቅት ከሚኖሩበት አሜሪካን ልከውልናል፡፡ እናመሰግናለን፡፡

የጥናት ጽሁፉ ውስጥ የተነሱትን ሐሳቦች በጥልቅ ለመረዳት፣ በዚሁ ጽሁፍ አቅራቢ የተዘጋጀውን ***“ሰላምና ዕርቅ፣ ትርጉምና መንገዶች”*** የሚባለውን መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡

# በአክቲቪስት መር የኢትዮጵያ ፖለቲካ

## ጋዜጠኝነት ቦታው የት ነው?

መላክ ቢ.

ብዙዎች አክቲቪስት የሚለው ቃል ወደኢትዮጵያ ፖለቲካ የመጣው ከ ውጡ ጋር ተያይዞ ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ። ነገር ግን ኢህአዴግ ሃገሩን ረግጦ በገዛበት እና ሁሉም ነገር ጸጥ እረጭ ባለበት የአለቅነት ዘመኑም ጭምር አክቲቪዝም አቆጥቁጦ ነበር።

የቀድሞው የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ሽመልስ ከማል በአንድ ወቅት ፕሬስንና የመረጃ ነጻነትን በተመለከተ በግዮን ሆቴል በተካሄደ ውይይት ላይ "እኛ አሁን የተቸገርነው በጋዜጠኝነት ስም አክቲቪዝም እየተተካ በመምጣቱ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ጋዜጠኞችን አላሰረም። በጋዜጣ ላይ በጻፈው፣ በራዲዮ ባወራው ምክንያት የታሰረም ይሁን የተጠየቀ ማንም ሰው የለም። በማረፊያ ቤቶች ያሉትም ይሁኑ የተፈረደባቸው ሰዎች ሁሉ በጋዜጠኝነት ስም አክቲቪስት ሆነው ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሞከሩ እና በተለያዩ የኦንላይን ሚዲያ ውጤቶች ላይ ይህንኑ ተግባር ሲያከናውኑ የነበሩት እንጂ ጋዜጠኞች አይደሉም" ብለው ነበር።

ያ መንግስት ጋዜጠኞችን ለመምታት ስማቸውን ወደአክቲቪስትነት ሲያሽጋግረውና "በጻፉት አልከሰስኳቸውም" ብሎ መረጃ የመጻፍ እና የማሰራጨት መብታቸውን ከፍርግርግ ብረቶች ኋላ አስቀምጧቸው ሲያግደው በሌላ በኩል ጋዜጠኞቹ በሚዲያቸው አንዳች መንግስትን የሚተች ነገር እንዳይጽፉ እና እንዳያወሩ አፋቸውን ሸብቦ ሲያስፈራራቸው የዚህች ሃገር የመረጃ ስርጭት ስራ አፈር በልቶ ኖሯል። ኢህአዴግ በዘመኑ በሚያውቀው ፣ ዘወትር በሚሰልለው እና መዝግቦ ፍቃድ ነጠቅኩ፣ ሰጠሁ እያለ በሚያስፈራራበት ሜይንስትሪም ሚዲያ ላይ አንዳች እንዳይነተፈስ እና እንዳይወራ አደርጎ ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነው የኢንተርኔት ሚዲያ ላይ ደግሞ ወፍ እንኳን እንዳታመልጠው ሲሰራ ነው የኖረው። በዚህም ከፍተኛ በጀት እያወጣ ኦንላይን ሚዲያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይከፈቱ እስከመዝጋት፣ የራዲዮ እና ቴሌቪዥን ስርጭቶች እንዳይሰሙ እስከማገድ እና መረጃ በሚፈለገው መጠን እንዳይዛመት እንቅፋት እስከመፍጠር የደረሰ ስራ ሰርቷል። በነዚህ ዲጂታል በሚባሉት ሚዲያዎች ላይ በሚሰሩ ሰዎች ላይ ክስ ሲመሰርት እና ሲያስራቸው ራሱ ስማቸውን አክቲቪስት ብሎ እየጠራ ነው።

ዋናው ሚዲያ በዚህ መልክ ተጠልፎ ከመዝናኛ ጉዳዮች የላቀ ስራ መስራት ባልቻለበት ወቅት የህዝብ መረጃ የማግኘት መብት ሙሉ በሙሉ ተደፍጥጦ ነበርና ብዙሃኑ በሚያገኙት ቀዳዳ ሁሉ መረጃ ማነፍነፍ እና በሃገራቸው እየሆነ ስላለው ጉዳይ ለማወቅ እንደፌስቡክ ባሉ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ጀመሩ። ይህ የተደራሲ መረጃ መፈለጊያ ስፍራ ለውጥ ብዙሃኑን የመብት ተሟጋቾች እና አክቲቪስቶች ወደማህበራዊ ሚዲያው ስቦ አውዱ ማንኛውም ሃገር አቀፍ የፖለቲካ ጉዳዮች የሚንሸራሸሩበት አውድ እንዲሆን ምክንያት ሆኑ። በዚህ ሳቢያም እንደ ድምጻችን ይሰማ ፣ ኦሮሞ ፕሮቴስት እና የመሳሰሉ ግዙፍ የፌስቡክ ንቅናቄዎች ተፈጠሩ። መረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እና ገደብ በሌለው ስርጭት መዳረስ ሲጀምር ኢህአዴግን በማያውቀው ሜዳ የገጠመውን ጦርነት እና ባልገመተው መንገድ የመጣበትን የመረጃ ጠላት ለመከላከል በብዙ ጥረት አደረገ። እንዲያም ሆኖ መረጃ ከመታፈኑ በፊት ሚሊዮኖች እጅ እየገባ በኢህአዴግ ላይ ለሚካሄደው ተቃውሞ እና ትግል መስመር መክፈት ጀመረ።

ኢህአዴግ በቁም ያለ መስሎ በውስጥ ግን መፈረካከስ መጀመሩ ፣ በውስጠ ትግል መዳከሙ እና በውጭ ያለውን ጫና መቋቋም ያቃተው መሆኑ የልብ ልብ የሰጣቸው አክቲቪስቶች ይህንን ፓርቲ አብዝተው መታገል አላቋረጡም። መንግስት በራሱ ብዛት ያላቸው የማህበራዊ ሚዲያ አክቲቪስቶቹን በደሞዝ ቀጥሮ ይህንን ጦርነት ቢቀላቀልም ፣ በተለይ ህወሃት ዛሬ ድረስ በዲጂታል ወያኔ ስም አቅፏቸውና ደግፏቸው የሚጓዘውን አባላቱን ቢያሰማራም የብዙሃኑ ሃይል አጋደለና ኢህአዴግ የሚንገዳገድበት ብቻ ሳይሆን የሚወድቅበት ምሳር ይፈልጠው ጀመር።

እየቆየም የህዝብ አመጽ በከፍተኛ የመረጃ ፍጥነት እየተገናኘ ሲተባበር እና በተለይም ኦሮሞ እና አማራ ክልል የተካሄዱ ተጋድሎዎች በሃሳብ ጥምረት ተጠናክረው ለጋራ አላማ እየተባበሩ ሲመጡ በአንጻሩ ኢህአዴግ እንደፓርቲ አንድ የመሆን እድሉን እያጣ፣ በመካከል ልዩነት እየሰፋ እና የጋራ ድምጽ እየቀነሰ መጣ። በመጨረሻም ፓርቲው በራሱ ተፈረካክሶ ከውስጥ አዲሱ የለውጥ ሃይል ብቅ አለ።

### አክቲቪዝም ከለውጡ በኋላ

በአማራም ይሁን በኦሮሞ ብሄር ልሂቃን ዘንድ አክቲቪዝም ለዚህ ለውጥ መገኘት የነበረው ድርሻ ምስክር ነጋሪ አላጣም። ምክንያቱም ሁለቱን ትልቅ ህዝቦች በአንድ መስመር አዋህዶ ትግሉ እንዲጠና እና ኢህአዴግም አማራጭ አጥቶ ሃገር እና ፖለቲካ በሚመራበት ኢንተርኔት መረብ ውስጥ ገብቶ እንዲንተፋተፍ በማድረግ ሃይሉን እንኳን የሚጠቀምበትን አቅም ያሳጡት በየጊዜው ውስጠ ምስጢሩን ደጅ እያወጡ ያሰጡለት የነበሩ አክቲቪስቶች ናቸው።

ኢህአዴግ ተለውጦ ሲመጣ እንደነጀዋር ላሉ አክቲቪስቶች ነው ቀድሞ እውቅና የሰጠው። (የዛሬን አያድርገውና) ጀዋር የኦሮሞ ተቃውሞን በመምራት እና በተለይ ቄሮ የተባለውን ቡድን ከኦህዴድ የለውጥ አካላት ጋር አደራጅቶ በመምራት በጊዜው ለነበረው አፋኝ ስርዓት የጎን ውጋት በመሆን የለውጥ ሂደቱን ማፋጠኑ አይካድም።

ለውጡ መጥቶ ህዝቡም ተቀብሎት መንግስትም በህዝብ እና በኢህአዴግ መካከል መቃቃር የፈጠሩ ጉዳዮች ላይ መፍትሄ አበጅቶ እና የታሰሩ የህሊና እስረኞችን ፈትቶ ወደመስመር ከገባ በኋላ አክቲቪዝም መልኩን ቀይሮ ሶሻል ሚዲያን የጦር ሜዳ አደርጎ ራሱንም በተዋጊ መስመር አሰልፎ መጣ። በለውጡ ደጋፊ እና በለውጡ ተቃዋሚ አክቲቪስቶች መካከል የሚካሄድ የፌስቡክ እና የዩቲዩብ ጦርነት ዐውድ ተከፈተ። ከሁለቱ ለአንዱ ወገን ይጠቅማል የተባለ መረጃ ሁሉ ሳይጣራ በወረደበት መልኩ ለህዝብ እየተሰጣ የመረጃ መወናበድ ችግር ተፈጠረ። በተለይም ህወሃት ላይ አነጣጥሮ የነበረው ትኩረት ቀስ በቀስ ወደተከፋፈሉ አዲስ ብሄርተኛ አስተሳሰቦች ሲሰራጭ በኣላማ የማይስማሙ አክቲቪስቶች አንዱ አንዱን ለመጣል እና ተቀባይነቱን ለማሳጣት የሚሰናዘሩት ቃል በራሱ የመረጃ መድረኩን ረብሾ የሃሰት ዜናዎች እንዲፈሉ ምክንያት ሆኗል። አክቲቪዝም በኢትዮጵያ መሰረታዊ የፖለቲካ አውድ ላይ ጉልሁን ስፍራ መጨበጥ በመቻሉም ፖለቲካው በዚያ ሂደት የሚቃኝ እየሆነ መጣ። ለዚህም ነው ከለውጡ በኋላ አክቲቪስትነት ከነበረው ለውጥ እንዲመጣ የማፍጠን አላማ በተቃራኒ የሸኩቻ አውድ ሆኖ ብቅ ብሏል የሚባለው።

▶

በዚህ ሂደት ውስጥ ነው ህዝብ ሊያምነው እና ሊቀበለው፣ የተጣራ መረጃ ነው ብሎ ህይወቱን ሊመራበት እና ለውሳኔ ሊጠቀምበት የሚገባው ዋና ሚዲያ (ሜይንስትሪም ሚዲያ) በሶሻል ሚዲያ እየተመራ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው:: ይህንን ለማስተካከልም መንግስት ምንም አይነት እርምጃ ለመውሰድ ዳተኝነት ከማሳየቱ ባሻገር በአንድ በኩል አክቲቪስት አጀጋኝ፣ በሌላ በኩል ሚዲያ ወቃሽ አመራር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል::

## አክቲቪስት ማነው? ጋዜጠኛስ?

በምክንያታዊና አሳታፊ የሚዲያ ባህል ውስጥ ጋዜጠኝነትና አክቲቪዝም ሁለት የተለያዩ መስመሮች ናቸው:: ጋዜጠኝነት መርህ ያለው፣ በሙያው ለወጡ ስታንዳርዶች የሚገዛ፣ ህዝብ እምነት ጥሎበት የሚቀበለው እና በሃላፊነት ስሜት የሚሰራ፣ በስህተቱም ተጠያቂ የሚሆን ሙያ ሲሆን አክቲቪዝም የጋዜጠኝነትን ያህል የጠነከሩ ህጎች የሌሉበት፣ በአንጻሩ የራስ ሃሳብ የተጨመረበት ድቅል መረጃ በማቅረብ ለአንድ አላማ የሚሚገት ፣ የሚሚገት አላማ ሲሳካም ስራውን እዚያ ላይ የሚያጠናቅቅ ቋሚ ያልሆነ ተግባር ነው:: በአማርኛው ቃል አራማጅነት ብለን የምንጠራው አክቲቪዝም የተረጋጋ ፖለቲካ ባለበት ሃገር ማህበራዊ፣ ጤና ተኮር፣ ሰብዓዊ መብት እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አትኩሮ የሚሰራ ጨቅጫቂ ቡድን ሲሆን እንደኢትዮጵያ ባሉ ሃገራት ደግሞ ሙሉ ትኩረቱን ፖለቲካ ላይ አድርጎ ጠዋት ማታ በፍላጎት ውስጥ የሚበቅለውን የራስ የበላይነት ለማንገስ የሚሯሯጥ አካሄድ ነው::

የ'ዴሞክራሲያዊ ሚዲያ' አላባውያን የሆኑት ነጻ ሚዲያ እና ሃሳብን የመግለጫ መዋቅሮች ባልተሟሉባቸው አገራት ዘንድ እነዚህ ዘርፎች አንዱ ሌላዉን ተክቶ የሚሰራበት ሁኔታ በእጅጉ የበዛ ነው:: ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነት ሲታፈን እና ህዝብ የመረጃ ምንጭ ሲያጣ አክቲቪዝም ያንን ክፍተት ተክቶ መስራት የጀመረው::

ከዚህ ቀደም በወሊሶ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበረው እና አሁን ሙሉ ጊዜውን አንዳፍታ ዶት ኮም በሚባል ኦንላይን ሚዲያ ላይ በውይይት አዘጋጅነት እና አክቲቪስትነት የሚያሳልፈው ስዩም ተሾመ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሲናገር "የኛ አክቲቪስትነት በኢትዮጵያ ሚዲያ እና ጋዜጠኝነት ላይ በመታፈን፣ በመሳደድ፣ በመታሰር እና በመዘጋት ክፍተት ሲፈጠር ያንን ለመድፈን የተፈጠረ እና በዚያው መጠንም ያደገ ሂደት ነው" ይለዋል::

ይህንን ተከትሎ የተፈጠረው እና መሰረታዊ ተግባሩን በሶሻል ሚዲያ መረጃ ማቀበል እና መሚገት አድርጎ የዘለቀው አክቲቪዝም ግን የጋዜጠኝነት ተግባር የሆነውን "ሰበር ዜና" ከማቅረብ ጀምሮ ያልተጣራ መረጃ መድረኩ ላይ በማስጣት አስቀድሞ ለሚፈጠር የተከታይ መረጃ ተዓማኒነት ማነስ በር የከፈተ ድርጊት ሆኗል:: ጋዜጠኝነት የሚጠይቀውን መረጃ ማጣራት፣ አርትዖት መስራት እና ከስነምግባር አኳያ የመገምገም ሂደት አክቲቪዝም ስለማይጠይቅ የቀደመው መረጃ ተዓማኒ ሆኖ ጋዜጠኝነት የሚሰራው መረጃ ግን በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጎታል::

የአዲስ ስታንዳርድ መጽሄት ዋና አዘጋጅና መስራች ጋዜጠኛ ፀዳለ ለማ ይህን በተመለከተ ስትናገር "አክቲቪስቶች ለመቅደም ሲሉ ያበላሹትን እና ያቀረቡትን የተሳሳተ መረጃ ጋዜጠኞች ለሚዲያ በሚሆን መልኩ ለመስራት ሲነሱ አስቀድሞ መረጃው በተደራሲው ዘንድ ስዕል ይዞ በመቆየቱ እውነትን ማቅረብ አዳጋች እየሆነባቸው ችግር ውስጥ ወድቀዋል ትላለች:: ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ መረጃን ቀድሞ ለማቅረብ በሚደረግ ጥድፊያ እና የተጣራ መረጃን ለማቅረብ በሚደረግ ሂደት መካከል ያለው ጊዜ ላይ ብልሽት ስለሚፈጠር ነው ባይ ናት ጸዳለ::

አሁን አሁን በተጨባጭ እንደምናየው ጋዜጠኝነትንና "አክቲቪዝም"ን በደምሳሳው በአንድ ጆንያ ከቶ አንድና ያው እንደሆኑ የመመልከቱ ቅኝት በሁለቱ ሞያዎች መካከል ያለዉን ሰፊ መስመር መገንዘብ ያለመቻል ችግር መኖሩን ነው የሚያሳየው::

በጋዜጠኝነት እና አክቲቪዝም ላይ የተጻፈ አንድ ሃተታ የሁለቱን ልዩነት እና አንድነት እንዲህ ያብራራዋል::

*"ጋዜጠኝነት በመሠረታዊ ጽንሰ ሓሳቡ መረጃን በማደን፣ በመሰብሰብ፣በማዋቀርና በማንጠር እንዲሁም በመዘርጋትና በማከፋፈል በሕብረተሰቡና በዴሞክራሲያዊ የሕግ ማዕቀፍ በሚሠራ መንግሥት መካከል ባለው የኃላፊነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና የሕግ የበላይነት መስተጋበር ውስጥ የሚንቀሳቀስ የሙያ ዘርፍ ነው:: በአንጻሩ "አክቲቪዝም" በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን ሥር የተማከለን ማሕበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ስሜትን፣ አመለካከትን ብሎም ጥቅምን ለማስፈፀም በሚደረግ የለውጥ ግብ ውስጥ የተሰለፈ ሆኖ ለዚህ ለውጥ እውን መሆን አውዱና ግብዓቱ በሚፈቅደው መጠን አስቀድሞ የታሰበ የሕብረተሰብ ክፍልን በማንቃትና በማደራጀት ሥራ የሚጠመድ ዘርፍ ነው:: ከሁለቱ መሠረታዊ አፈጣጠር የምንረዳው ነገር ቢኖር ጋዜጠኝነትና "አክቲቪዝም" ሕብረተሰቡን በማስተማርና በማንቃት ረገድ የሚጋሩት ቀጭን መስመር ቢኖርም በጋዜጠኝነት ሞያ ዉስጥ ግድ የሚሉ እሴቶች ማለትም ተጠያቂነት፣ አሳታፊነት፣ ዕውቀትንና ክህሎትን በኃላፊነት የመከወንና በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የመንቀሳቀስ ሁነቶች በአክቲቪዝም ውስጥ ችላ የሚባሉበት ብቻ ሳይሆኑ የማይታሰቡ አጋጣሚዎች ሆነው መምጣታቸው ነው::"*

በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን እንዲሁም ሥነምግባር ዙርያ በርካታ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን ያበረከቱት ፕሮፌሰር ቦብ ስቲልን በጋዜጠኝነት እና አክቲቪስትነት መካከል ያለዉን ልዩነት ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ::

*"An activist is someone who pushes a cause without aiming to reflect an alternative viewpoint, one who makes no attempt to remain objective and impartial while a journalist must always aim to avoid becoming emotionally and politically involved in the issues he/she is covering." በግርድፍ ትርጉሙ "አክቲቪስት ማለት የትግል መነሻን ዉጤታማ ለማድረግ በሚደረግ ሂደት ውስጥ ሌሎች አማራጭ አመለካከቶችን ለማስተናገድ የማያስብና ምክንያታዊና ገለልተኛ ለመሆን የማይጥር ሲሆን ጋዜጠኛው በአንፃሩ የራሱን ግላዊና ፖለቲካዊ ስሜት ከሚዘግበው ዘገባ ማራቅ የሚጠበቅበት ዘርፍ ነው::"*

## ጋዜጠኝነት ወይስ አክቲቪዝም

የኢትዮጵያ ሚዲያ እንዳለመታደል ሆኖ አጀንዳ ፈጣሪ መሆን ሲገባው አጀንዳ ተቀባይ የሆነበት፣ ማህበራዊ ሚዲያውን መምራት ሲገባው በማህበራዊ ሚዲያው እየተመራ የተጓዘበት፣ ተዓማኒነት በርሱ በኩል ማለፍ ሲገባው ዕምነት እያጣ የሄደበት ወቅት በመሆኑ እድገቱ ላይ አሉታዊ ጫና እንዳሳደረበት ጥርጥር የለም::

ያም ሆኖ ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የመንግስትም ሆነ የግል የሚዲያ ተቋማት ዘንድ ከጋዜጠኝነትና "አክቲቪዝም" የትኛው ገዝፎ ይስተዋላል የሚለው ነው::

በሃገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ መንግስት አገሪቱ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ ተቋማት ህልውናቸው ቀጣይነት የሚኖረው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የቅኝት ምልከታና በልማታዊ ዴሞክራሲ የአተገባበር አቅጣጫ የሚዛን ልኬቱን ካሟሉ ብቻ ነው የሚለው አቋሙ ከሞያዉ መሠረታዊ ባህሪያት ጋር የሚላተም ሆኖ አሁን ለደረሰበት የውድቀት ደረጃ አድርሶታል::

የጋራ መግባባትና ገዢ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮት በሌሉበት ሁኔታ የኔን የሃሳብ መንገድ ብቻ አቀንቅኑ የሚለው የአሁኑ የመንግስት አቋምም ቢሆን ዞሮ ዞሮ ከነችግሮቻቸው ጋዜጠኝነትን እየሞከሩ ያሉ ወገኖችን ፖለቲካዊ "አክቲቪዝም"ን እንዲቀላቀሉ ገፊ ምክንያት ሆኗቸዋል እየተባለ ነው::

አንድ ጋዜጠኛ ማንኛውም ለህዝብ በሚያደርሳቸው ስራዎቹ ውስጥ አድሎ፣ኢፍትሀዊነት፣ የውሸትና ታማኝ ያልሆነ መረጃን ማቅረብ የጋዜጠኝነት መርሁ አይፈቅድለትም:: በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ አክቲቪስት ነን የሚሉ ጋዜጠኞች የጋዜጠኝነትን መርህ ባልተከተለ መልኩ አድሎ የተላበሰ አሰራርና አዘጋገብ ተከታይ ሆነዋል:: በተለይ እያቀጠቀጡ የመጡት የብሄር ተኮር ሚዲያዎች ቆመንለታል የሚሉትን አላማ ለማሳካት ጋዜጠኝነታቸውን ሽፋን በማድረግ በእጅጉ ሲተጉም ይስተዋላሉ::

በዚህ ስሌት እንደነጀዋር ያሉ የብሮድካስት እና የህትመት ሚዲያ ባለቤቶች በማህበራዊ ሚዲያ ቀንደኛ አክቲቪስት ሆነው ሲገኙ ሙያው መስመሩ የት እንደሆነ እንዳይገባ ሆኖ ሲጣረስ ነው የምናየው::

▶እንደእስክንድር ያሉ አስቀድሞ ታሪካቸው ጋዜጠኛ የሆነ አሁንም የግል ህትመት ውጤት ባለቤቶች የሆኑ ዜጎችም በተመሳሳይ አንድ አቋም ይዘው አክቲቪዝም ላይ ሲያተኩሩ የኢትዮጵያ ሚዲያ እጣ ፈንታ በሁለቱ ሚና መደበላለቅ ላይ ተንጋሎ መውደቂያ ቀኑን እየተጠባበቀ ያለ ያስመስለዋል፡፡

## አክቲቪስቱ ማነው?

አክቲቪስትነት ሙያ አይደለም ይላሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት እና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ቤት ረዳት ፕሮፌሰር ንጉሴ መሸሻ፡፡ አንድ ሙያ ሙያ ለመባል ስልጠና ወይም ሰርተፍኬት፣ ያንን ሙያ የሚያስተዳደር ተቋም እንዲሁም በዚያ ሙያ የሚገኝ ቋሚ መተዳደሪያ ሊኖረው ግድ ነው፡፡ በዚህ ስሌት አክቲቪዝም ሙያ አይደለም፡፡ አክቲቪዝም ማንም የፈለገ ሁሉ የሚገባበት ነገር ግን በብቃቱ እና ማሳደር በሚችለው ተጽዕኖ መጠን የሚተገበረው እና በዙሪያውም ያነሳውን ሃሳብ የሚደግፍ ብዛት ያለው ህዝብ የሚከተለው ሊሆን ይገባል፡፡ ጋዜጠኝነት ሙያ ሆኖ የሚያገለግለው ያልተገደበ የህዝብ ስፋትን እንዲሁም ያልየለየ ሁሉን አቀፍ ማህበረሰብን በመሆኑ በተከታይ ብዛት ሊለካ የሚችል አይደለም፡፡ ብዙዎች አሁን ከፍ ያለ እውቅና እያሰጠ በመጣው እና እንደማዕረግ በተቆጠረው ነገር ግን ከራስ በቀር ማንም በማይሰጠው አክቲቪስት የሚል መጠሪያ ራሳቸውን ኮፍሰው ከሚዲያ በላይ ተዓማኒ እና ከሁሉ በላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነን እያሉ ይታያሉ፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ የሚከተላቸው ምናልባትም መቶ እና ሁለት መቶ ሺህ ህዝብ 110 ሚሊዮን ህዝብ ባላት ኢትዮጵያ ላይ ከሚሰሩ ሚዲያዎች የላቀ ተዓማኒ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ያደረጋቸው እየመሰላቸው ራሳቸውን ለማንገስ ሲሮጡም ይታያሉ፡፡

በዚህ ስሌት ዛሬ ለማህበራዊ ፍትህ፣ ለዜጎች እኩልነት እና ለጋራ ተጠቃሚነት እንዲሁም ለአንድ የጋራ ግብ የሚጮህ እና የሚታገል ሰው እንደትርፍ ጊዜ ሃሳብ አቅራቢ፣ የመበታተን፣ በዘር የመለያየት፣ የአንድ ብሄር የበላይነትን የማስፈን፣ መንግስትን የመቀየር እና ፖለቲካን በፈለጉት መንገድ የመቀየድ አላማ ይዞ የሚሰራው ደግሞ አክቲቪስት በሚል ስም ተጠምቆ “ማነው አክቲቪስቱ” የሚለውን ለማወቅ ከብዷል፡፡ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪው ሳይሰፋ እና በልቶ የማደር እና መሰረታዊ አገለግሎቱ ሳይሰፋ የፖለቲካ ተሳትፎው ከሚገመተው በላይ ማሻቀቡ አክቲቪስት ነን የሚሉ ሰዎች እንዲፈጠሩና ዓላማ ይዘው ሃሳብ እንዲመሩ እድል ቢፈጥርላቸውም በአንጻሩ ይህች ሃገር የምትፈልገው አይነት የጎደሉ ህልቆ መሳፍርት ችግሮቿን የሚፈታ አክቲቪስት ግን ያለመኖሩ በኢትዮጵያ ከማህበራዊ ፍትህ አክቲቪስት ይልቅ የ“ፖለቲካ አቀንቃኝ” ብቻ እንዳለ እንዲገመት ያደርገዋል፡፡

## አክቲቪስትነትን ለዝና እና ንግድ

አሁን ባለው ሁኔታ በዘር በተቧደነ እንደኢትዮጵያ ባለ ሃገር ስለአንድ ብሄር ወግኖ የሚከራከረው እና በሌለ ትርክት የራስን ጀግና ለመፍጠር የሚታትረው ሁሉ ክብር እያገኘ በአንጻሩ ለእውነት ፣ ሚዛናዊነት፣ ከአድልዎ ነጻ እና ፍትሃዊ ዘገባ አቅራቢ ሆኖ የቆመው ጋዜጠኛ ደግሞ ዕምነት እያጣ እና ሚዲያውም ተገፍቶ ከመስመር እየወጣ የሃገራችን የመረጃ ፍሰት አውድ እየተበላሸ ነው፡፡ ይህንን አጋጣሚ ከሚጠቀሙበት እና አክቲቪስት በሚለው ቆብ እየተንቀሳቀሱ ለዝና እና ክብር ማግኛ ተግባር ያዋሉ ብዙ ናቸው፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ባላቸው እውቅና ተጠቅመው መንግስትን እያስፈራሩ፣ ህዝብንም እያስፈራሩ የሚደግፉትን አካል ግብር እያስጣሉ በፖለቲካው ደርሶ ፈትፋች እና አማሳይ የሆኑ አክቲቪስቶች ብሄራዊ ጀግና አይነት ምስል ይዘው ሲሳሉ እያየን ነው፡፡ ብዙዎቹ ከመንግስት ቀረቤታ፣ ድጋፍ፣ እርጥባን እና ጥቅማጥቅም ያገኙ ሆነዋል፡፡ ብዙዎቹ እንወክለዋለን ከሚሉት ማህበረሰብ እና ዘር ለልፋታቸው ቅቤ ሲቀቡ እና ቁርበት አንጥፉልኝ ሲሉም ይታወቃሉ፡፡ ሚዲያ ለሚሰራው ስራ አድናቆት እና ውግንና ሳይሆን እምነት ብቻ ለማግኘት የሚንቀሳቀስ ለማንም ያላደላ ለእውነት ብቻ የቆመ ተቋም በመሆኑ አክቲቪስቶቹ የሚፈልጉትን ሊፈልግ፣ እነርሱ የሚሰጣቸውን ሊቀበል አይችልም፡፡ ለዚህ የራሱ ስነምግባር ያግደዋል፡፡

ዛሬ በአክቲቪስትነታቸው የታላላቅ ሚዲያ ተቋማት ባለቤት የሆኑ ብዙ ናቸው፡፡ በአንድ በኩል ሃብት እያካበቱ በሌላ በኩል ተደብቀው ጦር እየሰበቁ ጥቅማቸው እንዳይቋረጥባቸውና ተረስተው ከመድረክ እንዳይወርዱ የሚጥሩም ብዙ ናቸው፡፡

## የመንግስት ሽፋፋ አቋም

## በአክቲቪስትነት እና ጋዜጠኝነት ላይ

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግስት ወደወንበሩ ሲመጣ አስቀድሞ ነጻነት የሰጠው ለሚዲያ ዘገባ እውቅና በመስጠት ነው፡፡ የታሰሩ ጋዜጠኞችን ፈትቶ፣ የተዘጉ ሚዲያዎችን አስከፍቶ ጋዜጠኞችን ከስደት መልሶ በሰራው መድረኩን የማመቻቸት ስራ ሊመሰገን ይገባል፡፡

በአንጻሩ ግን ይህንን በር ከፍቶ ሌላውን በር በመዝጋት ሃገር ተዓማኒ ሚዲያ እንድታጣ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ ሚዲያን የሚያዳክሙ የሚመስሉ እርምጃዎችን እየወሰደ ተጻራሪ ሃሳቦችን ያስወደገ የሚመስል አሰራር እየዘረጋ በድጋፍና ተቃውሞ መካከል የቆመች ኢትዮጵያን እየመሰረተ ያለም ይመስላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁንም ለሚዲያ ካላቸው በጎ ምልከታ ይልቅ ወቀሳ እና ትችታቸው ያመዝናል፡፡ ሚዲያው ባለመጠናከሩ በማህበራዊ ሚዲያ ተገፍቶ መፈናፈኛ መድረክ ማጣቱ ዞሮ ዞሮ የሚጎዳው የሚመሩትን ሃገረ መንግስት ሆኖ ሳለ ይህንን ከግምት ባለማስገባት ከሚዲያ ይልቅ አክቲቪስትን ሲያንቆለጳጵሱ ነው የታዩት፡፡ በርሳቸው መንግስት አክቲቪስቶች ከመገናኛ ብዙሃን የላቀ ክብር እና ስፍራ ሲሰጣቸው በአንጻሩ ሚዲያ የወቀሳ እና የትችት ማጠራቀሚያ ጎተራ ሲሆን እየታየ ነው፡፡ ባለስልጣኖቹ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ግለሰብ ፖለቲከኞች ሳይቀሩ ጋዜጠኛውን እና አክቲቪስቱን ባለመለየት በጋራ ጅራፍ ሲሸነቁጡ እና በተለይ ሚዲያውን ሲተቹ ነው የሚስተዋለው፡፡ አንድ አስተያየት ሰጪ እንደሚናገረው “ይህ መንግስት በሶሻል ሚዲያ ከፍ ያለ ንቅናቄ በተፈጠረለት ግፊት ከውስጥ ፈንቅሎ የወጣ የለውጥ ሃይል ያመጣው መንግስት በመሆኑ ይህንን የአክቲቪዝም ሚና ይፈራዋል፡፡ በአንጻሩ በህግ እና በስነምግባር የታጠረውን ጋዜጠኝነት በቁጥጥሩ ስር እንዳለ ስለሚገምት ይንቀዋል፡፡”

## የለውጡ ባለቤት ማነው?

በኢትዮጵያ ከ1983 ጀምሮ የህወሃት ኢህአዴግን መንግስት አምርሮ ሲታገል የነበረው ሚዲያው በተለይም የግል ሚዲያው ነው፡፡ ይህ መንግስት የተከተለውን እና አሁን ሃገር ላለችበት ቀውስ የዳረጋትን ፖሊሲ ተችቶ ጥርስ ውስጥ የተገባውም ሚዲያው ነው፡፡ ፌስቡክ ሳይኖር፣ ኢንተርኔት ሳይታወቅ በኢትዮጵያ የሃሳብ ትግል ላይ ህዝብን ወግኖ ፖለቲካውን እያበራየ ሲያሰጣው እና ውስጠ ሚስጢሩን እየጎለጎለ ሲያቃልለው የቆየው ሚዲያው ነው፡፡ ችግሮች እንዳሉ ሆነው ለኢትዮጵያ የስርዓት ለውጥ መፈጠር ቀዳሚው ደርሻ የአክቲቪስቶች ሳይሆን የሚዲያው ነው፡፡ ኢህአዴግን የጣለው በአንድ አመት የተፈጠረ ግርግር ሳይሆን ለ27 ዓመታት በሚዲያው የተካሄደ ያልተቋረጠ ትግል ነው፡፡ የህ ደግሞ በኢትዮጵያ ገሃዜጠኞች አንዲታሰሩ፣ እንዲሰቃዩ፣ እንዲሰደዱ፣ ተቋማቶቻቸው እንዲዘጉባቸው፣ ሰርተው እንዳይበሉ እና በገዛ ሃገራቸው ነጻነት እንዲያጡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንን ፍዳ የተቀበሉት ጋዜጠኞች እንደማናቸውም ስራ ሰርተው መኖር ያቃታቸው አይደሉም፡፡ ሙያዊ ሃላፊነታቸው ከእውነት እና ከህዝብ ጋር መወገን በመሆኑ ነው የዱላው እና የስቃዩ ሰለባ የሆኑት፡፡ ነገር ግን ዛሬ ይህ የሚዲያ በተለይ የግል ሚዲያ አስተዋጽዖ ተዘንግቶ አሁን ማስታወቂያ የተከለከሉ፣ ትኩረት የተነፈጉ፣ ወቀሳ ብቻ የሚዘንብባቸው፣ አያውቁም ተብለው የተናቁ ሚዲያዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በአንጻሩ ግን ግለሰብ አክቲቪስቶች በጥቂቱ ፊትለፊት ተወቃሽ በብዙ የጓዳ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የለውጡ ባለቤት ነንም ብለዋል፡፡ በሚዲያው ሆን ተብሎ መዳከም ሳቢያ በክፍተቱ የገቡ ሁሉ ዛሬ አርበኞች እና ነን ባዮች ናቸው፡፡ ይህ የሃገር ምሰሶ የሆነውን እና አራተኛ መንግስት የሚባለውም ሚዲያ የመናቅ አባዜ የአሁኑን መንግስት የቀደመው መንግስት እጣ ፈንታ ተቀባይ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ሚዲያን በቀረጥ ማዳከም፣ በማስታወቂያ ድርቅ ማክሰም፣ በህግ መቀፍደድ እና በትኩረት መንሳት ማሽማቀቅ መንግስትን በየትኛውም መንገድ ያኮሳምነው ይሆናል እንጂ አያጀግነውም፡፡ ሚዲያው የተዘነጋውን ያህል በባትሪ የሚፈለግበት ጊዜም ብዙ አይርቅም፡፡

# ጋዜጠኛነትና አክቲቪስት፤ የሚጋጩ ሁለት ሙያዎች!

የመናገር፣ የመፃፍና በነፃነት የመደራጀት መብት ለይስሙላ በተቀመጠበት የወያኔ/ኢህአዴግ ሀያ ሰባት አመት ጉዞ፤ በነፃው ፕሬስ ዘርፍ ብዛት ያላቸው የህትመት ውጤቶች፣ በፖለቲካውም ጥቂት የማይባሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ዕውን ሆነው የነበረ ቢሆንም፤ ሥርዓቱ በሚዘረጋቸው የተለያዩ የማጥፊያ ወጥመዶችና ተዛማች ተግዳሮቶች በሁለቱም መስኮች የነበሩት እንቅስቃሴዎች በእጅጉ ደብዝዘው ታይተዋል፡፡

የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግስት የሀሳብ ለውጥና ያልተለመደ የፖለቲካ መስመር ይዞ መምጣቱን ተከትሎ ባለፉት አስራ ሁለት ወራት በሕወሓት መራሹ መንግስት ማነቆ ውስጥ የሰነበቱ በርካታ ሚዲያዎች ወደ ስራ ገበታቸው ተመልሰዋል፡፡ ከጋዜጣና መጽሔቶች ባሻገር የተለያዩ ዌብሳይቶችና ዩቱቦችም በነፃነት እየተንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ በሬድዮና ቴሌቭዥን መስኩም አዳዲስ ቻናሎች ብቅ እያሉ ቢሆንም፣ በዛው መጠን ብሔርን መሰረት ያደረጉና "አክራሪ የጽንፈኝነት መንፈስ" እንዲስተጋባ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ የቴሌቭዥን ጣቢያዎችም ያለ ገደብ እንደልብ ተንሰራፍተው ታዝበናል፡፡

ጋዜጠኝነት ትልቅ ሙያ ከመሆኑ ባሻገር፣ የራሱ ሥነ ምግባርና ኃላፊነት ጭምር ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጋዜጠኛ ትክክለኛና ተዓማኒነትን ያዘለ መረጃ ለሕብረተሰቡ ከማቅረብ ባሻገር፤ ሀገርን የማረጋጋትና ደህንነትን የማስጠበቅ ኃላፊነትም አለበት፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ከዚህ መንገድ ፈር በለቀቀ መልኩ፣ በርካታ ስህተቶች ከጋዜጠኞች እየተመለከትን እንገኛለን፡፡ (በእርግጥ ሁሉም እነሱ እንደሚሉን ጋዜጠኛ መሆናቸውን አምነን መቀበል ቢያዳግተንም) በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የሚደርሱ ግጭቶችና መፈናቀሎች፣ የሰላም ዕጦቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ቢደርስም፤ በዛው ልክ ሕዝብ እውነታውን ማወቅ ቢኖርበትም እንኳ፣ጋዜጠኞች መረጃ ከማድረስ በዘለለ ችግሮች ላይ ሙጥኝ ብለው የሚያቀርቡት ተደጋጋሚ ዘገባ (ቅስቀሳ)፤ መፍትሄ ከማበጀት ይልቅ ነገሮችን ሲያከርርና አላስፈላጊ ደም መፋሰስን ሲያስከትል አስተውለናል፡፡

ስድስት ወር እንኳን በቅጡ ያልሰሩ፣ በተለያዩ ጋዜጣና መጽሔቶች ላይ አልፎ አልፎ በጽሁፍ አቅራቢነት ብቻ ተሳትፎ ያደረጉ፣ በሌላ መልኩ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በዘለፋና በወቀሳ የተሞላ ትችት በማቅረብ ለግል ዝና ሲሯሯጡ የሰነበቱ አንዳንድ ግለሰቦችም፤ ራሳቸውን በጋዜጠኝነት ማማ ላይ አስቀምጠው፣ በነፃው ፕሬስ ውስጥ ለዘመናት መስዋዕትነት ሲከፍሉ የቆዩ እውነተኛ  የህዝብ አገልጋይና ሙያተኞችን በድፍረት ሲተቹ ያየንበት ሁኔታም ተከስቷል፡፡ የጋዜጠኝነት ሙያ ምን እንደሆነ ያልገባቸው  የድል አጥቢያ አርበኛ ሆነው ብቅ ያሉ እንዲህ ዓይነት ግለሰቦች የሚፅፏቸው ጽሁፎችና የሚሰጧቸው አስተያየቶች፤ ግራ ቢያጋቡና ሕዝቡ ላይ መሰላቸትን ቢፈጥሩም የማያስገርመው ለዚህ ይመስላል፡፡

ሌላው ጋዜጠኞች ራሳቸውን ከሙያተኛ ወደ አክቲቪስትነት በማሻገር፣ ድርብ ስያሜ ሲሰጡ ያስተዋልንበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡ አንድ ሰው አክቲቪስት ከሆነ ጋዜጠኛ ሊሆን፣ ጋዜጠኛም ከሆነ አክቲቪት ሊሆን አይችልም፡፡ አክቲቪስት ድምጽ ላጡ፣ ለተቸገሩ፣ በደል ለደረሰባቸው ሰዎች ድምጽ ሆኖ መከራቸውን ማስተጋባት ዋነኛ ስራው እንደሆነ ቢታመንበትም፤ የእኛ ሀገር "አክቲቪስት ነን" ባዮች ግን ለተበደለው ሕዝብ ከመጮህ ይልቅ "የበደለህ ወይም የሚያሰቃይህ ይሄ ብሔር ነውና ተነስ፣ ግደል፣ ጨፍጭፍ" ማለት የሚቀናቸው ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ሰዎቹ የሚሰሩትን ጠንቅቀው የማያውቁ፣ ትርጉሙም ያልገባቸው እንደሆኑ ያመላክታል፡፡

በተግባር የተለያየ ቅርፅና ትርጓሜ የሚሰጣቸው ብሎም እርስ በርስ የሚጋጩትን ሁለት ሙያዎች አንድ ላይ ጨፍልቆ የማየት ነገር ብዙም ግንዛቤ በሌለው ሕብረተሰብ ውስጥ በስፋት እየተስተዋለ ቢሆንም፤ የተጠቀሱት ሙያዎች በትክክልና በተገቢው መንገድ ካልተሰራባቸው ሀገርና ሕዝብን ከመጥቀም ይልቅ ጉዳታቸው የከፋ ይሆናልና፤ በተለይ ከመሬት ተነስተው፣ ያለ አንዳች አሳማኝና በቂ ምክንያት ተራ አሉባልታ እየነዙ፣ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ፣ ብሔርተኝነት በሀገሪቱ እንዲነግስ ቀን ከሌሊት በማህበራዊ ሚዲያዎች ውዥንብር የሚነዙ፣ "አክቲቪስት ነን" ባዮች ከጥፋት ጉዟቸው ሊታቀቡ ይገባል እንላለን፡፡

**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
መለስ ሽኔ
ፍቅርተ ተሾመ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
አሸናፊ ዘደቡብ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09  የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10  የቤ.ቁ. 066/ሀ

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ
ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# ዕድሜና አስተሳሰብ



አሸናፊ ዘደቡብ

የሰው ልጅ ሕልውናውን ከፀሐይ በታች አስመስክሮ በእርሱነቱ ታምኖ፣ ማንነቱን አሳምኖ መኖር ከጀመረበትና በየዘመናቱ የሚከሰቱት ሁኔታዎችም በማኅበራዊው ኑሮ ላይ ለውጥ በማምጣት በባህል እድገት ድርሻ አበርካችነታቸውን ሊያስመሰክሩ ከበቁበት ጊዜ አንሥቶ ዕድሜና አመለካከት በተለያየ አቅጣጫ ሲራመዱ ወይም ለተወሰነ ጊዜ አብረው ሲገሰግሱ ቆይተዋል።

የዕድሜን ነገር አንስተን ለማውሳት ስንቃጣ ከልደት እስከ ሕልፈተ ሕይወት ባለው ዘመን ሰው በራሱ ላይ ያለውን አመለካከት፣ የነበረውን አስተሳሰብና በሌሎችም ሰዎች ላይ የሚኖረውን ግምት መመራመር ያሻናል።

"ልጅነት ከማለት ይልቅ ጅልነት ማለት ይሻላል" በማለት አረጋውያን ሲናገሩ ሰምተናል። እውነትነት ያለው መሆኑንም አንጠራጠርም።

ከልጅነት ዕድሜው የዘለለ ሰው በልጅነት ጊዜ የሠራውን፣ ባለማወቅም ያጠፋውን ባለማስታወስ ልጅ አጥፊ ሆኖ ሲያይ በጅልነት ይመድበዋል። የማስታወስ ችሎታ በደረጀበት የልጅነት ዘመን "በልጅነቴ ጊዜ" ከማለት ይልቅ በጅልነቴ ዘመን ብሎ መናገሩን ይመርጣል።

እንግዲህ አመለካከቱ የንቀት እንጂ የአክብሮት እንዳልሆነ ለመገመት አያቅትም። ልጅነት ማለት እንጭጭነት ማለት መሆኑን፣ ክፉና በጎ ለይቶ ማወቅና የአዕምሮ ጉልምስናው ያልፈቀደለት መሆኑን ለመገንዘብ ባያዳግትም ከጅልነት መደዳ ከማሰለፍ በቀር ሌላ አመለካከት ሊቸረው አልበቃም።

ከሁሉ በፊት መረዳት የሚገባን ልጅነት ከዘመነ እርጅና፣ ከጊዜ ጉልምስና፣ ከባህል እድገት፣ ከቴክኖሎጂ ርቀት ጋር ተጣምሮ በመታሰብ የአመለካከትን ወሳኝነት የሚጠይቅ መሆኑን ነው።

በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት የነበረ ልጅ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ልጅ ጋር ሲወዳደር በአስተሳሰባቸው በእጅጉ ይለያያሉ። አሁን ያለንበትን ዓመት ለማስተዋል ጥረት ብናደርግ ደግሞ የባህል እድገትና የቴክኖሎጂ ርቀት በልጅነት የእድሜ ክልልም ሆነ በሽምግልና ገደብ ሊጫወቱ የቻሉትን ሚና ግልጽ ያደርግልናል።

በገጠር ጭቃ አላልጦ እያድበለበለ ሲጫወት ያደገ ወይም ደግሞ በከተማም ቢሆን ሥልጣኔ ባዘመነው አካባቢ ለማደግ ዕድል ያልተለገሰው አንድ ልጅ፤ የባህል እድገት በመጠቀበትና የቴክኖሎጂ ርቀትም በተመሰከረበት ሥፍራ የጨቅላነት ጊዜውን ሊጨርስ ከበቃ ልጅ ጋር ሲነጻጸር ያ ብዙ እያየ፣ ብዙ እየሰማና የመሰልጠንን ትርጓሜ በአዕምሮው እየቀረፀ ያደገ በእድሜ ከሚበልጠው ገበሬ በእውቀት ልቆ ይገኛል።

የአካባቢ ሁኔታ በአንድ መልኩ ይህን ሲመስል ሲችል በሌላ በኩል ደግሞ ልጅነት በጅልነት ሊተረጎም የሚበቃበትን ሚዛናዊ አመለካከት ብናጤን ጅልነት በሁለቱም ዘንድ በተደላደለ ሁኔታ የሚከሰትበትን ወቅት እናያለን፡ ፡ ይኸውም ገጠር አደጉም ሆነ ከተሜው በየግላቸው ያደጉበት አካባቢ በሚገድብላቸው የሥልጣኔ ክልል መሠረት በዚያው እድገት መጠን አጥፊ የመባል አደጋ ሊያደርስባቸው መቻሉን በማመን ነው ጅልነት ለተወሰነ ወቅት በሁለቱም ላይ ነበር ማለት የሚቻለው።

በፍቅር በኩል ያለውን አመለካከት ብናጤን አንድ ልጅ ለወላጆቹ ያለው ፍቅር በጥገኝነት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ ቢታወቅም፤ ሕጻኑ ስለጥገኝነቱ የሚረዳው አንዳችም ነገር ስለሌለ ለእርሱ የሚደረገውን ሁሉ እንደ ልዩ ውለታ አይቆጥረውም። እንዲያውም አባት ወይም እናት ልጆቻቸው ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ትናንሾቹ ጨቅላዎች ያውቃሉ ብሎ ለመበየን ያስደፍራል። በልቅሶም ሆነ በኩርፊያ መብታቸውን ያስከብራሉና!

የልጅን አስተሳሰብ ወደ ወላጆች መልሰን አንድ ልጅ በአባትና በእናቱ ላይ ምን ዓይነት አስተሳሰብ እንዳለው ለማወቅ እንችል ዘንድ ብንመራመር የጨቅላነትን ትርጓሜ ይበልጥ እንድንገነዘብ ይረዳናል።

ትንሹ ልጅ የአባቱን ክንደ ብርቱነትና ዐዋቂነት በማድነቅ በአባትነቱ ይመካበታል። የእናቱን ውበት ባለሙያነትና ብልኀነት በማመን በወላጅነቷ ይኮራባታል። የዛለ ክንድ ያለው ጥበብ የጎደለው አባት፣ ወይም የውበት ጸጋ ያልተላበሰች የስንፍና አምባ የሆነች ገልቱ እናት ቢኖረው እንኳ የልጁ አመለካከት ሚዛናዊ ዳኝነትን ጠብቆ ብስለት የታከለበት ባለመሆኑ፤ አባቱን የወንዶች ሁሉ የበላይ በማድረግና እናቱንም እንደ ማለፊያ ሴቶች ምሳሌ በመውሰድ ከእነሱ በላይ ምንም ያለ አይመስለውም።

ውሎ እያደር ግን ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካና እንጭጭነት ለብስለት ቦታ እየለቀቀ አካል ሲደረጅ አዕምሮም የማሰብ ችሎታውን ሲያጎለብት የአባቱን ዕውቀት መመራመር የእናቱንም ፍጹምነት መጠራጠር ይቀጥላል።

ከመመራመርና ከመጠራጠር አልፎ ይሄድናም በለጋነት ዘመኑ የደረሰበትን ውሳኔ ይከልሰዋል፡ ፡ በዚህን ገዜ እንግዲህ የውሳኔውን ክለሳ ሊቀበሉ በማይሹት ወላጆችና በእርሱ መካከል ያለመጣጣም ይፈጠራል። "ይህንና ይህን ነገር አልቀበለውም አላምንበትም" ማለት ሲፈጠርና የወላጆቹን እስከዚህም በዕውቀት ያለ መጠበብ በአስተሳሰብም ያለመራመድ በግልጽ ለመናገር ሲሞክር "ምነው ልጄ የጥጃ ቀንዳም ሆንክብን" ማለት ይመጣል።

"ዕድሜና አመለካከት" በዚህ ወቅት ማንነታቸውን በማሳወቅ የአስተሳሰብን ልዩነት ገሀድ ያወጣሉ። በእድሜ የገፉ አረጋውያን የጉልማሶችን ጥበብ በልባቸው ቢያደንቁና አንዳንዶች የዘመንን ዘመናይነት አጽድቀው ለባህል እድገት ያላቸውን ከበሬታ ከመግለጽ ባይቆጠቡም "አይ! የልጅ ነገር !" ማለታቸው የማይቀር ነው።

እዚህ ላይ እንግዲህ የ "ቅናት" መሆኑን እናያለን። መንፈሳዊ ቅናት ሊሰርፅ የሚችለው ከቅን አመለካከት በመሆኑ "ምነው ዛሬ እኔም እንደ እርሱ ጉልማሳ በሆንኩ ኖሮ…" በማለት እርጅናን ከመኮነን እልፍ ብሎ ካለመሄዱም በላይ የጎልማሳውን ጥበበኝነት ወይም ሥልጣኔ ያዘመነውን ብልኃት በአንክሮ ከማዘከር አይታቀብም። ይህን መሰሉ መንፈሳዊ ቅናት የሚገኘው ግን ጥቂት ቀለም በደበደባቸው አረጋውያን ዘንድ ብቻ በመሆኑ በሀገራችን እምብዛም አይከሰትም።

በአመዛኙ ለዓይን እማኝነት የበቃንበት ሁኔታ "ቅናት" ብቻ ሳይሆን "ቀንቶ መናቅ" ስለሆነ የጎልማሶች ማለፊያ ተግባር እንደ መናኛ እየተቆጠረ ሊሄድ በቅቷል። በአኗያው ደግሞ የጎልማሳው አመለካከት የዚያኑ ያህል የፍተሻ ጉልበት ተችሮት ሲገኝ የዕወቀት ችሎታችንን ያበረክተዋል።

በነበረው ምጥን የትምህርት መዳረስ ወይም ፍጹም ያለመኖር በመውተርተርና በብርቱ በመፍጨርጨር ራስን "አንቱ !" ለማሰኘት የበቁ የሀገር ዳር ድምበር ተከብሮ ይኖር ዘንድ የታገሉ እነርሱነታቸውንም በእድንን ሀገሬነት ያሰመሰከሩ፣ ማለፊያ ጸሐፍት ዕውቅ ሊቃውንት ለመሆንም የቻሉ አረጋውያን አባቶችና አረጋውያት እናቶች በጉልማሶች ዘንድ ሲናቁ እናያለን። ደራሲ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት አርአያ በተሰኘው መጽሐፋቸው ይህንኑ በሚገባ ጠቅሰውታል።

ገጸ ባሕርይ የሆነው አርአያ ትምህርቱን አጠናቆ ከፈረንሣይ ሀገር ከተመለሰ በኋላ የሥራ ምደባ እንዲደረግለት ቤተ መንግሥት ደጅ በጠናበት ወቅት "አንድ ሽማግሌ ሀብታም መኮንን" አግኝተወት ስለነበር፤ የተለዋወጡዋቸውን ቃላት ብንመለከት፣ ባላንጣነት የቱን ያህል የርዕሳችን ማስተንተኛ ሊሆን እንደሚበቃ ዓይነተኛ ምስክርነቱን ይሰጠናል።

" ለመሆኑ ምን ተምረህ መጣህ? "

"የእርሻ ትምህርት"

"የእርሻን ትምህርት ምን ትምህርት ትለዋለህ! እኛ የትም ሳንሄድ፣ ማንም ሳያስተምረን ዐውቀን እየሠራንበት የለምን፤ ለምን? ሰው ሀገር እስኬደህ ልጄ"

ይህ አባባል የባላንጣነት መንደርደሪያ የሆነውንና "ቀንቶ መናቅ" የተሰኘውን ሁኔታ ያሳየናል።

የሁለቱን ገጸ ባሕርያት የንግግር ልውውጥ ደራሲው በዚህ ከደመደሙ በኃላ "ይህ አስተያየት በሽማግሎቹ ሁሉ ላይ ያለ ▶

▶እንደሆነ፣ በእውነቱ ከወጣቱ ጋራ ምንም አልተጣጣሙም ማለት ነው። እነርሱ እኛን እንደ መደገፍ ዐውቀው ቦታ እየለቀቁልን በማበረታት ፈንታ የባላንጣነት መንፈስ ካደረባቸውማ ይህ ከፍ ያለ ጉዳት የሚ ፈጥርነው እኮ” ሲሉ ባላንጣነትን ኮንነውታል።

“መንፈሳዊ ቅናት” በነባራዊነቱ ደንድኖ ሲገኝ ከተፈጥሮ የሰረጸ መሆኑን አውቀን፣ እንደ ሁኔታውና እንደአመጣጡ መቀበል ስንችል “ቀንቶ መናቅ”› ወይም አዘንባይነቱ ወደ ምቀኝነትና ወደ እብሪተኝነት የሚያጋድለውን “ባላንጣነት” በደስታ ለማስተናገድ እንቸገራለን።

ወደ ጡረተኛነት ዕድሜ ክልል በመቃረብ አንድ ወይም ሁለት ዓመት ፈሪ የሆነው አዛውንት ዘመነ ሽበቱን በዕረፍት ለማሳለፍና የትግል ዓመታቱን በማለፊያ ትዝታ ለማዘከር በናፍቆት መጠበቅ ሲገባው ሐሳቡን ሁሉ አብከንክኖ ይገኛል።

ይህም በመሆኑ “ዕድሜና አስተሳሰብ” ጣምራ ሚናቸውን መጫወት ይጀምራሉ። “እኛ እንግዲህ ተዳርሰናል። እስቲ የሚተኩት ሲሠሩ እናያለን” በማለት የነገው ጡረተኛ አስተሳሰቡን ገሀድ ያወጣዋል።

ዕድሜና አስተሳሰብ “በየዘርፉ” ከፍ ያለ ሚና ለመጫወት ይችላል። “ዕድሜና አስተሳሰብ” በቋንቋው ላይ እንኳ ያለው የድርሻ አበርካችነት ይህ ነው አይባልም፡፡ ጎልማሳው የ አረጋዊውን የጠራ ቋንቋ አጠቃቀም ስልት እንደ ኋላ ቀር ቆጥሮ ይንቀዋል። የእድሜ ባለጸጋው በበኩሉም በቴክኖሎጂ ርቅቀት ሳቢያ የተፈጠሩትን የአባባል ፈሊጦች እየሰማ “የዛሬ ልጅ አማርኛውን አበላሽቶታል” ሲል ያላላዋል።

አለባበስ፣ አበላል፣ የሰላምታ ልውውጥ እና የመሳሰሉት ሁሉ በየግላቸው ዕድሜና አስተሳሰብን አቃንተው ወይም አወላግደው እንደ ጊዜው ያስቀምጡታል።

በርካታ ሊቃውንት እንደሚሉት ጎልማሳው የሚችለውን መርጦ ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር ቢያዋህደው፣ አረጋዊውም የጎልማሳውን መጠበብ አምኖ የባህል እድገት ያለበሰውን ዕውቀት እንዲያካፍለው ቢፈቅድ አስተሳሰቡ የቀና እንደሚሆን ያምኑበታል። ቀንቶ መናቅንና ባላንጣነትን አስወግዶ ማለት ነው።

ግና ዳሩ ይህ እንዳይሆን “ዕድሜና አስተሳሰብ” ዘወትር ባሕርይ ሆነው አይላቀቁትምና ከተፈጥሮ ጋር ትግል እያደረጉ ራስን ወደ ቅን ጎዳና ለመምራት መጣጣር ብቻ ነው።

# በዜጎች ለዜጎች

**ፍቅርተ ተሾመ**

ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ ከግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵያ ጋር እሮብ ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል የጌድኦ ጉጂ ተፈናቃዮች ወደ ቀዬአቸው የማስመለስ እንቅስቃሴውና ሌሎች ተፈናቃዮችን እንዲያገግሙ በሚደረገው ስራ ላይ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ።

ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያና ግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵያ በመግለጫቸው ስምምነቱን ማድረግ አስፈላጊ የሆነው ለተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች አስቸኳይ እርዳታን በማድረግ ለተጎጂዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ነው ብለዋል። ሁለቱም አካላት የዜጎችን ህይወት ማሻሻል ላይ በማተኮር ሰላምን ለማስፈን እቅድ ቀይሰዋል፤ በመሆኑም ውስጣዊ መፈናቀሎች ያገኟቸውን ዜጎችና የጌድዮ - ጉጂ ተፈናቃዮችን መደገፍ እና ተመላሾችንም በማቋቋም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን በመፍጠር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉም ገልፀዋል፡፡

በዚህ የ12 ወር የስራ ዕቅድ መጠለያ፣ የሰላም ግንባታ እና መተዳደሪያ በማመቻቸት ላይ ያተኮረ ነው። የምግብ እርዳታን የማያካትተው ይህ ድጋፍ ከባለፈው ሚያዚያ 24 ጀምሮ ስራውን የጀመረ ሲሆን በተጠቀሱት ድጋፎች ላይ አተኩሮ አስቸኳይ እና ዘላቂ ድጋፉን ለተለያዩ አከባቢ ተፈናቃዮች ከጌድዮ - ጉጂ ዞን ተመላሽ ተፈናቃዮች እንደሚሰጡ አሳውቀዋል።

ተልዕኳችን ለኢትዮጵያ አንዳች አስተዋፅኦ ማድረግ ሲሆን በሰብዓዊ ጉዳዮች ላይ በጊዜያዊነትም ይሁን በኋላ ለሚፈጠሩ ችግሮች ለህፃናቱ ተስፋ መኖሩን ማሳየት ነው። በዚህ የመግባቢያ ሰነድ በሁለቱ ድርጅቶች የጋራ ጥረት የተቀናጀ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ለተፈናቃዮች እና ተመላሾች የተሻለ ኑሮ፣ የማገገሚያ አቅም የሚሆኑ ፍላጎቶች አቅርቦትን በማዳረስ የሰብኣዊ መብታቸውን ጠብቆ እንደሚሰራ የግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የሆኑት አቶ ታማኝ በየነ ገልፀዋል።

የተባበሩት መንግስታት እንዳስቀመጠው በደቡብ ክልሉ ጌድኦ እና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙት ጉጂ ዞኖች ውስጥ በተነሳው ግጭት ወደ 620, 747 የሚጠጉ ሰዎች ተፈናቅለዋል። 261,403 ከጌድኦ ሲፈናቀሉ ከምዕራብ ጉጂ ደግሞ 353,344 ዜጎች ተፈናቅለዋል። በዛው አከባቢ ከተለያዩ ቀበሌዎች ወደ አጎራባች አካባቢዎች የተሰደዱት 15%ቱ በ62 የመጠለያ ማዕከላት የሚገኙት በጌድዮ 32,510 እና በምዕራብ ጉጂ 62,573 ናቸው። በጌድዮ ከሚገኙት 75.3% የሚሆኑት ከቀርጫ ወረዳ (ምዕራብ ጉጂ ዞን) ሲሆን 116,764(58%) የሚሆኑት ደግሞ ከ 23 ቀበሌዎች ውስጥ ከቢብሳ፣ ሰራ ሳባ፣ እገ አባደ ባሊዳ በኪሳ እና ኤላ ፋርዲ ከተባሉ 5 የተለያዩ ቀበሌዎች የመጡ ናቸው።

ይህ ማለት በምዕራብ ጉጂ 57% የሚሆነው በዚያው ዞን ከዚያው ዞን የተፈናቀሉ ናቸው። 36.4% የሚሆኑት የአከባቢው ተፈናቃዮች ከጌዴኦ ገደብ ወረዳ 100,452 የሚሆኑት ዜጎች ማለትም 95%ቱ በአከባቢው ካሉት 12 ቀበሌዎች ውስጥ ከሶስቱ ጨልጨል፣ ባንኮ ዲዳቱና ሃርሙፎ ቀበሌዎች የመጡ ናቸው።

እነዚህ አከባቢውን ያልለቀቁ ተፈናቃዮች የሰብዓዊ ዕርዳታዎችን ማግኘት የቻሉት ካለፉት 3 ወራት ጀምሮ ነው አስቸኳይ ምግብ እና ጊዜያዊ መጠለያ እንዲያገኙ ተደርጓል። እስከ ቅርብ ጊዜ ከ21.013 በላይ የሚሆኑ በጎቲት የጋራ ማዕከል (በገደብ ወረዳ) የሚገኙ ተፈናቃዮች መንግስት በይፋ ባለማመኑ ምክንያት ተደራሽ መሆን አልቻለም ነበር።

በምዕራብ ጎጃም ችግሮቹ የተከሰቱባቸው ቀርጫ፣ ባላኔ፣ ሀምቤላ በሜንዳ እና ቡሉ ሆኖ ወረዳዎች ሆኖ ሳለ ተፈናቃዮቹን መቀበያ ጣቢያዎቹ ከወረዳ ከተሞቹ በመራቃቸው ሙሉ ለሙሉ ማዳረስ አልተቻለም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለቀበሌዎቹ ማለትም ለገላን እና ቢርቢርሳ ኮጆዎ ቀበሌዎች ምግብ ወደ አከባቢው ለሁለት ወር ያህል ዘግይቶ ነው የደረሳቸው።

ግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ለዲያስፖራዎች በተግባር ሀገራቸውን እንዲረዱ ባደረጉት ጥሪ መሰረት እየተገበረ ነው ያሉት ኤድዋርድ ብራውን የወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ ብሄራዊ ዳይሬክተር ይህ እቅድ መንግስታዊ ካልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች ጋር ለማህበረሰቡ እና መንግስት ጋር ለሚደረጉ ጥምረቶች ምሳሌ መሆን የሚችል ነው፡፡ የተቸገሩ ዜጎችን በማገልገል ቤተሰቦችን ህይወታቸው መልሶ በመገንባት እና የግጭቶችን መሰረታዊ ምክንያት በማጤን ዘላቂ መፍትሄን በማመቻቸት ሰላምን ለመገንባት አዲስ ምዕራፍ ይሆናል ብለዋል።

ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነ ክርስቲያናዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። ድርጅቱ ከ40 ዓመት በላይ የሰራ ሲሆን ትኩረቱንም የድሃ ድሃ የሆኑ አከባቢዎች ላይ ያሉ ህብረተሰቦች ላይ ህፃናትን፣ ቤተሰቦችና ማህበረሰቡን ከድህነት እና ኢፍትሃዊነት ለማለቀቅ እንደሚሰራ ይገልፃሉ።

ድርጅቱ በኢትዮጵያ ቢሮውን በ1967 የከፈተ ሲሆን ችግሮችን በማቅለል፣ በልማት እና መልሶ ማገገም ስራዎችን በአብዛኛው በመስራት ቆይቷል። አሁን ላይ በትምህርት፣ ውሃ፣ ንፅህና፣ ጤናማ አመጋገብ አስቸኳይ እርዳታዎች፣ እምነትና ልማት የምግብ ዋስትና የአየር ንብረት እና የመሳሰሉት እቅዶች ቀይሶም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵ ያም በበኩሉ ትርፋማ ያልሆነ በአሜሪካን ሃገር የተቋቋመ በኢትዮጵያውያን ዲያፖራዎች ከስድ ስት ዓመት በፊት የተቋቋመ ድርጅት ነው። በሰብዓዊ መብቶች ላይ የነበረውን ክፍተት ለመመስረቱ ምክንያት እንደሆነው የሚገልፀው ግሎባል አሊያንስ ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ኢትዮጵያ ለተጎጂዎች የገንዘብ እና የህግ ምክር ድጋፍ ማድረግ ላይ እርዳታው ያተኩራል።

ይህ የትብብር እቅድ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ 70,027 ሰዎችን በእርዳታው ተደራሽ ያደርጋል። 30 ሚሊዮን የእርዳታ ብር ይዞ የሚንቀሳቀሰው ይህ ጥምር ፕሮጀክት የሰዎችን ህይወት ከአደጋዎች ለማገገም እንዲያስችል ሰብል እና ከብቶችን በማቅረብ፣ ለዘላቂ ሰላምም ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚሰራ ሲሆን አስቸኳይ መጠለያ እና ምግብ ወጪ የሆኑ ቁሶች በእቅዱ ለታቀፉ ተጎጂዎች ይደርሳል በማለት ገልፀዋል።

**በጠቅላላ ተደራሽ የሚሆኑት ብዛት**

በቦታዎቹ የተጠቁ ግለሰቦች ጠቅላላ ብዛት

228,000 (38,000 አባወራዎች)

ይዳረሳል ተብሎ የሚታሰበው የተፈናቃዮች እና ተመላሾች ብዛት

70,072(11678.6 አባወራዎች)

**ከ1.1 ሚሊየን ዶላር የግሎባል አሊያንስ ፎር ኢትዮጵያንስ ራይት ፈንድ:-**

96.97% ማለትም 1,096,739 ዶላሩ

ለፕሮጀክቱ ግብአት

3.3% ማለትም 30,261 ዶላሩ

ፕሮጀክቱን ለማስኬጂያነት ይውላል

**ዋና ዋና የፕሮጀክቱ ትግበራዎች መጠለያ**

ይዳረሳል ተብሎ የሚታሰበው፡ለ170 ተፈናቃይ እና ተመላሽ አባወራዎች መጠለያ ግንባታ

**ግብርና እና የምግብ ዋስትና**

ይዳረሳል ተብሎ የሚታሰበው፡ ለ800 ተፈናቃይ እና ተመላሽ አባወራዎች

**ሰላም ግንባታ**

ይዳረሳል ተብሎ የሚታሰበው፡ 57,000 ተፈናቃይ እና ተመላሾች

**አስቸኳይ መጠለያ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጎማዎች**

ይዳረሳል ተብሎ የሚታሰበው፡ 1000 ተፈናቃይ እና ተመላሽ አባወራዎች



ነአመን ዘለቀ

# ከወጡበት ማህበረሰብ ይልቅ ኢትዮጵያዊነትን የሚያስቀድሙት፤

## የደርግ ጀነራሎችና የሸንፈቶቻቸው ምክንያቶች!



የዛሬ 10 አመት 2ኛው የጀግኖች ዓመታዊ ክብረ በአል በዋሽንግተን ዲሲ በከፍተኛ ድምቀት ተከብሮ ነበር። ከቀድሞ አየር ኃይል፣ ከሐረር እካዳሚ፣ ከምድር ጦር፣ ከአየር ወለድ፣ የባህር ሃይል የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት ፤ ከሲቪል ደግሞ አርቲስት እክቲቪስት ታማኝ በየነና እኔ አባል የነበርንበት ኮሚቴ ነበር።የመጀመሪያው የጀግኖች ምሽት ዋና የክብር እንግዳ የአየር ሀይል አብራሪ የነበሩት ብ/ጄነራል ለገሰ ተፈራ፣ የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የጀግና ሜዳሊያ ተሸላሚ ነበሩ። በሁለተኛው አመት ደግሞ የክብር እንግዶች የነበሩት ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተማሪያምና ብ/ጄኔራል ካሳዬ ጨመዳ ነበሩ። ሀለቱ ጀነራሎች ለበዓሉ ተጋብዘው ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ በተዘጋጀው የመተዋወቂያና የውይይት ፕሮግራም ወቅት የሚከተለውን ጥያቄ ለብ/ጀኔራል ተስፋዬ አቅርቤላቸው ነበር።

በሰላም ጊዜም ሆነ በጦር ሜዳ ውሎ አብረው ከሰሯቸው የጦር ጄኔራሎች መካከል በጦር አዠኘርነት ብቃታቸውና ችሎታቸው ትልቅ ግምት የሚሰጡት ለየትኞቹ ወይም ለእነማን ነው? የሚል ። እሳቸውም የመለሱልኝ መልስ እንደሚከተለው ነበር " ሜ/ጀኔራል መርዕድ ንጉሴ" (ኤታ ማጆር ሹም/ቺፍ ኦፍ ስታፍ የነበሩትና በ 1981 መፈንቅለ መንግስት ራሳቸውን ያጠፉት፣ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ) ፣ "ሜ/ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ" (ኤርትራ የነበረው የ2ኛ አብዮታዊ ሰራዊት ዋና አዛዥ፣ ከኦሮሞ ማህበረሰብ)፣ "ሜ/ጀኔራል አበራ አበበ" (የመከላከያ የዘመቻ ዋና መምሪያ ሃላፊ፣ ከአማራ ማህበረስብ) እንዲሁም "ሜ/ ጀኔራል ክንፈ ገብርኤል ድንቁ" (ከመፈንቅለ መንግስት ሙከራው መክሸፍ በኋላ የዘመቻ ዋና መምሪያ ሃላፊ የነበሩት፡ ከጉራጌ ማህበረሰብ) ። አራቱን ነበር የጠሩልኝ።

ለምን? ብዬ ስጠይቅ የሰጡኝ መልስ፣ "በእያንዳንዱ ሁኔታ በምሽግም፣ በጦር ሰፈ ርም፣ በውጊያ ወረዳም ነገሮችን በፍጥነት አይቶ ፣ እያንዳንዱን የተዛነፈ፣ ልክ ያልሆነ፣ ችግር ያለበት ጉዳይ አውቆ ፈጣንና ትክክለኛ መፍቴሄ በመስጠት " የሚል ነበር። ከወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀት/(ንድፈ/ ሃሳብ ቴዎሪ) ብቻ ሳይሆን የወታደራዊ ሳይንስና ጥበብን አዋህደው (በመሬት ላይ የወረደ ሰፊ ልምድና ከተሞክሮ) እንዲሁም ከምናባዊ (ኢማጂኔሽን) ጥንካሬ የሚመጣ ልቀት ነበራቸው ማለት ነው። ይህን መሰል ልዩ ችሎታ በሚመለከት ንድፈ ሃሳቦችና ልዩ ልዩ ጽንሰ ሃሳቦችን በማመንጨት ለዘመናዊ የውትድርና ሳይንስና የስትራቴጂ አስተምሮና እሳቤዎች መሰረት የጣለው ጀርመናዊው ካርል ቮን ክላሽዊትዝ የሰጠው ስያሜ ኩፕ ዲ ኦል coup d' oeil የሚል እንደሆነ ይታወቃል። እንደ ናፖልዮን ቦናፓርት አይነቶቹን ወታደራዊ ጄኒዎች (Military Genius) የነበራቸውን ልዩ ክህሎት ይመለከታል። ከፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚመነጨው (coup d' oeil,) an …"inward eye", an ecological sensibility. The man responsible for evaluating the whole must bring to the task the quality of intuition that perceives the truth, at every point…) በሚል ካስቀመጠው ጋር ተዛማጅ ነው።

ብ/ጀነራል ተስፋዬ ሃብተማርያም ከጉራጌ ማህበረሰብ የወጡ ናቸው። እንደሚታወቀው የመጨረሻ ከፍተኛ ደረጃ ወታደራዊ ሽልማት ማለትም "የሕብረተሰብዓዊት ኢትዮጵያ የጀግና ሜዳሊያ" ተሸላሚ ነበሩ። ናቅፋ ላይ በሻለቃ ማሞ ተምትሜ የሚመራው የ15ኛ ሻለቃ ጦር በሻዕቢያ/በህዝባዊ ግንባር ተከቦ በጀግንነት እየተከላከለ ለሳምንታት ሲዋጋ፣ ያንን ከበባ ለመስበር የአየር ወለድ ጦር ይዘው ውጊያ ወረዳው ላይ ከአንድ የሻምበል ጦር ጋር ከአውሮፕላን ላይ ዘለው ውጊያውን ተቀላቀሉ። ከዚያም ለረጅም ቀናቶች ከተዋጉ በኋላም፣ በመጨረሻም ከበባውን ሰብረው ወጡ። የወገንን ጦርም ተቀላቀሉ። ሰብረው የወጡበት ቦታም "ተስፋዬ በር" በሚል ስያሜ ይጠራል። ብ/ ጄኔራል ተስፋዬ የኢትዮጵያ አየር ወለድ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩ፣ የሐረር የጦር አካዳሚ ምሩቅ፣ በአሜሪካ፣ በእስራኤልና በሌሎች የጦር ት/ቤቶች የስፔሻል ፎርስ፣ የአየር ወለድ ወታደራዊ ትምህርቶችና ስልጠናዎች የወሰዱ "የጦር ሜዳ ውሎየ " በሚል ርዕስም የጦር ሜዳ ትዝታዎቻቸውን የጻፉ በጀግንነታቸውና ወታደራዊ ችሎታቸው ልቀት ላይ የደረሱ ጄኔራል ናቸው። በርካታ ስኬቶችና ውጤቶች ያስመዘገቡ እኚህ ስመ ጥር ጀነራል ናቸው ስለ አራቱ ጄኔራሎች ምስክርነታቸውን የሰጡት። ለአራቱ ጀኔራሎችና ስለሌሎችም ከፍተኛ ወታደራዊ መሪዎች ተመሳሳይ ምስክርነት የሚሰጡ የጦር ሠራዊት ከፍተኛ መኮንኖች ብቻ ሳይሆኑ፤ ተመሳሳይ ውይይት ለማድረግ ዕድሉ ካጋጠመኝ የአየር ኃይልና የባህር ኃይል ከፍተኛ መኮንኖችም ጋር የተደረጉ ውይይቶችም ወቅት የተረዳሁት ተመሳሳይ ምልከታ ነው። ኤርትራ በምመላለስበት ጊዜም የኤርትራ ግንባር ተዋጊና አዋጊዎች ለአንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ጀነራሎች ከፍተኛ ግምትና ክብር እንደነበራቸው ለማወቅ ችያለሁ። ስለከፍተኛዎቹ የጦር አዛገሮች በሚወራበት ግዜ አድናቆቱ በአንድ ወቅት የ2ኛው አብዮታዊ ሰራዊት ዋና አዛዥ የነበሩትን ሜ/ጀነራል ረጋሳ ጂማን ይጨምራል።

በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው ▶

የፓለቲካና የወታደራዊ ሁኔታዎችና ሂደቶች ብዙ ትንተናዎችና ልዩ ልዩ ምልከታዎች ስንሰማ ኖረናል፡፡ በርካታ መጻሕፍትና፣ መጣጥፎችም ከልዩ ልዩ ወታደራዊና ሲቪል ተዋናዮችና የታሪክ ጸሐፊዎችም ተጽፈው አንብበናል፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለምን ውድቀት ገጠመው? ለምንስ ግንባሮቹ (ሻዕቢያ፣ ወያኔ፣ ወዘተ) ድል ሊያደርጉ ቻሉ ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በርካታ ወታደራዊ፣ ፓለቲካዊና ሌሎች ምክንያቶችም ይቀርባሉ፡፡ በዋነኝነት የውድቀቶቹ ምንጮች ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንደነበሩ ይህን በጥልቀት ያጠኑና የጻፉ ምሁራዊና በአመዛኙ ሁለንተናዊ፣ እንዲሁም ሚዛናዊ ሊባሉ የሚችሉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በዶ/ር ገብሩ ታረቀ በእንግሊዘኛ የተጻፈውን “Ethiopian Revolution: War and Revolution in the Horn of Africa” በዋነኛ ምሳሌነት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ሌሎችም በሀገሪቱ ስለነበረው የፓለቲካዊ ሁኔታና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ስለተደረጉት ጦርነቶች ተጻፉት ሌሎች መጻፎችም ይህንኑ እውነታ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ታላቁ ቻይናዊ የስትራቴጂ ፈላስፋ ሰን ዙ እንደሚለው ፡ መሪና ተመሪ፣ መሪዎችና ሕዝብ፣ ሆድና ጀርባ ከሆኑ ጦርነትን ማሸነፍ አይቻልም፡፡ በፍትህ ያልተመራ ህዝብና ሰራዊት በጦርነቶች ወቅት አሸናፊ ለመሆን በጣም አዳጋች መሆኑን ከሰን ዙ በኋላ ላለፉት 2000 ዓመታት የተደረጉ የጦርነት ውጤቶች የሰን ዙን ዘመን የማይሽረው ስትራቴጂኪያዊ አስተምሮና አስተውሎ ያረጋግጣሉ፡፡ ክላሽዊትዝ እንዳስቀመጠው ደግሞ “ጦርነት የፓለቲካ/የፓሊሲ ቅጥያ” ነውና፣ ፓሊሲዎችና የፓለቲካ ስትሬቴጂዎች መሰረታዊ ችግሮች ካሉዋቸው የእዛ ምንዝር የሆኑ የፓለቲካ አመራር ከሚያወጡዋቸው ፓሊሲዎች የሚመነጩ የወታደራዊ ስትራቴጂዎችም እንዲሁ ወደ ውድቀትና ሽንፈት ከመሄድ ያዘገዩ ይሆን እንጂ የፓለቲካ ስርዓቱን ከሽንፈት፣ ከዚያም ከውድቀት ሊያድኑ አይችሉም፡፡ በብዙ ብዙ የታክቲካል፣ የኦፕሬሽናል ቲትር ዘመቻዎችና አውደ ውጊያዎች የኢትዮጵያ ሰራዊት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ይህ ነው በማይባል ጀግንነት እየተዋጋ ነበር፣ በርካታዎቹ ላይ ድል ያደረገ ቢሆንም በመጨረሻም በስትራቴጂ ደረጃ በመሸነፉ ፣ ጦርነቱ በሽንፈት የተጠናቀቀው ከዚሁ ሃቅ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡ የጦርነቱ ሽንፈት የፓለቲካው መክሸፍና የፓሊሲ ውድቀቶች ያመጣው መዘዝ በዋነኝነት ወይንም ዐቢይ መንስኤ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በሀገራችን የተካሄዱ ጦርነቶች ያስከተሉት ውድቀት ከፓለቲካ/በፓሊሲ ጋር የተያያዙ መሰረታዊ ችግሮች ስለነበሩ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ ነው ከፍተኛዎቹና ኢትዮጵያ ከ30 አመታት በላይ ብዙ ሃብቷን ያፈሰሰችባቸው፣ በዋና ዋናዎቹ የአለም የጦር አካዳሚዎች፣ የስታፍ ኮማንድ (የአዛዥነት) ማሰልጠኛ ማዕከሎች፣ በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በሩሲያ፣ በእስራኤል፣ በሕንድና በሌሎችም ሀገሮች የተማሩና በደረሱበት ልቀትም የሀገሪቱንም ስም ያስጠሩ (ከብዙ ሀገሮች ከመጡና ከፈረንጆችም መካከል ከእንግሊዙ ሳንድረስት የጦር አካዳሚ የላቀ ውጤት በማምጣታቸው ከእንግሊዝ ንግስት ልዩ ሽልማት የተቀበሉት ብ/ጄነራል ተስፋዬ ትርፌና ሌሎችም በርካቶች በምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ) ፣ ብዙ ልምድና ተሞክሮ የነበራቸው አይተኬ የጦር

ኤርትራ በምመላለስበት ጊዜም የኤርትራ ግንባር ተዋጊና አዋጊዎች ለአንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ጀነራሎች ከፍተኛ ግምትና ክብር እንደነበራቸው ለማወቅ ችያለሁ

ጀኔራሎችን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ለማድረግ የገፋፋቸው ዋነኛ ምክነትያቶች በሀገሪቱ የነበረው የፓለቲካ ሁኔታ፣ አመራር፣ ከዚህ ጋር በቀጥታ የተገናኛው የሰሜኑ የተራዘመ ጦርነት እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ በዊኪ ሊክ (wiki leak) ከአሜሪካ ኤምባሲ ወደ አሜሪካው የውጭ ጉዳይ ጽ/ቤት የተላከ አንድ ኬብል፣ በ1970ቹ በሶማሌ ጦርነት ጊዜ በየግንባሩ የተመደቡትን የዕዝ አዛዦች ይዘረዝርና፣ ስለ ሜ/ጄነራል ዴምሴ ቡልቶ (በወቅቱ ኮ/ል) የሚከተለውን አስቀምጦ ነበር፡፡ MAAG (የአሜሪካ የወታደራዊ ተራድኦ ሚሽን) ኮ/ል ደምሴን በኢትዮጵያ ሠራዊት ተዋረድ የመጨረሻውን ከፍተኛ ደረጃ ኃላፊነት ለመድረስ እምቅ አቅም ያላቸው ነበሩ ብሎ እንደገመገመ ማግ ያሰፈረውን ማስታወሻ ዋቢ አድርጎ በወቅቱ ኤምባሲው ወደ አሜሪካው የውጭ ጉዳይ መ/ቤት በላከው ኬብል አካቶት ነበር፡፡ “…COMMANDER OF SECOND ARMY DIVISION - COL. DEMISSIE BULTO. (MOST RECENT EMBASSY BIO SHOWS HIM AS DIRECTOR OF TRAINING AT HARAR MILITARY ACADEMY IN 1973. DEMISSIE IS HIGHLY DECORATED AIRBORNE OFFICER, WHOM MAAG IDENTIFIED IN 1968 AS HAVING POTENTIAL TO RISE TO VERY TOP OF ETHIOPIAN ARMY….)

ጦርነቶች ላይ መሸነፍ የበርካታ ምክነያቶች ድምር ነው፡፡ ለጦርነቶች ሽንፈትና ውድቀት በምክነያትነት፣ በዋነኝነትም ከሚጠቀሱት መካከል የፓለቲካና የፓሊሲ መሰረታዊ ችግሮችና የሚፈጥሯቸው ልዩ ልዩ ደንቃራዎች ናቸው፡፡ሌሎች መንስኤዎችም እንዳሉ እንደተጠበቀ ሆና፡፡ ያለፈውን ጦርነት ለመዋጋት በሞሞከር(በወታደራዊ ስትቴጂና እቅድ ጀምሮ ይህን ለማስፈጸም አዛዦች የሚጠቀሙባቸው ታክቲኮች)፣ የሚመጣውን/ሊሆን የሚችሉትን ምናልባቶች በአጋባቡ የቢሆንስ ሴናሪዮ/scenario አለማጤን/አስቀድሞ ለመገመት፣ በእቅድ ውስጥ ለማካተት አለመቻል፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር አንድ የጦር ኃይልና መሪዎቹ ራሳቸውን መለወጥ፣ ማዋሃድ አለመቻል፣ ልዩ ልዩ ስህተቶች ሲዳመሩ የሚፈጥሩት አጠቃላይ ድምር(aggregate failure) የመሳሰሉና ሌሎችም በበርካታ ጸሐፊዎች የተገለጹ ዝርዝር ምክነያቶች ለውድቀቱ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ገልጸዋል፡፡

ወታደራዊ ሽንፈቶችና ውድቀቶች ከጀግንነት፣ በወኔ ከመዋጋት፣ ከወታደራዊ ዲሲፕሊን እጥረት፣ ከወታደራዊ ሳይንስ ክህሎትና ብቃት ማነስ ጋር ብቻ የተያያዙ እንዳልሆኑም፤ በታሪክ ውስጥ ለከፍተኛ ውድቀትና ሽንፈት የተዳረጉ ለምሳሌ የአሜሪካ ጦር 8ኛው ሰራዊት በኮሪያና በቻይና የጦር ሃይሎች ፣ የእንግሊዝ ጦር በጀርመኖች በጋሊፓሊ በአንደኛው የአለም ጦርነት ጊዜ፣ የእስራኤል ጦር በሱዝ ካናልና በጎላን ተራሮች በአረብ ሀገሮች የጦር ሀይሎች፣ የፈረንሳይ ጦር ካናዚ ጀርመን ጋር በተደረገው ጦርነት የደረሰባቸው ሽንፈቶችና ውድቀቶች በሚመለከት “Military Misfortunes: The Anatomy of Faiure in War” የጻፈው የጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርስቲ የስትራቴጂ ባለሙያና ፣ ምሁር ኤልየት ኮሀንና ሌሎችም በስፋት የጻፉበት ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ ዋና ጭብጡ ከዘመናዊ የጦር አደረጃጀት ዋና ኢንጂነርና የጦርነት ጂየነስ ከሚባለው ከናፖሊዮን ሽንፈትና ውድቀት ጀምሮ እስከ አሁን ዘመን ድረስ በከፍተኛ ጀግንነት መዋጋት፣ ከፍተኛ ወታደራዊ ትህምርትና ልምድ፣ የስትሬቴጂ ክህሎትና እውቀት እንዲሁም ዘመናዊ መሳሪያዎች መታጠቅ ብቻቸውን የጦር ሃይሎች ከሽንፈትና ከውድቀት ሊያድኑዋቸው እንደማይችሉ ነው፡፡ የጦር ሃይሎች ለውቅደትና ለሽንፈት የሚጋለጡባቸው ምክነያቶች በርካታና ውስብስብ መሆናችውን ለማመልከት ነው፡፡

ከላይ የእነዚህን አራት የጦር ጀነራሎች፤ እንዲሁም የጀ/ል ተስፋዬ ሀብተማርያምንም የመጡበትን የብሔር/የዘውግ ማህበረስብ የገለጽኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ ከብሔር በላይ ለሀገራዊ ማንነት፣ ለኢትዮጵያዊነት ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸው፣ ክብራቸውን የሚጠብቁ፣ በብቃታቸውና በክህሎቶቻቸው ያስተማሩዋቸውና ያሰለጠኑዋቸው ጭምር ለመደነቅ የተገደዱባቸው የጦር መሪዎች ስለነበሩ ነው፡፡ ከሁሉም ብሔር/ቋንቋ ማህበረሰቦች የተወጣጣው የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ዋነኛ መለያውም ኢትዮጵያዊነት ነው የሚባለውም በዚሁ ሐቅ ምክንያት ጭምር ነው፡፡ ያ ህበረ ቀለም የነበረውና እንደ ኢትዮጵያዊ ታንጾ እንደኢትዮጵያዊ በኮሪያ፣ በኮንጎ ፣ በሶማሊያ ወረራ ወቅትና በልዩ ልዩ ግንባሮች በጀግነነት ያገለገለና ይህ ነው የማይባል መስዋእተነት የከፈለ የኢትዮጵያ ሰራዊት በስተኂላ ላይ በአሳዛኝ ሁኔታ ከውድቀት የተዳረገው ጀግንነት ስላነሰው፣ የላቀ ችሎታና ብቃት ያላቸው ወታደራዊ አዛዦች ስላልነበሩት አልነበረም፡፡

እብሮ አደግ ጓደኛዬና ወንድሜ ደረጀ ደምሴ ቡልቶ የ “አባቴ ያችን ሰዓት” ጸሐፊ፣ የ30 አመቱን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ዝክረ አመት በሚመለከት የጻፈው አንዱ ማዕከላዊ መልዕክት የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከብሔር በላይ በኢትዮጵያዊነት የተገነባ፣ ለዚሁም ሕይወቱን የገበረ፣ ደም፣ አጥንቱን የከሰከሰ፣ በየግንባሩ- በደቡብና በምስራቅ ከሶማሌ ወራሪ ሰራዊት ጋር፣ በሰሜን ከአማጽያን ግንባሮች ጋር ብዙ ብዙ መስዋዕትነት የከፈለ፣ ይህ ነው የማይባል ስቃይና መከራ ያለፈ ሠራዊት ነበር፡፡ ከታላላቆቹ በጣም የተከበሩና በችሎታቸውና በብቃታቸው ከፍተኛ ክብርና ዝናን ካተረፉት የኢትዮጵያ ጀኔራሎች አንዱ የሆኑት የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ዋና አዛዥ ሜ/ጀ ደምሴ ሶስተኛ የወንድ ልጃቸው የሆነው ደረጀ አብሯቸው በተጓዘበት የመስሃሊት ውጊያ፣ ኤርትራ የነበረውን የወቅቱን ሁኔታ ይገልጽና አባቱ ለክፍለ ጦሩ አዛዥ ለጀ/ል በሃይሉ ክንዴ በወቅቱ ኮ/ል በኦሮምኛ ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ እንደነበር ያወሳል፡፡ ለአሁኑ ዘመን ሁኔታውም ጥሩ አስተምህሮ ያስተላልፋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

# አንደበት




"ለእኛ አገር የሚያዋጣው የዜግነት ፖለቲካ ነው ስንል በዚህ ምክንያት ድምጽ እናገኛለን በሚል ስሌት አይደለም፡፡ በመሰረታዊነት ፖለቲካን ከዘር ወይም ከሌላ ማንነት ጋር ባያያዝከው ቁጥር ግጭት ከመፍጠር ውጪ፣ የተረጋጋ ማኅበረሰብ መፍጠር አትችልም፡ ፡ ፖለቲካው ከብያኔው ጀምሮ የመንግሥት ጉዳይ ከሆነ መንግሥት ደግሞ የሚመለከተው ሁሉንም ሰው ነው፡፡ አንዱን ለይቶ ለአንዱ ብቻ መንግሥት ሊሆን አይችልም፡፡ መንግሥት ሕግ ሲያወጣ ለኦሮሞ ለብቻው፣ ለትግሬ ለብቻው፣ ለአማራው ለብቻ ብሎ አይደለም፡፡ የወጣ ሕግ ሁላችንንም በአገሪቱ ውስጥ የምኖር ዜጎችን መከተል ያለብን ነው፡፡"

ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ /የኢዜማ መሪ/
አዲስ ማለዳ ጋዜጣ ግንቦት 10 ቀን 2011 ዓ.ም




"እንግዲህ የተጀመሩ በጎ ጅምሮች አሉ፣ በጎና ቀና ሀሳቦችን እየሰማን ነው፡፡ በጎ ሀሳብ ያላቸው ሰዎችን እያየንም ነው፤ ይሄ በጎ ሀሳብ ታዲያ በራሱ መሬት ላይ አይወርድም፣ በርትቶ በመስራት መሬ እንዲረግጥና እቅዱ ተግባር ላይ እንዲውል ያስፈልጋል፡፡ በዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ውስጥ ያለው የለውጥ ሀሳብ በእያንዳንዱ ካድሬ ልብ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ ይሄ እስከሌለ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል አሁንም እኛ ይህንን ያህል ፓርቲና ስብስቦች ተዋህደን አንድ ሆነናል፡፡ ብዙ የተለያየ አስተሳሰብና ልዩነት በሌለበት፣ በየቦታው ተበታትኖ ከመስራት አንድ ላይ ሆነው እንዲታገሉ፣ በሰው ሀይልም፣ በእውቀትም እንዲደራጁ ምኞቴ ነው፡፡ ህዝቡም በትዕግስትና በእርጋታ በሰላማዊ መንገድ መታገል አለበት እላለሁ፡፡

አቶ አንዱአለም አራጌ /የኢዜማ ምክትል መሪ/
ሸገር ታይምስ መጽሔት ግንቦት 10 ቀን 2011 ዓ.ም



"በእኔ እምነት፣ ሲጀመርም ቢሆን በኢትዮጵያ ታሪክ፣ "የዜግነት ፖለቲካ" የሚባል በንድፈ ሐሳብ እንጂ፤ በተግባር ኖሮ አያውቅም፡፡ እርግጥ ከአንድ ዓመት ወዲህ ጭላንጭሉ እየታየ ነው፡፡ እየጎላ ከመጣ እውን ሊኾን ይችላል የሚል ተስፋ አለ፡፡ የዜግነት ፖለቲካ በንድፈ ሐሳብ ሳይኾን በእውን የሚኖረው እያንዳንዱ ግለሰብ ሕዝብ ባፀደቀው ሕገ መንግስት ሲረጋገጥና ሕዝቡ በእውን የሥልጣኑና የጉዳዩ ባለቤት ሲሆን ነው፡፡ እዚህ ላይ የመረካከብ ወይም የመተካካት ነገር አይታየኝም፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ሲጀመርም አልነገረበም፡፡ የብሔር ፖለቲካ (እኔ የጎሣ ፖለቲካ ነው የምለው) ግን ቢያንስ ከዛሬ ሀያ ሰባት ዓመት ጀምሮ ሀገሪቱን ቀስፎ እንደያዘ ነው፡፡ በጎሣ ፖለቲካ የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑና የጉዳዩ ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ ሁኔታ በሀገራችን እውነተኛ ዲሞክራሲም ሊኖር አይችልም፡፡"

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ቦሌ ታይምስ ጋዜጣ ግንቦት 10 ቀን 2011 ዓ.ም




"ድርጅታችን በይፋ ስላልፈረሰ፤ እንዲፈርስም ስለማንፈልግ አዲስ አበበ ስንጠራ እንሄዳለን፡፡ አዲስ አበባ ያለው መንግስት እኮ የሁላችንም ነው፡፡ ለእከሌ ብለህ የምትተወው አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችንን እከሌ የሚባለውን ቡድን አኩርፈን የምንተዋት ነገር አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስብሰባ ስትሄድ እነዚህ ሰዎች ሊደመሩ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ሊኖር ይችላል፡ ፡ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም፡፡ በገባኝ ልክ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሚሰሯቸውን መልካም መልካም ነገሮችን መደገፍ ኢትዮጵያን መደገፍ ነው፡፡ አጥፊ መንገዶች ካሏቸው መተቸት ኢትዮጵያን መደገፍ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሕወሓት በመርህ ነው የሚመራው፤ የሚገመደው፤ የክልሉ ባለስልጣን እከሌ እከሌ በሚል አይደለም፤ ፀረ ለውጥ ካየን እኛ እዚሁ እንዋጋለን፡፡"

አቶ ጌታቸው ረዳ /የሕወሓትና የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል/
ዘመን መጽሔት ግንቦት 2011 ዓ.ም

በቆዳው ዘርፍ ውጭ ድረስ ልከን በርካታ የቆዳ ቴክኒሻኖችን አሠልጥነን ነበር፡፡ ዘርፉ ልክ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ነበር፡፡ ኃላፊዎቹ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሙያዎቹ፣ ቴክኒሻኖቹ፣ የሽያጭ ሠራተኞቹ የሠለጠኑ ኢትዮጵያውያን ነበሩ፡፡ እንግሊዝ፣ ህንድ፣ ጀርመን ልከን ያሠለጠናቸው ቴክኖሎጂስቶች ነበሩን፡፡ የቆዳ ሥራ ከትምህርትም በላይ ልምድና ስሜት ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ያሠለጠናቸውና ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች ግን ተበተኑ፡፡ ውጭ የሄዱና በተለያየ የሥራ መስክ የተሰማሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ በነጋሪት ጋዜጣ የወጣው የውጭ ፋብሪካዎች በቆዳ ውጤቶችና ቀለም በሚቀለም ቆዳ ምርት ብቻ መሥራት እንደሚፈቀድላቸው ተደንግጎ ነው፡፡ ይህ ሕግ ተረግጦ ነው የእንግሊዝ፣ የቻይና፣ የህንድ ፋብሪካዎች የገቡት፡፡ አብዛኞቹም ጥሬ ቆዳ መሰብሰብ ላይ አተኩረው ነበር፡፡ ምንግዜም ቢሆን እንደ አገርህ የሚሆን ሰው አታገኝም፡፡



አቶ አምዴ አካለ ወርቅ /የቆዳ ኢንዱስትሪ ባለሙ/
ሪፖርተር ጋዜጣ ግንቦት 11 ቀን 2011 ዓ.ም



"ከ40 ዓመት በላይ የዘለለው የኃላፊነት ቆይታዬ ሲነሣ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ አለ… የመጀመሪያዎቹ 17 ዓመታት የቡና ገበያ ኮርፖሬሽን ኃላፊ ነበርኩ፡፡ ነገር ግን ክልቡን በቀጥታ የሚመሩ ሌሎች የስራ አስኪያጅ ኮሚቴዎች ነበሩና የኔ አመራር በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ነበር፡፡ ካጠፉ ግን የመምከር መብት አለኝ፣ መልበሻ ቤት ሄጄ ተጫዋቾቹን ማናገር ሁሉ እችል ነበር… ከዚያ ቀጥሎ ከስልጣን ከተባረርን በኋላ ለአመታት በአካባቢው ብኖርም 8 አመት ያህል አቶ አብዱራዛቅ መርቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ እነ ኤሊያስ መርተውታል፡፡ ይህ በመሆኑ 43 ዓመቱ ተጠቅልሎ ለኔ መሰጠቱ ተገቢ አይመስለኝም….. ነገር ግን በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ ከክለቡ ጋር መኖሬ እውነት ነው፡፡

መቶ አለቃ ፍቃዱ ማሞ /የኢትዮጵያ ቡና የቦርድ ሰብሳቢ/
ሀትሪክ ጋዜጣ ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም

# ለዛ

## አባባል

የምትወደውን ሙያ
ከመረጥክ ህይወትህን
በሙሉ አንዲት ቀን
እንኳን የሰራህ ሳይመስልህ
ትኖራለህ፡፡

አንድ መቶ ጊዜ ወደቅሁ
ሳይሆን ወደ ውድቀት
የሚመሩ 100 መንገዶችን
አወቅሁ ነው ማለት
ያለብን፡፡

ስኬት ማለት ጉጉታችን
ሳይበርድ ካንዱ ውድቀት
ወደ ሌላው መሸጋገር ነው፡፡

መሸነፍ ጊዜያዊ ሲሆን
ቋሚና ዘላለማዊ
የሚያደርገው እጅ መስጠቱ
ነው፡፡

## ለጠቅላላ እውቀት

- ቴሌቪዥን ለልጆች እንደ ተፈጥሯዊ ሕመም ማስታገሻ ያገለግላል፡፡

- ሙሉ ጨረቃ ከግማሽ ጨረቃ በሁለት እጥፍ ብቻ ሳይሆን በ9 እጥፍ ትደምቃለች፡፡

- 1961 ተገልብጦ ሲነበብ ያንኑ 1961 ይሰጣል፡፡ በዚህ ዓመት ምህረት ከተወለዱት ታዋቂ ሰዎች ውስጥ አንዱ ባራክ ኦባማ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ እንደዚህ ተገልብጦ ሲነበብ መልሶ ራሱን የሚሰጥ ዓመተ ምህረት 6009 ብቻ ነው፡፡

- ከስምንቱ ፕላኔት ተለይታ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የምትሽከረከር ብቸኛዋ ፕላኔት ቬኑስ ናት፡፡ በቬኑስ ፀሐይ በምዕራብ ወጥታ በምስራቅ ትጠልቃለች፡፡

- በብራዚል ውስጥ ያሉት አንዳንድ ሰፋፊ አውራ ጎዳናዎች ላይ 160 መኪናዎች በአንድነት ጎን ለጎን ሆነው ማለፍ ይችላሉ፡፡

- ከሕዋ የሶላር ሲስተም ክብደት ውስጥ 99.86% ክብደት የያዘችው አንድዬዋ ፀኃይ ስትሆን ዘጠኙ ፕላኔቶች በአንድ ላይ ተጠቃለው የሚጡት ክብደት የፀሐይን 0.14 ብቻ ነው፡፡

# “ሕወሓትና ሻዕቢያን ከማጥፋት፤ ወደ ዕርቅ መውሰዱ ሰላምን ያመጣል”



## አቶ አብርሃም ገ/ሊባኖስ

አብርሃም ገ/ሊባኖስ ከወንድሙ ጋር ባቋቋሙት ሴሌብሬቲ ኤቨንትስ የተለያዩ ሀገራዊ ስራዎችን እያካሄደ ይገኛል፡ ፡ ኤርትራ ተወልዶ ያደገው አብርሃም ለበርካታ ዓመታት ተቋርጦ የቆየውን የኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት ለማደስ ላለፉት አራት ዓመታት ከሁለቱም ሀገራት ምሁራንና ያገባኛል ከሚሉ ሀገር ወዳዶች ጋር በእጅጉ ሲደክም ቆይቷል፡፡ a ከወራት በፊት የተካሄደው የሀገራቱ ዕርቅ ከ20 ዓመት በኋላ አዲስ መንገድ ቢከፍትም ፤ ዕርቁ ሙሉ እንዳልሆነና ዋናው የፀቡ መንስኤ የሆኑት ሕወሓትና ሻዕቢያ እንደ ድርጅት ሰላም ባለማውረዳቸው አሁንም ነገሮች በትክክለኛው መንገድ ላይ እየተጓዙ ባለመሆናቸው ድርጅቶቹ ወደ ዕርቅ እንዲመጡ ጥረት መጀመሩን የሚገልፀው አቶ አብርሃም ገ/ሊባኖስን በጉዳዩ ዙሪያ የግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ አነጋግረውታል፡፡

**ግዮን፡- ሕወሓትና ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራን (ሻዕቢያ) ለማስታረቅ፤ በቅርቡ አዲስ ፕሮጀክት ጀምሯችኋል፡፡ ለመሆኑ መነሻችሁ ምንድን ነው?**

አብርሃም፡- ሴሌብሬቲ ኤቨንትስ እንደሚታወቀው ቀደም ሲል በኢትዮ- ኤርትራ ጉዳይ ላይ፣ ስልጣን ላይ የነበሩት መንግስታት ወደ እርቅ እንዲመጡ ግፊት ሲያደርግ የነበረ ድርጅት ነው፡፡ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ከሶስትና አራት ዓመት ልፋት በኋላ ይሄ ነገር ፍሬ አፍርቶ፣ የሁለቱም ሀገር መንግስታት ያንን አጥር ሰብረውት አሁን የዕርቅ ማዕድ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው፣ ለጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድና ለፕ/ት ኢሳይያስ አፈወርቂ ምስጋናችንን በዚህ አጋጣሚ እናቀርባለን፡፡

ይህ ስምምነት ከተፈጠረ በኋላ፤ ሁለት ወራት ኤርትራ ላይ፣ ለተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ትግራይ ላይ በመቆየት የተለያዩ ጥናቶችን አድርገናል፡፡ ባገኘነው የጥናት ውጤት መሰረት የኢትዮ ኤርትራ ግጭትና ልዩነት ለዚህን ያህልዓመታት ያቆየው፤ የትግራዩ ሕወሓትና የሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ቅራኔና ፀብ ዋነኛው ችግር በመሆኑ ነው፡፡

ሕወሓትና ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ምን ምንድን ናቸው? ከሚለው ይነሳል፡፡ ቀጥሎ ያለመግባባታቸው ምክንያትስ ምንድን ነው? ላለመግባባታቸው ምክንያት የሆነ የውጭ ጣልቃ ገብነት አለወይ? ጊዜና ወቅቱ አሁን ለዕርቁ ምቹ ነወይ? ይሄንንስ ዕርቅ ኃላፊነት መውሰድ ያለበት ማነው? ከዚህ ዕርቅ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግስታት፣ ብሎም የትግራይ የኤርትራ ሕዝብ ምን ጥቅም ያገኛል? ለሚሉና ተጨማሪ ጥያቄዎች በቂ መልስ ለመስጠት ባደረግነው ጥረት ነው እነዚህን ወሳኝ ጉዳዮች ስናጠና የቆየነው፡፡

ሕወሓትና ሻዕቢያ ወደ ዕርቅ ሲመጡ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግስት ፖሊሲዎቻቸውን ወደ ታች ወርደው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ዕንቅፋት አይገጥማቸውም ከሁለቱም ድርጅት፡፡ ቀጥሎ በድንበሩ ግጭት ምክንያት የተነሳው ቅራኔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዕልባት እንዲያገኝ ነው፡፡ እዛው ላይ ምክንያቶች እየተጠመጠሙ እየከረሙ ስለሆነ፤ አሁንም ያ ነገር ድጋሚ እየተነሳ ባለበት ሁኔታ ነው ያለነው፤ ይህ ቢሆንም የሁለቱ ድርጅቶች መታረቅ ግን ችግሩን ይፈታዋል ብለን እናምናለን፡፡ ይህን እርቅ ደግሞ በድንበር አካባቢ ያለውን ማህበረሰብ እንደልቡ ሆኖ እንዲያርስ፣ እንዲነግድ፣ የልፋቱን ውጤት እንዲያጣጥም ያስችለዋል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የሕወሓትና የሻዕቢያ ዕርቅ፣ የቀይ ባህር ፖለቲካ እንዲረግብም የራሱ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያና ኤርትራ ከወራት በፊት የዕርቅ ስምምነት ፈፅመዋል፡፡በትግራይ ክልል ደረጃ ያለን አንድ ፓርቲ ኤርትራን ከሚያስተዳድር ድርጅት ጋር ለማስታረቅ መሞከሩ ከህግ አግባብ ተቀባይነት ይኖረዋል?**

አብርሃም፡- የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግስት ሂደቱን ጀምረውታል፤ ወደ ፊትም እየሄዱ ነው፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት ግን የግጭቱ መንስኤ በትግራይ ክልልና በኤርትራ አዋሳኝ ቦታ ላይ ስለሚገኝ፣ ሁለቱ የሚመሩት ድርጅቶች ይህ ህዝብ ሰላም እንዲያገኝ መግባባት ስላለባቸው ነው ዕርቁ ያስፈለገው፡፡ ቅራኔው ያለበት ቦታ ላይ፣ መፍትሔ የሚገኝበት ቦታ ላይ፣ የትግራይ ክልል መንግስት የሚያስተዳድረው ቦታ አለ፣ የፌደራል መንግስቱ የሚመራው ማለት ነው፡ ፡ ቀጥሎ ደግሞ በኤርትራ በኩል የሚመራው አካል ደግሞ አለ፤ ስለዚህ የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግስታት ግንኙነት ሙሉና አስተማማኝ እንዲሆን፣ ሁለቱ ድርጅቶች ወደ ዕርቅ መምጣት አለባቸው፡፡

በቅርብ ከተደረገው ስምምነት በኋላ መንግስታቱ እየተነጋገሩበት ነው ተብሎ ከሚታመነው ጉዳዮች አንዱ የአልጀርሱ ስምምነት ነው፡፡ የኤርትራው መንግስት እዚህ ላይ “በቅርብና በአፋጣኝ መፍትሄ እንዲበጅልኝ እፈልጋለሁ፣ በመሬቱ ጉዳይ” እያለ ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ የፌደራል መንግስቱ ዕውን እንዲያደርግ የሚያስችል ሁኔታ በትግራይ በኩል አለ ወይ? የሚለው ጉዳይ አሳሳቢ ነው፡፡ ሕወሓት ይሄንን ለማድረግ መጀመሪያ መሬቱ ላይ ካለው ሕዝብ ጋር መወያየት አለበት፣ ቀጥሎ ደግሞ ከኤርትራ ጋር ደግሞ በግልፅነት መወያየት ይኖርበታል፡፡

**ግዮን፡- ጉዳዩ ወደ አንድ ክልል መውረዱ ዕርቁን አያሳንሰውም? ያለውን ችግር ለመፍታት እንደ ሀገር የኢትዮጵያ መንግስት መጠየቅና መደራደር ሲገባው ሕወሓት እንደ አዲስ ከሻዕቢያ ጋር ዕርቅ ያድርግ ማለቱ ተገቢ ነው? ከኤርትራ ጋር እኮ ከድንበር ባሻገር የወደብ አጠቃቀም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፤ ይሄ ደግሞ የሕወሓት ኃላፊነት አይደለም፡፡**

አብርሃም፡- በነገራችን ላይ ማንሳታችን ካልቀረ ወደብ የህልውናችን ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ምስራቅ አፍሪካን፣ የቀረውን ዓለም ፖለቲካሊ እንዳንሸነፍ የሚረዳን፣ ዲፕሎማሲካሊ፣ ተፅዕኖ እንድንፈጥር የሚያደርገን ነው፡፡ ስለዚህ እሱ የህልውናችን ጉዳይ ነው ብለን እናስባለን፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን አሁን እያልኩ ያለሁት የትግራይ ክልል ስራውን ይስራው አይደለም፡፡ በትክክል ሕወሓት የሚባለው ድርጅት እዚህ ጉዳይ ላይ የራሱን አንኳር ሚና ስለሚጫወት፣ በተመሳሳይ ኤርትራን በመንግስትነት የሚያስተዳድረው ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ስለአለ፣ የእነሱ አለመግባባት ነው መጀመሪያውኑ ወደእዚህ ጦርነት ውስጥ የከተተን፡፡ እዚህ ላይ በግልፅ ከተግባባን፣ የፀቡ መነሻዎች የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ወደ ዕርቅ ይምጡ እያልን ነው ያለነው፡፡

**ግዮን፡- ስለዚህ እስካሁን ድረስ ዕርቅ የለም፣ አልተከናወነም እያልክ ነው?**

አብርሃም፡- ዕርቅ የለም፡፡ በነገራችን ላይ የእዚህን ወር ስታተስ ነው እየሰጠሁህ ያለሁት፡፡ አሁን የኤርትራ መንግስት በድንበሩ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶኛልና መሬቱን አስረክቡ እያለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ይሄንን ውሳኔ ለመወሰን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ማውራት አለበት፡፡ ያንን ቦታ የሚሸፍንና የሚያስተዳድር ድርጅት ደግሞ በኢህአዴግ መሀል አለ፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ በእነሱ መሀል ያለው ቅራኔ መፈታት አለበት፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የሚሰራው ስራ፣ በኤርትራ ጉዳይ ማለት ነው፤ ትልቅ ስራ ነው፡፡ አንዲትም አረፍተ ነገር፣ አንዲትም አንኳር ነገር ግን ብትሆን የሕወሓትና የሻዕቢያ አለመታረቅ የችግሩን ዕንቅፋት ይጨምረዋል እያልኩ ነው ያለሁት፡፡ በትክክል ነገሮች እንዲሳኩ ከተፈለገ አስቀድሞ የሁለቱን ድርጅቶች ቅራኔ ማስወገድ ይኖርብናል፡፡

**ግዮን፡- አንተ አሁን ከምትለው አንፃር ዕርቁ ጥሩ ስሜት ሲኖረው ይችላል፤ ግን በአንፃሩ ሕወሓትና ሻዕቢያ ስልጣን ላይ ቢቆዩ ኖሮ የኢትዮ ኤርትራ ችግር ከ20 ዓመትም በዘለለ አንዳቸው እስኪወገዱ ድረሰ አይፈታም ነበር፡ “ሕወሓት አልታረቀም” በሚል ሀገራዊ ዕርቅና ስምምነቱን ወደ ድርጅት ማውረዱ ምን ይጠቅማል? ባይታረቅስ?**

አብርሃም፡- እኔ በግሌ ከዕርቅ ማትረፍ ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን ላነሳኸው ጥያቄ ይሄንን ፕሮጀክት ተንተርሶ ሶስት ዓይነት አስተያየቶች እየተሰጡ ነው፡፡ አንድ፡- ሁለቱም (ሕወሓትና ሻዕቢያ) እንዲጠፉ የሚፈልግ ኃይል አለ፣ ሁለቱም አያስፈልጉም በሚል፡፡ ሌላ ደግሞ ሁለቱም ሳይሆኑ አንደኛው ቢጠፋ መፍትሄ ሊገኝ ይችላል የሚል ነው፡፡ የእኛ ፕሮጀክት ደግሞ ዕርቁን ይደግፋል፡፡ መጠፋፋቱ ዋጋ ስለሚያስከፍል አንፈልገውም፡፡

እኔ በሕወሓትና ሻዕቢያ ጉዳይ ላይ አንድ ጥያቄ አለኝ፡፡ እነዚህን ሁለት ድርጅቶች አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ማጥፋት ይቻላል ወይ?

**ግዮን፡- እኛ አሁን ይጥፉ እያልን አይደለም፡፡ ግን ሁለት ጊዜ እርቅ የለምና የመጀመሪያው ሀገራዊ ስምምነት ይበቃል፣ ይልቅ የሁለቱን ሀገር ሕዝቦች በተለያየ መንገድ ለማቀራረብ ብትሞክሩ አይሻልም ወይ?** ►

አብርሃም፦ የእኛን ጉዳይ እንድትወስደው የምፈልገው ለምሳሌ የኦሮምና የሶማሌ ክልል እርቅ በሁለት ክልሎች መሀል የተደረገ ዕርቅ ነው። ለፌዴራል መንግስት ይጠቅመዋል እንጂ አይጎዳውም። የትግራይ ክልልን የሚያስተዳድረው ተወደደም ተጠላም ሕወሓት አለ፤ በኤርትራ በኩል ደግሞ ተወደደም ተጠላም ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ አለ። የእነሱ ዕርቅ ለኢትዮጵያ መንግስትና ለኤርትራ መንግስት ጠቃሚ ነው እያልን ነው ያለነው፤ በመታረቃቸው የምንጠቀመው ይበልጣል ከመጣላታቸው ይልቅ።

አሁን ከያዝነው ፕሮጀክት አንፃር ነገሮችን ፖለቲካል ማየት ስለማልፈልግ ነው፤ ግን የሁለቱ ግጭቶች ከምንግርህ በላይ በኢትዮጵያ ምድርም፣ በኤርትራም ምድር እየተስተናገዱ ነው። ስለዚህ ከዕርቁ አትራፊ እንሆናለን፤ ሌላው የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ አንድ አካል ከሆነ የትግራይ ሕዝብ ከኤርትራ አቻው ጋር ሪሊፍ ማግኘቱ ለኢትዮጵያ ጥቅም አለው እያልን ነው። የትግራይ ሕዝብ የሚፈልገውን ሰላምና ዕርቅ ካገኘ ክልሉን ወደሚፈለገው ዴሞክራት ክልል ሊቀይረው ይችላል።

ዕርቁ ከተካሄደ እኮ ዓመት ሊያስቆጥር ነው፤ ግን በዚህ ውስጥ የታየ አንድም ሕጋዊ የሆነ የወረቀት ልውውጥ አላየንም ፣ኢትዮጵያ ይሄንን ጠየቀች፣ ኤርትራ ይሄንን መልስ ሰጠች እየተባለ ግልፅ ሆኖ የመጣ ነገር አላየንም። የውዝግቡ ቦታ አሁንም በሁለቱ ሀገሮች ወታደሮች እየተጠበቀ ነው ያለው። ወታደር እየጠበቀው ባለው ክልል ላይ ደግሞ ኢንቬስተሮች ይመጣሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። ኢንቬስተር ከሌለ፣ ስራ ከሌለ መሰደዱ ደግሞ ግድ ነው። ስፔሻሊ ቦርደር ላይ ያለውን ሕዝብ ብታየው ስደቱ ቀጥሏል። የመጣላቸው ፋይዳ፣ እስካሁን መሬት ላይ ወርዶ የተገኘ ነገር የለም። መተቃቀፉ፣ መገናኘቱ አምጥቶት የነበረውን ሰላም እንኳን አለመግባባቱ፣ ድጋሚ "እኔን እየነኩኝ ነው" በሚል በዲፕሎማሲያዊ ወርድ ሳይሆን፣ በሌላ ወርድ ድጋሚ ድንበሩ ተዘግቷል።

ሁለቱ ድርጅቶች መኳረፋቸው ሳይሆን አንድ ላይ መሆናቸው ነው ውጤታማ የሚያደርገው፤ እነዚህ ሁለት ድርጅቶች 30 እና 40 ዓመታት አብረው ኖረዋል፤ አሁንም አብረው እየቀጠሉ ናቸው። አብረው እስከቀጠሉ ድረስ፣ አንደኛው አንዱን ጥሎ እስካላጠፋው ድረስ፤ ወይም ደግሞ ሁለቱ ተኳርፈው እኛ ላይ ጉዳት እያመጡ ከሆነ ሁሉቱም አንድ ጠረጴዛ ላይ መገናኘታቸው ኢትዮጵያና ኤርትራ እንደ ሀገር ለጀመሩት ግንኙነት ተጨማሪ ድጋፍ ነው።



ግዮን፦ ፖለቲካ ውስጥ መግባት አልፈልግም ብለኻል፤ ግን ልታስታርቋቸው የምትሞክሩት ሁለቱም ድርጅቶች የፖለቲካ ፓርቲ ናቸው። ይሄ አይጋጭም?

አብርሃም፦ በነገራችን ላይ ፖለቲካ ውስጥ ጠለቅ ብዬ መግባት አልፈልግም የምለው፤ ባለው ቅራኔ ላይ "እኔ ነኝ፣ አንተ ነህ" የሚለው ውስጥ መግባት አልፈልግም ከሚል ነው። የእኛ ፕሮፖዛል ላይ "የጥፋታቸውን መጠን ለታሪክ ተመራማሪዎች ትተን፤ ዕርቁ ላይ ትኩረት እናድርጋለን" ነው የሚለው። እኔ ኤርትራ ተወልጄ ነው ያደግሁት፣ ይሄ ኮንፍሊክት ነው "ኢትዮጵያዊ ነህ" ተብዬ ወደ እዚህ እንድባረር ያደረገኝ። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ሆኜ ስሜቱ አለኝ፣ ኤርትራ ውስጥ ሆኜ ያየሁትም ስሜት አለ። ሁሉቱም ሕዝብ በእነዚህ ድርጅቶች ችግር ሲሰቃይ፣ ሲሞት፣ ወደ ባህር ሲገባ እኔ አውቃለሁ። የቅርብ ጓደኞቼንም አጥቼበታለሁ።

ስለዚህ ጉዳዩ ላይ ላዩን የምንፈታው ችግር እንዳልሆነ አውቃለሁ። የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግስታት የሚያደርጉትን ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን፣ አስተማማኝና ሙሉ እንዲሆን የእነዚህ ድርጅቶች ዕርቅ አስፈላጊ ነው ብዬ የተነሳሁት ከላይ ከጠቀስኩት አንፃል ነው። የኤርትራ ሕዝብ አልተመቸውም፤ ‹‹በዚህ ኮንፍሊክት ተወረናል፣ መሬታችንን እስክናስመልስ ድረስ መከላከል ላይ ነው ያለነው›› የሚል ነው። ለእዚህ ሪፎርም ማካሄድ አይቻልም። የኤርትራ ሕዝብ ነፃነት ሰላም እንዲያገኝ ይሄ ነገር መዘጋትና በዕርቅ መቋጨት አለበት ብዬ አምናለሁ።

ግዮን፦ ይህንን ዕርቅ ዕውን ለማድረግ ከድርጅቶቹ ጋር የደረሳችሁበት ስምምነትና መግባባት አለ?

አብርሃም፦ የእኛ አቅም የሕዝብ ፍላጎት ነው፤ ህዝብ መንግስታትን አስገድዶ፣ መንግስት የሚቀይርበት ሁኔታ ላይ እንዳለን ከተለያዩ ሀገራት ተሞክሮዎች መመልከት እንችላለን፤ ስለዚህ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች፣ በተለይ እዛ ቦርደር ላይ ያሉ ሕዝቦች በአንድ አስተሳሰብና ዓላማ ስር እስኪመጡ ድረስ ይሄንን ፍላጎታቸውን ወደዱም ጠሉም ሁለቱ ፓርቲዎች ቁጭ ብለው እንዲያስፈፅሙላቸው የማድረግ አቅም አላቸው። እኛ በጥናታችን የሕዝቡ ፍላጎት ስላለና ስለተረዳን ነው እዚህ ጉዳይ ውስጥ የገባነው።

ይሄንን ጅምር እንቅስቃሴያችንን የኤርትራ መንግስት እንዲያውቅ አድርገናል በደብዳቤ። ከክቡር ፕሬዝዳቱ ቢሮ ጀምሮ ወደ ስድስት የሚጠጉ ሚኒስትሮች የዕርቅ ጥረት መጀመሩን እንዲያውቁ፣ አግዙን ከሚል መልዕክት ጋር አድርሰናል። በተመሳሳይ ትግ ራይ ክልልን ለሚመራው ሕወ ሓት ደብዳቤ አስገብተናል።

ግዮን፦ ምን ምላሽ አገኛችሁ?

አብርሃም፦ አሁን ጥረቱ መጀመሩን ነው ያሳወቅነው፤ መልሱን ደግሞ ከዚህ በኋላ ስለምንጠይቅ ጊዜው ሲደርስ ሀሳቡ ምን ላይ እንደደረሰ ለሕዝብ ይፋ እናደርጋለን። አሁን ባለው ሁኔታ ድርጅቶቹ እምቢም፣ እሺም አላሉም። እኛ ግን የዕርቁ ግንኙነት እንዲጀመር ፍላጎት ስላለ ጥያቄ አቅርበናል።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኔና ወንድሜ ሃብቶም ገ/ሊባኖስ ይሄንን ሀሳብ ያነሳነው ለጉዳዩ ቅርብ ስለሆንን ነው። ከዚህ የምናገኘው ትርፍ ሪሊፍ ነው። እኛ በግል ጥቅም የምናገኝባቸው ሌሎች ቢዝነሶች አሉን፣ ላውንጆች ላይ ነው የምንቀሳቀሰው። ይሄን ጥረት አንዳንዶች በኤርትራ መንግስት በኩል የምንደገፍ፣ ሌሎች ደግሞ በሕወሓት በኩል የምንታገዝ አድርገው አሉባልታ ሲነዙ እንሰማለን። እኛ ከሁለቱም ወገን የለንበትም። ለእዚህ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ፋይናንሻል ወጪዎችን የሚሸፍኑሉን አቶ ዳዊት ገ/እግዚአብሔር የሚባሉ ባለሀብት ናቸው።

ባለፉ አራት ዓመታት ሁለቱን ሀገራት ለማስታረቅ በተደረገው ጥረት ውስጥ ጉልህ አስተዋፅዖ ማድረጋቸውን ተከትሎ እኚህ ባለሀብት በሁለቱም ወገን ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴዎች "የኢትዮ - ኤርትራ የሕዝብ ለሕዝብ የሠላም አምባሳደር" በማለት እንደመረጧቸውና እንደሸለሟቸው ይታወቃል። እኚህ ሰው ናቸው ሀሳባችን ዕውን እንዲሆን በፋይናንስ እያገዙን ያሉት። አሁን እኛ ለዕርቁ ጅማሬ መንገድ ላይ ነው ያለነው፣ ከዚህ በኋላ ያለውን ሂደት ግን የኢትዮጵያ መንግስት እጁን ከተቶ እንዲያግዘን ነው ፍላጎታችን። ምክንያቱም የሚጨርሱት እነሱ ስለሆኑ፤ የእኛ ስራ ሀሳቡን ማቀበል፣ የሕዝብን ፍላጎት ማሳየት ነው፤ ፍፃሜው የሚያደርሱት ግን የኢትዮጵያ እና የኤርትራ መንግስታት ናቸው።

ግዮን፦ አሁን በድንበር አካባቢ ያሉ የሁለቱም ሀገር ሕዝቦች ስሜት ምን ይመስላል?

አብርሃም፦ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ይሄን ሀሳብ ስናመጣ ወደየሀገራቱ እየሄደን በቂ ሪሰርች ሰርተናል። ሰላም ከሆነ በኋላ አስመራ ሄደናል፣ የኤርትራ ህዝብ ለእኛ አብሮ አደጋችን ስለሆነ ዲቴል ችግሩን ለመንገር የለበትም። ሁለት ወር ሙሉ ይሄንን ነገር ሕዝቡን ተጠግተን አግኝተናል። በትግራይ በኩል ይሄን አይነት ግንኙነት አካሂደናል። ባለፈው ግንኙነታቸው ላይ ኤርትራውያን ተጥልለውባቸው በነበሩ አምስት ትግራይ ውስጥ በሚገኙ መጠለያዎች ውይይት አካሂደን እናውቃን።

የሕዝቡ ፍላጎት ሰላምና ፍቅር ነው። በነገራችን ላይ በጣም የሚገርም ነገር ያየነው፤ ቦርደር ላይ ኢትዮጵያውያን እያረሱበት ካለ መሬት በቅርብ ርቀት ባዶ መሬት አለ ግን አያርሱትም። ይሄ መሬት ለምንድን ነው የማይታረሰው? ካልካቸው ‹‹የኤርትራዊ እከሌ መሬት ነው አናርስም›› ይሉሃል። 20 ዓመት ሙሉ መሬት ጠባቸው ባዶውን መሬት አልነኩትም። በተመሳሳይ በኤርትራ በኩልም እስካሁን የኢትዮጵያዊ የሆነ መሬትን ማንም አልወሰደም። ቅድም ያነሳሁት የሁለቱ ድርጅቶች አመራሮች ቅራኔ እንጂ የሕዝብ ግጭትና ቅራኔ እንዳልሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል።

በግልፅ ያየነው በሀለቱም ወገን 20 ዓመት ሙሉ አንዱ የሌላውን መሬት ሳይነኩ፣ አሁንም በጨለማ እየተደበቁ ሠርግና ጋብቻ እያደረጉ ያሉበት ሁኔታ ነው ያለው። ሕዝቦቹ ይዋደዳሉ፣ ይከባበራሉ፣ ይፈላለጋሉ። የሕዝቡ ፀብ ስላልሆነ፤ ቅራኔው ጫንቃው ላይ መከራ የጫኑበት ድርጅቶች ችግር ግን፣ ለዘለቄታው መነሳት ይኖርበታል ነው የምንለው።

ግዮን፦ እናመሰግናለን።

# አቧራ ወይስ አሻራ? !

## ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ በእራት ግብዣው ላይ ያደረጉት ሙሉ ንግግር

*ክቡራትና ክቡራን፣ እንደምን አመሻችሁ!፣ አሰላም አለይኩም!፣ Good Evening!፣ ኒ ሐው!፣ ናማስቴ!፣ ቦና ሴራ!*

“በሰላምታህ አስቀድመህ ልቤን ረታኸው ፣ You had me at Hello” ይላሉ እንግሊዛውያን፡፡ አገላለፁን ጠለቅ ብለን ከመረመርነው በውስጡ ታላቅ ፍሬ ነገር እንዳዘለ መገንዘብ አንቸገርም፡፡ በመጀመሪያው የግንኙነት ወቅት ለእንግዳችን የምናቀርበው ሰላምታ ከድምፀቱ እስከምንደረድራቸው ቃላትና እስከምናሳካው ሐረግ ለቀጣይ ግንኙነታችን መንገድ ጠራጊ ነው፡፡

ሁሌም ግርምት የሚያጭርብኝ ጉዳይ በእንግዳ ተቀባይነታችንና በትኅትናችን የምንታወቀው እኛ ኢትዮጵያውያን፤ ከአብዛኞቹ ሀገራት በተለየ የግንኙነት ሰላምታ አሰጣጣችን በቀጥታ መልካም ከመመኘት ይልቅ፣ የውሎና አዳር ደኅንነታችንን የሚጠይቅ ለምን ሆነ? የሚለው ነው፡፡

እንደምን አደርክ? እንደምን ዋልክ? እንደምን አመሸህ?

ከንጋት እስከ ምሽት ያለው የሰላምታ መግለጫ ሐረጎቻችን በልባችን ውስጥ ያለንን ጥልቅ ሐሳብና ፍቅር አያመለክቱም፡፡ ለምሳሌ ያህል በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጠዋት ስንገናኝ Good Morning - መልካም ጠዋት እንላለን፡፡ በዐረብኛ ቋንቋም “አሰላም አለይኩም” (ሰላም በአንተ ላይ ይሁን፣ ሰላም ካንተ ጋር ይሁን) የሚል የሰላምታ ልውውጥ አለ፡፡ በጣልያንኛም ቢሆን “Buon giorno” or “Buno sera” “መልካም ጠዋት፣ መልካም ምሽት” የሚል የሰላምታ ሐረግ ይገኛል፡፡ በሕንድ እጅን አጣምሮ የሚሰጠው ሰላምታ ከዚያም በላይ ርቆ በመንዝዝ bhaarat mein namaskaar “በአንተ ውስጥ ላለው አምላክ ሰላምታ እሰጣለሁ” እስከ ማለት ይዝዛል፡፡

ታላቅ የእንግዳ ተቀባይነት ባህልና ዕምቅ የቋንቋ ክምችት ያለን ኢትዮጵያውያን የሰላምታ ቋንቋችንን መልሰን ማየት ሳይኖርብን አይቀርም፡፡ ከሥጋትና ከጭንቀት በመውጣት የተስፋ ብርሃንን በልባችን ማሳደር ያሻናል፡፡ አዎን ከፊታችን አዲስ ቀንና አዲስ ተስፋ በመኖሩ፣ እንደ ከተማችንና እንደ ሀገራችን ሁሉ ሰላምታችንም በሰላምና በአዲስ ተስፋ መታጀብ ይኖርበታል፡፡ የመኖር ደኅንነት ሰላምታችን ከማይሆንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ጠንክረን መሥራት አለብን፡፡

በዚህ ታሪካዊ ቦታ ታሪክ ለመሥራት የተሰበሰባችሁ፣ ክቡራትና ክቡራን፤ ዛሬ ለእናንተ የማነሳው አንድ ጉዳይ አለኝ፡፡ ስለ አቧራና አሻራ ጉዳይ፡፡ በትውልድ ጉዞ ውስጥ አቧራ ያነሡም፣ አሻራ ያተሙም ሰዎች ነበሩ፣ አሉ፡፡ ወደፊትም ይኖራሉ፡፡ አቧራ ማስነሳት ቀላል ነው፡፡ አካባቢን ማናወጥ ይበቃዋል፡፡ መርገጥ መረጋገጥ ከበቂ በላይ አቧራ ያስነሣል፡፡ አቧራው በቀላሉ ይታያል፡፡ ወደ ላይ በቀላሉ ይንሳፈፋል፡፡ በቶሎም በአካባቢው ሁሉ ይዳረሳል፡፡ በሀገራችንም “አቧራ ሲነሣ፣ ጉፋያ ሲያገሣ በቀላሉ ይታወቃል” ይባላል፡፡ ጉፋያ የተባለው ያረጀ የጃጀ አንበሳ ነው፡፡ አንድ ቦታ ሆኖ፣ ያለ የሌለ ዐቅሙን ሰብስቦ ሲጮኽ ሁሉም ስለሚሰማው ነው፡፡

አቧራ ችግሩ ዓይንን ጋርዶ ከእይታ፣ ጉሮሮን አፍኖ ከመናገር፣ ጆሮን ደፍኖ ከመስማት - ከማዳመጥ ይከለከላል፡፡ አካባቢውንም የሕይወት ሳይሆን የሞት ቀጠና ያስመስለዋል፡፡ ምንም እንኳን ላስነሣው ሰውዬ “ጨሰ አቧራው ጨሰ” ተብሎ ቢዘፈንለትም፤ አቧራው እየባሰ ሲሄድ ግን ዘፋኞቹ ወደ አልቃሽነት መቀየራቸው አይቀሬ ነው፡፡

አሻራ የአቧራ ያህል ቶሎ አይታይም፣ ቶሎም ወደ ላይ አይነሣም፤ በቶሎም ስም አያስጠራም፡፡ በቀላሉም አሻራ ጥሎ መሄድ አይቻልም፡፡ ብዙም ድምፅ የለውም፣ ብዙም ታይታ አይገኝበትም፡፡ አድካሚ ነው፣ አሰልቺም ነው፡፡ ሐሜትና ትችት፣ ነቀፋና ወረፋ ያስከትላል፡፡ ያልተረዱ እስኪረዱ፣ የተረዱ እስኪሠሩ፣ የሚሠሩ እስኪፈፀሙ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ትዕግሥትን ይፈታተናል፡፡ በዓለም ላይ የትውልድ አሻራን ያኖሩ ሁሉ ይህ ገጥሟቸዋል፡፤

በዛሬም ምሽት በፊታችን የተዘረጋው ጥያቄ ይሄው ነው፡፡ አሻራ ወይስ አቧራ? የሚል፡፡ የአክሱም ሐውልቶች፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲናት፣ የፋሲል ቤተ መንግስት፣ የጀጎል ግንብ፣ የጂማ አባ ጅፋር ቤተ መንግሥት አሻራ እንጂ አቧራ አይደሉም፡፡ የዐድዋና የካራማራ ድሎች አሻራ እንጂ አቧራ አይደሉም፡፡ የነ ፀጋዬ ገብረ መድኅን፣ የነ ሐዲስ አለማየሁ፣ የነ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ የነ ጥላሁን ገሠሠ፣ የነ ዓሊ ቢራ፣ የነ አበበ በቂላ፣ የነ ምሩጽ ይፍጠር፣ የነ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ፣ የነ ደራርቱ ቱሉ ሥራዎችና ድሎች ሁሉ አሻራ እንጂ አቧራ አልነበሩም፤ አይደሉምም፡፡ ሁሉም አሻራቸውን ያስቀመጡት በየመስካቸው ነው፡፡ ብንጠይቃቸው ግን አንድ ተመሳሳይ ነገር ይነግሩናል፡፡ አሻራን ማስቀመጥ ሲጀመር ፈታኝ - ሲፈፀም አስመስጋኝ የመሆኑን ዘላለማዊ እውነት፡፡

በዚህ ዘመንም አቧራ አስነሥጠው ስም ለማስጠራት፣ ታሪክ ለመሥራት የሚደክሙ ሰዎች አሉ፡፡ ለጊዜው ያደናግራል፡፡ አቧራ ማስነሣት የጉብዝና ምልክት ይመስላል፡፡ “ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች” እንደተባለውም ለጊዜው ስምን ያስጠራ ይመስላል፡፡ የአቧራና አቧራ አስነሺዎች ታሪክና ሥራ ግን እንኳን ዘመን ወቅትን አይሻገርም፡፡ “ያማ ቀርቶ ሌላ ዘፈን መጥቶ” እንደሚባለው ፋሽን ሆኖ መጥቶ እንደ ፋሽን ያልፋል፡፡ የሀገራችን ታሪክም ይሄን ይነግረናል፡፡ መከራና ችግርን ተቋቁመው እዚህ የደረሱልን የሀገራችን መኩሪያ ቅርሶች አሻራዎች እንጂ አቧራዎች አይደሉም፡፡ በየዘመኑ የተነሡት አቧራዎች ለጊዜው ታይተው፣ አስደንቀው፣ አደባልቀው፣ አነዋውጠው ሄደዋል፤ አልፈዋል፡፡

መልካም ሥራን የመከወኛ ጥሩው ጊዜ መቼ ነው? ተብለው ይጠየቃሉ - ጠቢቡ ሰው፤ አላመነቱም ሲመልሱ፡፡ በልበ ሙሉነት “መልካም ሥራ የመከወኛ ጊዜዋ ትናንት ነው” ሲሉ መለሱ፡፡ ዛሬማ ይዘገያል፡፡ ነገ - ይብሱኑ ይረፍድብናል፡፡ ጊዜ የለንም ብለን በቁጭት ጥድፊያ ውስጥ መግባት የሚኖርብን በዚህ የተነሳ ነው፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ የተከማቸ ታላቅ ሀብት ምስጢሩ ታላቅ ሐሳብ እንጂ ተፈጥሯዊ ችሮታ አይደለም፡፡ ታላቅ ሐሳብ የደማቅ አሻራ መነሻ መሰረት ነው፡፡ ደማቅ አሻራ አብዝቶ በመስጠት እንጂ በመቀበል የሚገኝ ፍሬ አይደለም፡፡ የጋራ ቤትን ተባብሮ ለመሥራት በቆረጥን ጊዜ ሁሉ፣ በአብሮነትም በጋራ ለመቆም በተነሣን ጊዜ ድል ከፊታችን ትቀርባለች፡፡ እናሸንፋለን እንጂ ሽንፈት አጠገባችን አይቀርብም፡፡ በጎ ተግባርና ምግባር በመስጠታችን ልክ፣ ለማጣት በተዘጋጀን መጠን ዋጋው ከፍ ይላል፡፡ በትልቁ ማትረፍንና አሻራውን ማኖር አሁንም ዛሬም ሆነ ነገ ከመስጠት ጋር በጽናት ይቁም፡፡

መሰናክልን አይፍራ፡፡ ፈተናንም አይሸሻት፤ በአሻራው ዘለዓለማዊነት ይካሳልና፡፡ ያለመሞት ምሥጢር - እንደ ዋዛ ተረስቶ ያለመቅረት የሐውልትነት ትንግርት - ዛሬን ከወደፊት የማስናኘት እውነት የሚገኘው ከመስጠት እንጂ ከመቀበል አይደለም፡፡

አሻራ የሚተዉ ሰዎች የዚያን ዘመን ባለ ሥልጣናት፣ የዚያን ዘመን ፖለቲካ፣ የዚያን ዘመን ድጋፍና ተቃውሞ ከቁብ አይቆጥሩትም፡፡ አሻራ የሚተው ሰው አሻራውን የሚያስቀምጠው ለመንግሥት ሲል አይደለም፤ ለባለሥልጣናት ሲልም አይደለም፤ ለፓርቲዎች ሲልም አይደለም፤ ለድርጅቶችም ሲባል አይደለም፤ ለሀገሩ ሲል ብቻ ነው፡፡ አሻራ የሚቀመጠው ለሀገር ነው፡፡

“ሀገራችን ቆላ እርሻው በደጃችን፤ ያ ቢሾም ያ ቢሻር እኛ ምን ተዳችን” እንዳለው ገበሬ አሻራ ከሚሾሙና ከሚሻሩ ባለ ሥልጣናት ጋር አይገናኝም፡፡ ከማትሾምና ከማትሻር የጋራ ቤታችን ከሆነች፣ ሁላችንንም እንደ አመላችን ከምታቅፈን ውድ ሀገራችን ጋር እንጂ፡፡ ያ ሲሾም ያ ሲሻር የሚጨንቀው አቧራ የሚያስነሣ ሰው ነው፤ እኛ ከእነርሱ ወገን አይደለንም፡፡ ▶



በዛሬው ምሽት የተገናኘንበትን መስጠት የላቀ መስጠት የሚያደርገው የዓላማው ቅድስና ነው። በተቀደሰ ተግባርና በተቀደሰ ዓላማ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆን ሁሉ ነገ አንገቱን ያቀናል እንጂ አይሰብርም። በተከለው አንድ ፍሬ ምትክ ሺሕ ፍሬዎችን ለመልቀም የሚታደል ቅን ገበሬ መደሰት ያንሰው እንደሁ እንጂ አይበዛበትም። እናንተ የመስጠት ገበሬዎች ናችሁ። ሁሌም ስጡ። የምትሰጡ ከኪስና ከእጃችሁ እንዳይጠፋ ሰግታችሁ ካልሆነ በቀር መስጠትን አትሽሹት።

ቀደምት ወላጆቻችን ከመስጠት ጋር ተያይዞ አንዲት ሽጋ ምርቃት አላቸው። "የሰጠም አብዝቶ ይስጠው፣ ያልሰጠው እንዲሰጥ ይስጠው" ይላሉ። መልካም ብለዋል። የምንሰጠው ብቻም ሳንሆን የምንቀበለውም ጭምር መዳረሻ ግባችን መስጠት፣ ደግሞ ደጋግሞ መስጠት እና አሻራ ማኖር ነው። ለሰጣችሁ አብዝቶ ይስጣችሁ - ላልሰጠንም እንሰጥ ዘንድ አብዝቶ ይስጠን።

ዛሬ እዚህ ቦታ የተሰብሰብነው ራት ለመብላት አይደለም። አሻራ ለማኖር ነው። የከፈላችሁት ገንዘብ ለእራት የሚከፈል አይደለም። በኢትዮጵያ ዕድገትና ሥልጣኔ ላይ አሻራችሁን ለማኖር ነው። አስቡት ከዛሬ ሠላሳና ዐርባ ዓመት በኋላ፤ ሁላችንም አርጅተን በዚህ የአዲስ አበባ ተፋሰስ ግራና ቀኝ፣ ከዘራችንን ይዘን ወዲያና ወዲህ ስንል የሚሰማንን ስሜት፤ የዛሬውን ቀን ስታስቡት የሚሰማችሁን ደስታ - አስቡት እስኪ። እውነት ለመናገር ያ ደስታ በ5 ሚሊዮን ብር የሚገኝ እንዳሆነ ለእናንተ ማስረዳት - ለቀባሪው ማርዳት ነው። ልጆቻችን በዚህ የትውልድ ፕሮጀክት ላይ ስማችንን ሲያዩት፣ የዛሬው ፎቶ ግራፋችን ሲመለከቱት፣ የዚያ ዘመን ትውልድ በወንዞቹ ዳርቻ እየተዝናና፣ በዛፎቹ ሥር እያወጋ፣ በቤተ መፃህፍቱ ውስጡ እያነበበ፣ ይህንን አሻራ የተውለትን አባቶቹንና እናቶቹን ሲያመስግን ምን ሊሰማን እንደሚችል እስቲ ለአፍታ አስቡት።

ዛሬ እዚህ የተገናኘነው ለአባቶቻችን ክብር እና ለልጆቻችን ፍቅር ስንል ሁላችንም ለምንወዳት ቤታችን፤ የኢትዮጵያውያን የወል ካስማ - የታላቂቱ አፍሪካ ዋና ከተማ እና የብዙ ታሪካችን ማማ ለሆነችው ለአዲስ አበባ አደይ አበባዋን እንመልስላት ዘንድ ነው። ከተማችን ከመስከረም ወፍ እና ከቢራቢሮዎች ውብ ትዕይነት ከተፋታች ቆይታለች። ከተማችን ከተክሎች የተፈጥሮ መዓዛ - በስሱ ከሚነፍስ ቀዝቃዛ ንፋስ እና ዝቅ ብለው ከሚበሩ መንፈስ ጠጋኝ ድንቅ ወፎች ከተኳረፈች ከራርማለች። ይሄንን ማጣታችን እኛንም ሆነ ልጆቻችንን ያሳጣን ብዙ ነገር አለ።

የደጋጎቹ አባቶቻችን ለልጆቻችን ጨካኝ እንሆን ዘንድ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን - እምነታችን - ባሕላችን እና የትናንት ታሪካችን አይፈቅድልንም፤ በፍፁም። እናም እኛ የእኛን አደይ አይተናል የእኛን የመስከረም ወፍ ቆጥረናል፣ አባቶቻችን ቆሻሻ ያላሸነፈው ቀበና፣ ውኃ ያልነጠፈው ግንፍሌ፣ መኖሩ ያላሰጋው ጎርደሜ፣ የፋብሪካ ፍሳሽ ያልገደለው አቃቂን አስረክበውናል፤ እኛስ ለልጆቻችን ምን እንስጣቸው!? ዛሬ እዚህ ያገናኘን ይህ ጥያቄ ነው።

የዛሬ ድካማችን፣ ትችቱና ነቀፌታው፣ የልክ አይደለም ማስረገጫ እልፍ ሰበቡ፣ የአይሆንም - ይሆናል ውዝግቡ .... ሁሉ ያኔ ይረሳል። ግራ ቀኝ ሆነው የሚሟገቱት ሁሉ ያኔ አይኖሩም፤ እንዳይሰራ ዕንቅፋት፣ እንዳይሳካ የጎን ውጋት የሆኑት ሁሉ በሂደት ያልፉሉ። የሚያስታውሳቸውም አይኖርም። ሥራ ግን አሻራ ነው። አሻራ ደግሞ ዘመን ተሻጋሪ ነው። የዛሬዋን ቀን ማሰብ ያለብን ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ሆነን ነው። ዛሬን ለነገ እየተከልን ነው።

አባቶቻችን ልበ ሩኅሩህ ደጎች - ወኔ ሙሉ ጀግኖች - ሆደ ሰፊ ቅኖች ስለነበሩ ዛሬ እኛ የምንመካበትን - ግን የመመካታችንን እና የነፃነታችን ቀንዲል እያልን የማዜማችንን ያህል ያልተንከባከብናትን ውብ ሀገር አወረሱን። ደጋግሜ እንደምለውም ይህች ሀገር ከአባቶቻችን የወረስናት ብቻ ሳትሆን ከልጆቻችንም የተዋስናት ናትና እኛስ ላዋሱን ልጆቻችን ይህችን ሀገር ስናስረክብ እጃችን ከምን? ከልጆቻችን የሚጠብቀን - ኅሊናችንም የሚጠይቀን ጥለነው ስለምናሳልፈው ታሪክም ስናስብ የሚያስጨንቀን እና የሚያሳቅቀን ቁልፍ ጥያቄ ይሄ ነው። በመዋስ በመውረስ መካከል ያለው ክፍተት የሚሞላው እና የትውልድ ሠንሠለት ጤናማ ሆኖ የሚቀጥለው በመስጠት ነው፤ በመስጠትም ብቻ ሳይሆን በመሰጠት - በተራዛሚውም አሻራ ለማኖር በመጀገን ጭምር ነው።

በራሱ ላብ ራሱን ሊከፍል የሚተጋ ሕዝብ ቢዘገይም እንኳ ከራሱ አልፎ ለሌሎች መትረፋ አይቀሬ ነው። ከመቀበል ይልቅ መስጠትን መርጠን እንድንቆም የሚያስወድደን የመደመር ዕሴት መነሻ አንዱ መሰረትም ይኸው ሐቅ ነው። በጋራ፣ በመተባበርና በአብሮነትም እንጂ በነጠላ የግል ጉዞ አከባቢን መጠበቅ አይቻልም። በመጥፋት ላይ ያለውን የአካባቢ ሕይወትና ውበት፣ ውድመት እና ጥፋት ከመደመር ፍልስፍናና እሳቤ ውጭ መልሶ እንዲያገመግም ማስቻል አይቻልም፤ እናለዝበው ብንል እንኳን እጅጉን ከባድ ነው። በተፈጥሮ ሚዛን ጥበቃ ውስጥ እኔ እንድኖር ሌሎችም መኖር ይኖባቸዋል ብሎ መነሳት ቀዳሚ ጉዳይ ነው። መጨፈን ምን አልባት ሥራና ወጪን እንጂ ጥፋትን አያስቀርም። በሸገር ፕሮጀክት ከተማችንን እንደስሟ የማስዋብ፣ የማሣመርና ከፍ የማድረግ እርምጃ መነሻ የመደመር ታላቅ ሐሳብና የአርቆ አስተዋይነት ውጤት ነው።

ልጆቻችን ገሚሶቹ በአካል ሌሎቹም በሥነ ልቦናና በምናብ ስደተኛ ሆነዋል። ኢትዮጵያዊውን ቀለም፣ ማንነትና ስብዕና እየተው፤ የቆጡን ለማውረድ የብብታቸውን እየጣሉ ያሉ ልጆቻችንን ወደሚወዷት ቤታቸው የመመለስና የሚወዷትን ከተማ የመገንባት ኃላፊነት የእኛ የሁላችንም ነው። እኛ ዛሬ ልጆቻችን የዚህች ሀገር ትምህርት ባይጥማቸው አሜሪካና አውሮፓ - እረፍት ቢያምራቸው ዱባይና ጣልያን - ሕክምና ቢያስፈልጋቸው ባንኮክና ጀርመን ልከን ያሻንን እናደርግ ይሆናል። ስለ ሁለት ነገር ቆም ብለን እንድናስብ እፈልጋለሁ፤ አንድም ይህንን ማድረግ ስለማይችሉ - ግን ይህችን ሀገር በሥጋቸው ብቻ ሳይሆን በነፍሳቸውም ጭምር ስላዘሉ ብዙ ወገኖቻችን፤ ሁለትም ይህች ሀገር እየፈለገቻቸው እየፈለጓት የታሪካቸው ብዙ ገፅ በባዕዳን ቀለም በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በሩቅ ምሥራቅ እየተፃፈባቸው ስላሉ ልጆቻችን።

ኒውዮርክ የዓለማችን መዲና ከተማ ብቻ ሳትሆን የማታንቀላፋዋ ከተማ በመባልም ትታወቃለች። አዲስ አበባም የአፍሪካ መዲና ብቻ ከመባል አልፋ የአፍሪካ ውብና ፅዱዋ ከተማ የምትባልበት ጊዜ እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ። አልማለሁም። እነሆ ከባዱን የመጀመሪያ ርምጃ አንድ ብለን ጀምረናል። በንፅህና ባህሉ እና በተግባራዊ መልኩ እንጂ ከተማ በስሙ አይወደድም። በግብሩ እንጂ በባዶ ቃሉ አይመሰገንም።

ሀገራት ሀገራትን በተምሳሌነት እንደሚያዩ ሁሉ ከተማዎችም በተምሳሌትነት ከተማን እንደሚያዩ እናውቃለን። ከዚህ በኋላ አዲስ አበባ በሀገራችን ላሉ ሁሉም ከተማዎች በአረንጓዴ አፀድና በንፁህ ምንጭ መፍለቂያነቷ ለአፍሪካ ከተማዎች ሁሉ ተምሳሌት እንደምትሆን አሁንም ተስፋ አደርጋለሁ። በጽዳት ባሕሏም ላይ ከተማችን ስር ነቀል ለውጥ ለማስመዝገብ በነዋሪዎቿ ፊት ቃል ኪዳኗን ታሥራለች። መጭው ትውልድ፣ የመስቀል አዕዋፍ ውርውር ሲሉ፣ የአደይ አበቦችም ሲፈኩ። ልጆቻችን፣ በሕብረ ቀለማት ሽማ ያጌጡ ቢራቢሮዎችን በየበራቸው ማየት ብርቃቸው አይሆንም። በአፀዶችና በጫካዎቻችን ውስጥ አጋምና ቀጋ፣ ኮሽም እና ዶቃ ያብባሉ፤ በኩሬና በምንጮቻችን ውስጥ የውኃ እናት ከዓሣ ዘር ጋር በነፃነት እንደሚዋኙ ተስፋ አደርጋለሁ፣ አምናለሁም።

ለዚህች ታላቅ ሀገር ለዚህች ታላቅ ከተማ፣ ለዚህም ታላቅ ሕዝብ ገፅታውን፣ ታሪኩንና ደረጃውን የሚለውጥ አሻራ ለማኖር እንኳን በዚህ ታረካዊ ሥፍራ ተገናኘን። አቧራው ይጭስ ተውት፤ ስለ እርሱ ብዙ አታስቡ። እኛ አሻራችንን በክብር እናኖራለን። በክብርም በዚህች ሀገር ታሪክ እንታወሳለን፤

ሁላችሁንም አንድ ነገር እጠይቃችኋለሁ። የቀኝ እጃችሁን አውራ ጣት አውጥታችሁ፣ ጠረጴዛው ላይ አብራችሁኝ አሻራችሁን እንድታሰርፉና - የምለውን አብራችሁኝ እንድትሉ፡-

**አቧራውን አልፈዋለሁ፤**

**አሻራዬን አኖራለሁ**

**ታሪኬንም እሠራለሁ።**

**አመሰግናለሁ።**



# በማስተዋል እንራመድ

ብሩክ አስቻለው

የፍቅር፣ የሰላም፣ የይቅርባይነትና የመልካ ምነት አርአያ ተምሳሌት የሆነው ማንዴላ “መጥፎ ነገር ለማድረግ ጥሩ ጊዜ የለም፤ የሚመጣውን ሁሉ ጥሩ ለማድረግ ማመን አለብን” በማለት የተናገሩትን በመሆን፣ ለመሆንም ከባድ መስዋዕትነቶች ጭምር ተቀብለው አስተምረው አልፈዋል። ክብር ያንስባቸዋል።

አንድ ሀገር ካለችበት የከፋ አስተዳደርና ፍፃሜው ከማያምር የዘር ፖለቲካ ወጥታ ብርሃን ወደሚፈነጥቅበት ከፍታ ላይ ለመድረስ እንደ ማንዴላ በአቋሙ የፀና፣ የማይዋዥቅ፣ ግቡን የሚያውቅ ለዚያ ግብም የሚታገል፣ የሚያታግል፤ ከግለኝነት የፀዳ፣ ዘሩ ከተመዘዘበት ጎሳ ይልቅ አጠቃላይ በሀገሩ ጥላ ስር የሚኖሩትን ሁሉ የሚያስቀድም ለዚህም እስከ መስዕትነት የሚፈትኑ ነገሮችን ሁሉ በመጋፈጥ የሚታገል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ቢሳሳት እንኳ ለመታረም እራሱን ያዘጋጀ፣ የነቃና የበቃ መሪ ያስፈልጋታል።

በእርግጥ “አንድ እንጨት ብቻውን አይነድም” እንደሚባለው በግለሰብ ላይ ብቻ የተንጠላጠላ አካሄድ አዋጭ አይደለም። ዘርፈ ብዙ የሆነ መዋቅራዊ ጥንካሬ ያስፈልጋል፤ እዚያ ላይ ነው ችግሩ፣ የመዋቅሩ ቁመና ይኖር ይሆናል አሰራሩ ግን ችግር ስላለበት ከትችት አያመልጥም። በእኔ ምልከታም፡- መንግስት ከከፍተኛ ሚንስትር እስከ ቀበሌ ካቢኔ ድረስ የሚያሰማራቸውን ሰዎች፣ ከጅምሩ ወገናዊነታቸውን ለሀገራዊ አገልግሎት ያላቸውን ቁርጠኝነት በበቂ ሁኔታ ማጥናት ወይም ማብቃት፤ ሲቀጥልም የሚቆጣጠርበት ሰንሰለት አመርቂ እና ግልፅ መሆን አለበት። ይሄ ሀገርን እየመራ ላለ መንግስት ይጠፋ ዋል ብዬ አይደለም፤በጎልዳፋ መጣጥፌ የምሞነጫጭረው፣ የምናየው ውጤት እንዲህ እንድል ስለሚያስገድደን እንጂ። ዛሬ ላይ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ገብተው የሚሰሩ ሁሉ በአንድ ዓይነት አላማ ስር ያሉ ቢመስልም ከምናስተውለው ወቅታዊ ችግር ግን “ውስጡን ለቄስ” የሚያስብል ሁኔታ ነው ያለው።

ለሀገራችን ኢትዮጵያ ትንሳኤ በተለያየ መስክ ተሰማርተው ከልብ የሚተጉትን አብሬ ልደፈጥጥ እንዳልሆነ ግንዛቤ ይወሰድልኝ። ሁላችንም ፍላጎታችን ይለያይ እንጂ ለውጥ ናፋቂዎች ስለሆንን አጨብጭበን በሙሉ ተ ስፋ ሜዳውም ፈረሱም ይኼው ብለን ነበር።

እየተመለሰልን ያለው ግን “ወርቅ ላበደረ ጠጠር” እየሆነ ነው።ሰዎች ከኖሩበት ቀዬ በማንነታቸው የተነሳ ሲፈናቀሉ፣ ሲገደሉ፣ የኛነው ብለው የኖሩበትን መሬት “የእናንተ አይደለም” በሚል የወረደ አመለካከት ሲነጠቁና ሰማይ ሲደፋባቸው፤ “ተው፣እረፉ” በማለት አጥፊዎችን መገሸፅ፣ ስርዓት የማስከበር ስልጣንም አቅምም ያለው ፌደራላዊ መዋቅር ግጭቶች በተከሰቱባቸው አካባቢዎች ምን እያደረገ ነበር? የትስ ገባ?

እነማንን ነው መንግስት በዚያ ቦታ ላይ ያስቀመጠው? አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ ካህናት ሲሰው፣ ባንኮች ሲዘረፉ፣ ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሠት ሲፈፀም፤ በዚያ ያሉ የመንግስት አካላት አቅም ከዳቸው ወይስ አቅማቸውን ለሌሎች አገልግሎት አዋሉት? ተጎጂ ፍትህ አጥቶ፣ ገዳይ “ብሔሬ” በሚለው አደባባይ ከሸለለ፤ እንደ ለውጥ የተደመምንባቸው ይሁንታና አድናቆት የሰጠናቸው ገፀ በረከቶች ቢኖሩም፣ እየተከተለ የመጣውና ስርየት የማይደረግለት በሰው ህይወት ላይ የሚቀልድን ወንጀለኛ የገዳይነት እድሜውን ማራዘም እና ፍትህ አለማስፈን፤ “እየገነቡ ማፍረስ፣ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ” አይሆንምን? “ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም” እንዳይሆንብን ሰጋን።

“በቡድን የተደራጁ ኃይሎች” “የታጠቁ ኃይሎች” በማለት አጥፊውን ወገን በመግለጫ ሸፋፍኖ ማለፍ ይህን ሰፊ እና ታጋሽ ህዝብ ለሚመራ መንግስት የሚመጥን አይደለም። በሰላም ዕጦት ለሚሰቃይ፣ለተቸገረ ሕዝብ መፍትሔ አልባ ንግግር ቁስሉን አይጠግንም። አንድ ቀዳዳ መድፈን ግን ፈውሱን ያፋጥነዋል፤ እናም መንግስት መዋቅሩን ያጥና፣ የንስር ዐይንም ያስፈልገዋል። ማንን የት ቦታ ላስቀምጥ? ብሎ ሲያስብ ከእውነተኛ ሚዛን ፈቀቅ የሚያደርጉትን ጣኦቶቹን ይሰባበር። ያለዚያ “ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ” እንዳይሆንብን እናስተውል።

በቋንቋ በባህል በሃይማኖት በጎሳ በአመለካከትም ጭምር ብዙ ስለሆንን፤ ይህንን ብዝኃነታችንን በሃገራዊ፣ በኢትዮጵያዊ አንድነት ካላሰርነው ውበታችን ይደበዝዛል። ያለ ማሰሪያ የተሰበሰበ እንጨት እጣ ፈንታው የታወቀ ነው። ስለዚህ በየደረጃው ያሉ የመንግስት ኃላፊዎች ሚና ትልቁን ድርሻ ይይዛል።

ሌላው ክልሎች እንደደረጃቸው የፌራሉን አመራር ስራ ከመቀጠል ይልቅ በራሳቸው መንግስት ሆነው የሚያራምዱት አንዳንድ ዕንቅስቃሴ ሃገራዊ ቀውስን እየፈጠረ ነው። ህገ መንግስቱ የሰጣቸው ስልጣን መጠን ፈር የቀደደላቸውም ይመስለኛል።ሁሉም ነገር ጤናማ አካሄድ ሆኖ የሚስተካከለው እነዚህን ሁሉ ማየት ስንችልና ስንተገብር ነው። ሰው ሰው ሆኖ የሚቆመውና ውሎውን ውጤታማ የሚያደርገው ሁሉም የሰውነት ክፍሎቹ ጤናማ ሆነው ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ነው። አንዱ የሰውነት ክፍል ሲታመም ግን ሌሎችም ይታመማሉ፣ ስራውም ይታጎላል። ኢትዮጵያ የምትባል በጋራ የምንኖርባት ድሃ አገራችንን በሽታ እንሁንባት፤ በሽታችን ፈውስ አላጣም፣ መድኃኒት አለው። ሁሉም እንደፈለገ የሚቦርቅበት መንገድ ቅጥ ይያዝ፤ ዋጋ እያስከፈለን ስለሆነ ይታረም።

ሌላኛው ነጥቤ የሚዲያዎች ጉዳይ ነው። ተደጋግሞ እንደሰማነው ሚዲያ ለአንድ ሀገር አራተኛ መንግስት ነው ይባላል። እውነት ነው የአስፈላጊነቱን ደረጃ ይገልፀዋል። በትክክል ከተሰራበት ሚናው ብዙ ነው፤ የዜጎች ንቃተ ህሊና የሚጎለብትበት አንዱ መንገድ ነው። አጠቃቀሙን ካላወቅንበት ደግሞ በጎረቤት አገሮች መንስኤ እንደሆነው ህዝብ እንዲተላለቅ ክብሪት የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው። ሚዲያዎች ጠባብ ስቲዲዮ ውስጥ ሆነው፣ እንኳንስ አስበውበት እንደዋዛ የተናገሩትና የዘሩት ዘር፤ እነሱ ከሚጠብቁት በላይ ሰፊ ማሳ ላይ ተዘርቶ አድጎ ለመሰብሰብ የሚቸግር ፍሬ ያፈራና ለመጠፋፋት አንዱ መንገድ ይሆናል። በተለይ ብሔርተኝነት የወለዳቸው ሚዲያዎች መስፋፋት በራሱ መጥፎ ባይሆንም እንወክለዋለን ላሉት ብሔርም ቢሆን፣ የማይበጅ ስራ መስራት የለባቸውም። እያንዳንዷን አየር ላይ የሚያውሉትን ስራ በማስተዋል በኃላፊነት ስሜት መስራት አለባቸው።

በመጨረሻም ህብረተሰቡ በተለይ የዚች ሀገር የወደፊት ተረካቢ የሆነው ወጣቱ ትውልድ በማስተዋል ይራመድ። ትክክለኛ መንገዱን ሊያገኝ ይሩጥ እንጂ በነዱት ሁሉ የሚንደረደርበት አካሄድ በሬ ሆይ ሳሩን አየህ እንጅ ገደሉን ሳታይ እንደተባለው እንዳይሆን ታሪክንም ያለፈውንም፣ የወቅቱንም ሁኔታ በደመነፍስ ሳይሆን በንቃት፣ ከወገንተኝነት ማለትም ከአድሎአዊነት በፀዳ ሁኔታ ይከ ታተል።

ታሪክን ከመተረክ በዘለለ ታሪክ ሰሪ መሆን ያስፈልጋል። ካወቅንበት አዲሱ ታሪካችን የነገው ትውልድ በኩራት የሚያነሳው፣ እንደ አድዋ ድል የማያፍርበት ለማድረግ አልመ ሽብንም። አላዋቂዎች አወቅን በሚሉት እኩይ አካሄዳቸው እየጨፈሩ እንዲቀጥሉ፤ አሜን ብለን መቀበል የለብንም። ከመፈራራት ይልቅ በመከባበር እንወያይ። ዛሬ መፈራራትን፣ መጠራጠርን በውሎአችን ሁሉ እያየነው ነው። ባለንበት 20ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ የስልጣኔ ደረጃ የትናየት በደረሰበት ሰዓት፤ እኛ ከዚህ በረከተ እውቀት ከመቋደስ ይልቅ በራችንን ዘርህ፣ ብሄርህ፣ ቋንቋህ በሚል ጠንካራ መዝጊያ ጠርቅመን፤ አሳፋሪ በሆነ አዙሪት ከመሽከርከር የበለጠ መሐይምነት የለም። ገና ነን፤ ድህነት ብዙ አሳጥቶናል፣ ደቁሶናል። ከዚህ እንዴት እንውጣ የምንልበት ትልቅ አጀንዳ አለብን። መንቀፋችንም ሆነ መደገፋችን የሰመረ ውጤት ለማምጣት እንጂ የከሰረ ጉዞ ለመተለም እንዳይሆን በማስተዋል እንራመድ እላለሁ።



ጃፈር ሰዩም

# ኢዜማ ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገቡ 6 ወሳኝ ነጥቦች

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም "አገቱኒ ተምረን ወጣን" በተሰኘ የምርጫ 97 ሁነትን ከመነሻው እስከ መድረሻው በሚያስቃኘው መጽሐፋቸው ሥለ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመሰራረት ሲገልጹ ጭቆናን እና ረገጣን "እስከ መቼ ችዬው?" ባሉ ቆራጦች የተመሰረተ እንደሆነ በስፋት ያብራራሉ፡፡

የምርጫ 97 ውጤትን ተከትሎ ጀግኖቹ የቅንጅት መሪዎች በምርጫው በዝረራ በተሸነፈው በአምባገነኑ ህወሃት/ኢህአዴግ ወደ ወህኒ ከወረዱ በኋላ እነዚህ "ጭቆና በቃን" ያሉት አመራሮች በእስር ቤት እጅ ሰጥተው አልተቀመጡም፡፡ ከዚያ ይልቅ ከወህኒ ሲወጡ በምን አይነት መልኩ ከአምባገነኑ መንግስት ጋር ትግል ማካሄድ እንዳለባቸው ያውጠነጥኑ ነበር፡፡

በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ለውስጥ እንዲሁም በአውሮፓና አሜሪካ ካሉ ሰዎች ጋር በመገናኘት አንድ ፓርቲ በህቡዕ ተመሰረተ፡፡ የቅንጅት ሊቀመንበር የነበሩት ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል ስለሁኔታው በሚያወሱበት "ህይወቴና የፖለቲካ እርምጃዬ" በተሰኘው መጽሐፋቸው የዚህን ፓርቲ የውስጥ ለውስጥ ምስረታ ሰምተው ስለ ሁኔታው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ይጠይቃሉ፦ እንደ ገዢው ፓርቲ በሚያደርሰው አፈና፣ እንደ ሀይማኖት በሚያምኑበት የሰላማዊ ትግል ላይ እምነት ያጡት የያኔው ዶክተር "ዴሞክራሲን ለኢትዮጵያ በምናመጣበት መንገድ እናመጣዋለን" በማለት ከሌሎች ጓደቻቸው ጋር በመሆን የሁለገብ ትግል ለማድረግ "ግንቦት 7 ለዴሞክራሲና ለፍትህ ንቅናቄ" የተሰኘውን ፓርቲ መሰረቱት፡፡

ለውጡን ተከትሎ ግንቦት 7 ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ራሱን አክስሞ ከሌሎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለረዥም አመት ከምናውቃቸው ፖለቲከኞች ጋር በመሆን ይህንን በዜግነት ፖለቲካ የሚያምን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ(ኢዜማ) የተሰኘውን ፓርቲ ለማቋቋም ችለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ(ኢዜማ) ፓርቲ የዜግነት ፖለቲካን ወደፊት ለማምጣት ተቋቁሞ ከ2 ሳምንት በፊት መስራች ጉባኤ ማካሄዱ የብዙዎቻችንን ትኩረት ስቧል፡፡ ፓርቲው ህብረ ብሔራዊ እንደመሆኑ "በአክራሪ ብሄርተኝነት እየታመመችና እየታመሰች ሳለችዋ ሀገራችን ከበሽታዋ እንድታገግም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ይኖራል" በሚል በርካቶች ተስፋ እንደሚያደርጉበት እሙን ነው፡፡ ከሀገሪቷ ወጣት ፖለቲከኞች እስከ ጉምቱ ፖለቲከኞች ድረስ በፓርቲው ውስጥ መካተታቸው ሌላው ተስፋ ሰጪ ነገር ነው፡፡




የፓርቲውን ፕሮግራም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ አግኝቼው አንብቤዋለሁ፡፡ የፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀቱ፣ በተለይ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገው ፌደራላዊ አወቃቀሩ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ የቀረጻቸው ፕሮግራሞች እንዲሁም የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቹ ፓርቲው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍ ያለ ሚናን ለመጫወት መምጣቱን የሚያሳይ ሆኖ ይታያል፡፡

እንደ አንድ የኢትዮጵያ ፖለቲካን ላለፉት አመታት እንደሚከታተል ኢትዮጵያዊ ኢዜማ እነዚህን 6 አጫጭርና ወሳኝ ነገሮች ትኩረት ሊያደርግባቸው ይገባል በማለት የዛሬውን ጽሁፌን አስቀምጣለሁ፡፡

## 1) ከገዢው ፓርቲ ጋር ያለው መስተጋብርና ግንኙነት

በዶ/ር ዐቢይ አህመድ የሚመራው ኢህአዴግ ምንም እንኳ በእስር ላይ የነበሩትን የተወሰኑት የኢዜማ አመራሮችን የመፍታት ቁርጠኝነትን ከማሳየት ጀምሮ በሽብር ተፈርጀው የነበሩትን ድርጅቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ ጥሪ ከማድረግ እስከ መደራደር ደርሰው ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ አድርጓል፡፡ ይህ ድርጊትም የዴሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት እንደሚደረግ በጎ እርምጃ ተወስዶ ሊበረታታ የሚገባ ቢሆንም ራስን አንዴ እንደተፎካካሪ ፓርቲ (በጠቅላይ ሚንስትሩ ቃል ልጠቀምና) ካቋቋሙ በኋላ ከገዢው ፓርቲ ጋር እጅና ጓንት መስሎ ለህዝብ መታየት፤ አንድም ራስን ማስገመት ከዚያ ከፍ ሲልም ራስን ማስናቅ ነው የሚሆነው፡፡ በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ ስምምነቶች እንዲሁም በሀገር ሰላምና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ አብሮ መስራቱ ሀገርን እንደሚጠቅም ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ የቀደመው ከሕወሓት አስተዳደር ጋር ተፎካካሪ ፓርቲዎች የነበራቸው ደስ የማይል የጠላት የሚመስል ግንኙነት ልክ እንዳልሆነው ሁሉ አሁን በአንዳንድ ፓርቲዎች የምንመለከተው ከኢህአዴግ ጋር የሚደረገው ከመስመር የወጣ አንድነት አይሉት ውህደት አካሄድ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ወደኋላ እንዳይጎትተው ያሰጋል፡፡ በተለይ ኢህአዴግ በኋላ ቀሩ የብሄር ፌደራሊዝም ላይ ተከንቸሮ "በብሄር ፌደራሊዝም አልደራደርም" እስከማለት በደረሰበት በዚህ ወቅት፤ ከኢህአዴግ ጋር የሚደረግ መርህ አልባ ግንኙነት የትም እንደማያደርስና ዋጋ እንደሚያስከፍል ለመናገር ነብይ መሆንን አይጠይቅም፡፡

## 2) ከዘመኑ ጋር የሚሄድ ፈጣን የህዝብ ግንኙነት ቡድን ማዋቀር

ዘመኑ ፈጣን የማህበራዊ ሚዲያ ዘመን መሆኑን ከግምት በማስገባት ፈጣን የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ ቡድን በቦታው በመመደብ፤ ▶

ወቅታዊ መረጃዎችን በፍጥነት የሚያደርስ፣ የተሳሳቱ መረጃዎችን ጉዳት ከማድረሱ በፊት የሚያስተባብል፣ ለተለያዩ ሚዲያዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በፍጥነት ማብራሪያና መልስ የሚሰጥ የህዝብ ግንኙነት ቡድን በማቋቋም፤ የመረጃ ክፍተትን መድፈን ከፓርቲው ይጠበቃል፡፡ በተለይ ምርጫ በሚቃረብበት ወቅት ገዢው ፓርቲም ሆነ የተለያዩ ተፎካካሪዎች በየራሳቸው መንገድ ነጥብ ለማስቆጠር ሲሯሯጡ ስም ማጥፋትን፣ የሀሰት መረጃን እንዲሁም አወዛጋቢ ነገርን በመልቀቅ ፓርቲው ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ከመስመር የወጡ አካሄዶች ሊፈጠሩ ይችላሉና ይህንን በፍጥነት መመከት የሚችል የህዝብ ግንኙነት ቡድን(PR TEAM) በማቋቋም መረጃዎች ስር ሳይሰዱና በመራጩ ላይ ተጽዕኖ ከመፍጠራቸው በፊት ማክሸፍ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ፓርቲው ዘመኑን የሚመጥን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር መናበብ የሚችል ህዝብ ግንኙነት ቡድን መፍጠሩ ላይ በፍጥነት መስራት ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ እስከዛሬ የቀድሞው የዞን 9 ጸሀፊ ናትናኤል ፈለቀ በፌስቡክና ትዊተር እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ሲያጋራን እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ ይህ ድርጊት በቡድን ደረጃ ተቋቁሞ ለህዝብ መረጃን በመስጠት ማጠናከሩ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ሊሆን ይገባል፡፡

### 3) የአዲስ አበባችን ጉዳይ

ፓርቲው በስትራቴጂና ፕሮግራሞቹ ላይ አዲስ አበባን በተመለከተ የሚያራምደው አቋም እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡የአፍሪካ መዲናዋ አዲስ አበባችን የኢትዮጵያ ፖለቲካም እምብርት ናት፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር የሚፈልግ የትኛውም ፓርቲ አዲስ አበባ ላይ የሚያሳየው አቋም አዲስ አበባ ላይ ለሚያገኘው ድምጽም ሆነ በመላ ኢትዮጵያ ለሚሰጠው ድጋፍም ሆነ ድምጽ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ የአዲስ አበባ የባለቤትነት ጉዳይም ሆነ የኦሮሚያ የልዩ ጥቅም ጥያቄ ፓርቲው በፍጹም በቸልተኝነት ሊያየው አይገባም፡፡ ኢዜማ ፕሮግራሙን በእውነተኛ መርህ ላይ ከቀረጸ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያሳየው አቋም በህዝብ ልብ ውስጥ እንዲገባም ሆነ ከህዝብ ልብ እንዲርቅ የሚያደርገው እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ “በስልጡን ፖለቲካ” ስም የህዝብን አወቃቀር፣ ፍላጎትና ታሪካዊ ዳራ ግምት ውስጥ ያላስገባ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ ተብሎ የሚካሄድ የይስሙለ “ሰጥቶ የመቀበል” ፖለቲካ በነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ አንጸባርቃለሁ ማለት ታሪካዊ ስህተት እንደሚሆን ከአሁኑ መናገር ይቻላል፡፡ ፓርቲው የዜግነት ፖለቲካን እንደማቀንቀኑ ከ”የኛና ኬኛ” ጉትቻ ውስጥ ራሱን እንደማያስገባ መገመት ብንችልም “ልዩ ጥቅም” በምትለዋ ጉዳይ ላይ ምን አይነት አቋም እንደሚያራምድም ሆነ በአዲስ አበባ ጉዳይ የፓርቲው ፕሮግራም የሚገልጸው ምንም ነገር የለም፡፡

ስለሆነም ፓርቲው በፖለቲካ ፕሮግራሙ አዲስ አበባችን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ቤት መሆኗንና ባለቤቷም ኗሪው ህዝብ መሆኑን ያላንዳች ማወላዳት በግልጽ በማስቀመጥ ከላይ እንደገለጽኩት የአዲስ አበቤውንም ሆነ የሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች ድጋፍ ማግኘት ይችላል፡፡ ከዚያ ውጪ ለጊዜያዊ ፖለቲካም ተብሎ ይሁን ለሌላ አንዱን ባለቤት ሌላውን ተከራይ የሚያደርግ አካሄድን የሚከተል፣ ገዢው ፓርቲም ይሁን ተፎካካሪ ይህንን አጀንዳውን በጉልበት ሊያስፈጽም እስካልሞከረ ድረስ በሀቅ ላይ ያልተመሰረተ አጀንዳ ስለሆነ በምርጫም አያሸንፍም! መላ ሀገሪቷንም ዋጋ ያስከፍላታል! ከታሪክ ተጠያቂነትም አያመልጥም! ስለዚህ ኢዜማ አዲስ አበባን በተመለከተ ቁርጠኛ አቋምን ያሳየናል ብለን እንጠብቃለን፡፡

### 4) የአመራሩ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

ዘመኑ የማህበራዊ ሚዲያ(social media) ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ በጠንካራ የህዝብ ግንኙነት ቡድን የሚሰራ ውጤታማ ስራ ለፓርቲው ከፍተኛ ጉልበት እንደሚሆነው ሁሉ የፓርቲው አመራሮች ከሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋርም ሆነ ከገዢው ፓርቲ ጋር በማህበራዊ ሚዲያ እሰጣገባ ውስጥ የሚገቡ ከሆን ግን ሰዎች የፓርቲ አመራር የሆነውን ግለሰብ እንደ ግለሰብ ሳይሆን እንደ የፓርቲ አመራር ስለሚቆጥሩ ምንም እንኳ ግለሰቡ የሚያስተላልፈው መልዕክቱ የግል ስሜቱን የሚያንጸባርቅና ፓርቲውን የማይወክል ቢሆንም እንኳ፤ በፓርቲው ላይ ጉዳት ማድረሱ የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም በተቻለ መጠን መሰል ውዝግብ ናፋቂ ግለሰቦች ወደፊት መውጣታቸው ፓርቲውን ዋጋ እንዳያስከፍለው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አመራር ግለሰቦች በግል ገጻቸው ከፓርቲ አቋም ጋር የሚቃረን አስተያየቶችን ማስፈር የማይችሉበት የውስጥ አሰራር እንዲፈጠር ማድረግ ህዝብ ላይ ከሚፈጠር ውዝግብ ያድናል፡፡ ይህን ማድረግ የግለሰብ ነጻነትን የሚጋፋ ከሆነ ደግሞ ግለሰቦቹ የሚያንጸባርቁት ሀሳብ የፓርቲው አቋም አለመሆኑን ያለምንም ይሉኝታ ከስር ከስር እየተከተሉ በማውገዝ ፓርቲውን ከትዝብትና ቅርቃር ውስጥ ማውጣት ይቻላል፡፡

### 5) ከብሄር ፖለቲካው ጋር የሚኖረው ግንኙነት

የብሄር ፖለቲካ በኢትዮጵያ በጣም ስስ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ እንዲሆን አሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ የብሄር ፖለቲካን የሚያራምድ ፓርቲ ወይም የቴሌቪዥን ቻናል በጥቂት ቀናት ውስጥ በቀላሉ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ዶላሮችን ከብሄር ተወላጆቹ መሰብሰብ ሲችል፤ ህጻናት ለሚታከሙበት ለጥቁር አንበሳ የልብ ህክምና ሆስፒታል መሳሪያዎችን ማሟያ እርዳታ ግን አስር ሺ ዶላር ለማግኘት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ቢደረግበት እንኳ ትኩረትን አይስብም፡፡

> ...ኢዜማ የብሄር ፖለቲካ ፓርቲና ሚዲያ ሱቅ ከፍተው እየነገዱ ካሉ ሰዎች ጋር ፓርቲው ብልህት የተሞላበት ግንኙነት ማድረግ ይጠበቅበታል...

ባለፉት 27 አመታት ህዝብ ላይ ከተዘራው የዘረኝነት መርዝ በተጨማሪ በነዚህ ጥቂት አመታት የተፈጠሩ ዘርን መሰረት አድርገው የተቋቋሙ ፓርቲዎችና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሁሉንም ነገር የሚመለከቱት በዘር መነጽር ብቻ ነውና ነገሩን የማክበድ ሀይላቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በሰፊው በገዢው ፓርቲ በኩል በስፋት ይቀነቀን የነበረው የብሄር ፖለቲካ አሁን አሁን ተቃዋሚዎችም በስፋት ሲቀላቀሉት እያስተዋልን ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑት በዜግነት ፖለቲካ ከልባቸው ያምኑ የነበሩ በብሔር መደራጀትን የማይደግፉ ነበሩ፡፡

ኢዜማ የብሄር ፖለቲካ ፓርቲና ሚዲያ ሱቅ ከፍተው እየነገዱ ካሉ ሰዎች ጋር ፓርቲው ብልህት የተሞላበት ግንኙነት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ዜግነትን ማራመድ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ያለምንም ዘር ቆጠራ ወደ አንድ ማዕቀፍ ማምጣት መሆኑን በበሰለ መንገድ ማሳየት መቻል ይኖርበታል፡፡ በፓርቲው ላይ ወይም በአመራሮቹ ላይ ሊነሱ የሚችሉ ፍረጃዎችን በማስረጃ የመመለስ ወይም ስህተቶች ሲፈጠሩም ነገሩን ከመካረር ይልቅ በፍጥነት የማመን፤ እንዲሁም ይቅርታ የመጠየቅ መንገድን በመከተል የህዝብን ልብ ማግኘት ይቻላልና በነዚህም ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ እይታን ማዳበር ግድ ይላል፡፡

### 6) “ስልጣን አንፈልግም”

ከላይ በመግቢያዬ እንዳልኩት በብሔር ፖለቲካ ህመም ለተሰቃየው የኢትዮጵያ ህዝብ በሚልዮኖች ለአስርት አመታት ከኖረበት ቀዬው በብሔሩ ምክንያት ለሚፈናቀለው የኢትዮጵያ ህዝብ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ተስፋ የሚያደርግ በርካታ ህዝብ ይኖራልና አመራሮቹ በየሚዲያው እየቀረቡ የስልጣን ፍላጎት እምብዛም እንደሌላቸው ሲገልጹ ለተመለከተ ሰው እንግዳ ስሜት መፍጠር አይቀርም፡፡ ፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ የተቋቋመ የትኛውም ፓርቲ የስልጣን ፍላጎት ሊኖረውና ለዚያም ሊታገል ይገባል፡፡ ከዚያ ውጪ ማህበረሰቡ ላይ ንቃተ ህሊና ለመፍጠር ወይም የዜግነት ፖለቲካን ህብረተሰቡ ላይ ማስረጽ ከሆነ ዓላማቸው በሲቪክ ማህበር ወይም የሆነ አይነት ንቅናቄ ማቋቋሙ የተሻለ አይሆንም ነበርን? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ “ያለመታደል ሆነና ጠንካራ ተቃዋሚ አጣን” ብለው በድህረ ምርጫ 1993 እንደተናገሩት ሁሉ ይህ ታሪክ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የአስተዳደር ዘመንም ከመደገሙ በፊት ቆፍጠን ብሎ ራስን ጠንካራ ተፎካካሪ አድርጎ በማቅረብ ምስኪኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ከስቃይ ለማውጣት ፓርቲው የአቅሙን ማበርከት አለበት ባይ ነኝ፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ነጥቦች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ፓርቲው ሰሞኑን በሚያካሂዳቸው ህዝባዊ መድረኮች ላይ ይብራራሉ ብዬ ተስፋ የማደርግ ሲሆን በነዚያ ምላሾች ላይ ተነስቼ ወደፊት ሀሳቤን የማክል ይሆናል፡፡



ወ/ጊዮርጊስ ይሁኔ

# ያላስተዋልናቸው ለውጦች!

ለውጥማ አለ! ያውም ግጥም ያለ ለውጥ። መምህራን በ 11/09/2011 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ነበር። ያውም ፍቃድ ሳይሰጣቸው።( እውቅና ያለው አስተባባሪ አካል የነበረው አልመሰለኝም) ታዲያ ምን ተፈጠረ? ምንም። ግርግር የለ።ወከባ የለ።

እንደውም የሚገርመው ነገር የአዲስ አበባ የፖሊስ አባላትና የፌዴራል የፖሊስ አካላት ‹ አይዟችሁ! ግን ከናንተ ውጭ ሌላ አካል በመሀላችሁ ገብቶ እንዳያስቸግራችሁ ጥንቃቄ አድርጉ›› እያሉ ያበረታቱን እና ይመክሩን የነበረው ነገር ነው።ከዚያም አልፈው አስተባባሪዎች ወደ ኢቲቪ ገብተው ድምጻችን ይሰማ! ለማለት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመወያየት ወደ ግቢው ሲገቡ አብረው የገቡ ቢሆንም፤ ውይይታቸውን ግን ላለመስማት ወደ ቢሮው ሳይገቡ ይጠብቁ ነበር።የኢቲቪ ሰዎችም ‹እውቅና ለሌለው ሰልፍ መዘገብ አንችልም› በማለት ሲመልሱና አስተባባሪዎችም ከግቢው ሲወጡ ሁኔታውን ተረድተው የተወሰኑ ፖሊሶች ‹‹ አሁን እኮ ብዙ የሚዲያ አካላት ስላሉ እዚህ ችክ ከምትሉ ወደ ሌላው ብትሄዱ ይሻላል›› በማለት አስተያዬት በመስጠታቸው፤ አስተባባሪዎች እና በርካታ መምህራን ኢሳት ወደሚገኝበት ወደ ባንቢስ አካባቢ ሲሄዱ እጀባቸው የሚገርም ነበር።

ለከተማው የፖሊስ አባላትና ለፌደራል የፖሊስ አባላት የነበረኝ የተዛባ እይታ ተቀርፎልኛል።ለካ አያቶቻችን ወደው አይደለም ‹የዓሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ› የሚሉት። ትክክል ናቸው።በወቅቱ ለነበሩት የጸጥታ አካላትና ለሀላፊዎቻቸው ምስጋና አለመስጠት ንፉግነት ብቻ ሳይሆን አለመማር ነው። አለማገናዘብ፡፡ሁኔታዎችን ለመረዳት አለመቻል።እናም እነሆ አክብሮቴና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ይልመድባችሁ!!

ለውጥማ አለ! ያውም ግጥም ያለ።የፊቱን አላውቅም። ማወቅም አይጠበቅብኝም። ግን ከሁለት ዓመት በፊት እኮ መምህራን አይደለም ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ ቀርቶ በእስታፋቸው ውስጥ ስለፖለቲካ ሲያወሩ (የሚያወሩት እጅግ ጥቂቶች ነበሩ። እንዳሁኑ ሁሉም ‹የፖለቲካ ተንታኝ ነኝ› የሚል በፍለጋ ነበር የሚገኘው። ) በፍራቻና በስጋት ተውጠው ዞር ዞር ብለው በአካባቢያቸው ያለውን ሰው መንጥረው ከለዩ በኂላ ነበር።አሁን ከዛ ሁሉ ፍርሃትና ከተኙበት ጽኑ እንቅልፍ ነቅተው በሰላማዊ ሰልፍ ጥያቄ ማንሳታቸው በራሱ ትልቅ ነጥብ ነው።

ከዓመት በፊት እኮ የግምገማው አቢይ ነጥብ ‹ በህገ-መነግግስቱ ታምናለህ? አታምንም?› የሚል ነበር።በስራህ መቀጠል ትፈልጋለህ? አትፈልግም? አይነት ጥያቄ፤ ስለብሔሮች እንጂ ስለ ዜግነትህ ግድ ስለሌለው ህገ-መንግስት፣ ዜጋውን ስለረሳው ህገ-መንግስት፣ ያለህን አስተሳሰብ ለማዎቅ ትገመገምበት ነበር።ቀጥሎም ‹በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ታምናለህ? አታምንም?› ተብለህ ትገመገም ነበር። ደሃ ስላደረገህ፣ክብርህን ስላዋረደው ፖሊሲና ስትራቴጂ ‹ታምናለህ አታምንም?› ተብለህ ማስፈራሪያ በመሰለ የግምገማ ነጥብ ሰላምህን እንድታጣ ትደረግ ነበር።

ክፍል ውስጥ በማስተማር ብቃትህ፣የተለየ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይተህ በትርፍ ሰዓትህ ማስጠናትህ፣የባህሪ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች እንደጓደኛ አቅርበህ በመምከርህና ከችግራቸው እንዲወጡ በማድረግህ፣በተማሪዎች መወደድህ ራሱ በአስተዳደር አካላት እንድትጠላ ያስደርግህ ነበር እኮ።

ስብሰባ ላይ ሰውኛ ባህሪህና ስሜትህ አስገድዶህ ስለምታየው ችግር ካወራህ፣ ካድሬ በሆኑ በሚቀርቡህ የስራ ባልደረቦችህ ሁለተኛ እንዳትደግመው በተዘዋዋሪ መንገድ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ይደርስህ ነበር እኮ!ስለተማሪዎችህ ችግር ከተናገርክ ሁለተኛ እንዳትደግመው እና እንድትሸማቀቅ ከዛች ‹የደም ወዝ› (ከስራህ አንጻር ደመወዝ ለመባል ብቁ ካልሆነች) ብርህ ላይ በቅጣት ሰበብ፣ርካሽ ምክንያት ተፈልጎ ይወሰድብህ ነበር። የማስጠንቀቂያ ደብዳቤም እንደ ፍቅር ደብዳቤ ቶሎ ቶሎ ይደርስህ ነበር እኮ!

በመማርህና በማስተማርህ ህብረተሰቡ ልጆቹን እንደምታስተማርለት እረስቶ ‹ውይ! አስተማሪ ነህ እንዴ!/ እንዲልህ እና እንድትሸማቀቅ ሆነ ተብሎ በፖሊሲና በስትራቴጂ በሆዳምና ህሊናቸውን በሸጡ ካድሬዎች ተሰርቶብህ ነበር እኮ! አስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍል በጨረሱ (አንዳንዶችን ደግሞ በማታው መርሃ ግበር ባስተማርካቸው) ከወረዳና ከክፍለ ከተማ የትምህርት አስተዳደር አካላት እየመጣ ስለማያውቀው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና፣ ስላልገባው የትምህርት ዘይቤ፣ ስላላነበበው ካፒታሊዝምና ኒዮ ሊበራሊዝም በግዴታ ተሰብሰብ ተብለህ እየሰበከህ ጆሮህን ያደማው ነበር እኮ! ተናደህ የምታውቀውን ለማስረዳት እጅ አውጥተህ ስትናገር ስድብ ቀረሽ ምላሽ ይሰጥህ ነበር እኮ! ከፍ ሲልም እንደተቃዋሚ ታይተህ በአይነ ቁራኛ ትታይ ነበር እኮ! አሁን ይሄ ነገር ቀርቶልሃል። ታዲያ ለውጥ የለም!? አሁን እኮ ከፍርሃትህ ዛጎል ወጥተሃል። ታዲያ ይሄስ ለውጥ አይደለም!? ትናንት የበላኸውን ምሳ ብትረሳ እንኳን በተፈጥሮ ተሰጥቶህ የነበረውን የመናገር ነጻነት ሰዎች ቀምተውህ አልነበረም ወይ/?

ነገር ግን የማይካደው ሀቅ በኢኮኖሚና በጥቅማጥቅም አሁንም ወለል ላይ ነህ። በአንድ ዓመት ውስጥ ይፈታል ብሎ ማሰብ ግን ከባድ ነው።( የአዲስ አበባ መምህራን ከሆኑት ለተወሰኑት መምህራን በ2009 ዓ.ም. በዝቅተኛ የዋጋ ኪራይ የተሰጠው ኮንዶሚኒየም ሁለተኛው ዙር ‹በቅርብ ይሰጣል› የተባለው የግድ መሰጠት አለበት፡፡ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም። መምህራንን ሺህ ግዜ መሸንገል ማብቃት አለበት! ምክንያቱም የተሰራና ለማጠናቀቂያም 125 ሚሊዩን ብር እንደተመደበለት ከዓመት በፊት በተለያዩ ሚዲያዎች የተገለጸ ስለሆነ ነው።ጥያቄው አዲስ አይደለም።)

መምህራን ስለሀገር ልማት፣ስለፍትህና ርትህ፣ስለፖለቲካ … እንዳያወሩና እንዳያስቡ፤ ሁሉም ስለኢኮኖሚ ችግራቸው ብቻ እንዲያስቡ፤ከዚህ ችግር ለመውጣት ከፈለጉ ደግሞ ከሙያቸው ውጭ ካድሬ እንዲሆኑ በርካታ ስራ ተሰርቷል።ይሄን ▶

> ከሁለት ዓመት በፊት እኮ መምህራን አይደለም ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ ቀርቶ በእስታፋቸው ውስጥ ስለፖለቲካ ሲያወሩ (የሚያወሩት እጅግ ጥቂቶች ነበሩ፡፡ እንዳሁኑ ሁሉም ‹የፖለቲካ ተንታኝ ነኝ› የሚል በፍለጋ ነበር የሚገኘው፡፡

ያላደረጉ ደግሞ ስራቸውን እንዲጠሉና ተስፋ እንዲቆርጡ ተደርጓል፡፡ይሄ ሁሉ ችግር እንዲመጣ ያደረገው የትምህርት ፖሊሲው ችግር፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሀላፊዎች ሆነው ከሚሾሙት እስከ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ድረስ የሚሾሙት አንተን ለመጉዳት (በሞራል እና በጥቅማጥቅም) የፖለቲካ ሹመኞች እንጂ ባለሙያዎች እንዳይሆኑ በመደረጉ ነው፡፡ አብዛኞቹ ማስተማር የሰለቻቸው እና ለማስተማር ብቃት የሌላቸው ናቸው፡፡አሁንም አልተቀየሩም፡፡(እንደውም ለውጡ ያልነካው ብቸኛው ዘርፍ የትምህርት ዘርፉ ነው ማለት ይቻላል፡፡) በእርግጥ በአንድ ግዜ ከቦታቸው ማንሳት አስቸጋሪ ሆኖ ይሆናል፡፡ነገር ግን ዋና ዋና መሪዎቹን በመቀየር ሌሎችንም ማስተካከል ይቻላል፡፡

አሁን ላይ የትምህርት ዘርፉ በተለያዩ ሚንስትሮች እንዲመራ መደረጉ እና የችግሩ ምንጭ የሆነው ፖሊሲው እንዲሻሻል የሚደረገው ጥረት መልካም ጅምር መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ ቢክዱትም አያዋጣም፡፡ የችግሩን ምንጭ መቀየርና መለወጥ ትልቅ ተግባር ነው፡፡የሆነው ሆኖ በመጭው የትምህርት ዘመን የመማሪያ መጽሐፍቶችን መቀየር ባይቻል መዋቅሩን (ስትራክቸሩን)ግን ተቀይሮ የግድ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

የመምህራንን ክብርና ጥቅም ከመግደል ጋር ተያይዞ 70/30 በሚል ፖሊሲ በርካታ የምንድህስና (የኢንጅነሪንግ) ተማሪዎችን በገፍ ካስመረቁ በኋላ ‹ድንጋይ ፍለጡ› በማለትና ሌላ የስራ አማራጭ በማሳጣት፣ድንጋይ ሲፈልጡ በሀገሪቱ የቴሌቪዥን ጣብያ እንደ ትልቅ ተሞክሮ ማሳየት፤ ለታዳጊ ህጻናት ትምህርት እንደማይጠቅም ማስረዳት መሆኑን ስንቶቻችን ተገንዝበነው ነበር? ይህም የመምህራንን ክብር ከማላሸቅ ከጥሎ የምህንድስና ትምህርትን (ገና በጅምር ላይ ባለች ሀገር) ዋጋ ለማሳጣት የተሰራ ሌላው ስራ ነበር፡፡

ከዚህ ስራ ጎን ለጎን ደግሞ ማህበረሰቡና አዲሱ ትውልድ ከትምህርትና ከዕውቀት ይልቅ አቋራጭ መንገድ በመከተል ጥቅም ማግኘትን እንደ ገዢ ሀሳብ በመውሰድ እንዲከተሉት ሆኗል፡፡(ገንዘብ ያለውን ‹አለው ስለተባለ ብቻ› የምናከብርና የምናሽቃብጥ፣የምናጎበድድ ከሆነ፣ ገንዘብ ለሌለው ሰው ክብር የለንም ማለት ነው፡፡ የተከበረውን የሰው ልጅ ከቁሳቁስ ማሳነስ ግን ጤነኝነት ነው!?) ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ የሚዲያ ተቋማት ስራ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡

ዶክተር ፀሐይ ጀምበሩ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን ከአምስት ዓመታት በላይ በፕሬዝዳንትነት በዕውቀትና በታማኝበት መሩት፣ ስለህይወት ታሪካቸው በ2008 ዓ.ም በጻፉት ‹የአንጎሌ ሁካታ (ህይወቴን ልተንትን)› በተሰኘው መጽሐፍቸው ገጽ 300 ላይ ክሌራነስ ፊሽር << The Dictator’s Guide to Education>> written by clarance Fisher. በሚል ርዕስ ከጻፈው አርቲክል ተመስርተው በአንድ ንዑስ አርዕስት ‹ስለትምህርት ለአምባገነኑ መሪ የተግባር መመሪያ› በሚል በአጭሩ ያስቀመጡትን ሀተታ እኔ ለዚህ ጽሁፍ አጋዥ ናቸው ያልኳቸውን ሀሳቦች እጅግ በጥቂቱ እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ፡፡

ገጽ 300፣ “መንግስትህ አገርህን ለመምራት ከደህንነት እና ከመከላከያ በተጨማሪ ትምህርትን ማካሄድ ወሳኝ ተግባርህ ነው፡፡ 301፣ ተጠንቀቅ ጥራት ያለው ዙሪያ አቀፍ ትምህርት ህብረተሰብን ሊቀይር የሚችል አደገኛ ሀይል ነው፡፡ በተገቢው ሁኔታ የተማረ፣ለአዳዲስ ነገሮች ጉጉ የሆነ እና በቴክኖሎጂ አቅም የተላበሰ ህዝብ ለእንዳንተ አይነቱ በስልጣን ረጅም ዘመናት ለመቆየት ለሚፈልግ መሪ አደጋ አለው፡፡የሀገሪቱ ህጻናት ሁሉ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ግዴታ አብጅ፡፡ ህጻናት ከቤት ከዋሉ ከወላጆቻቸው የማይፈለጉ ነገሮችን ሊቀስሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ከወላጆቻቸው በመንጠቅ ማስረጽ የምትፈልጋቸውን ዝንባሌዎችና እሴቶች ማስረጽ ትችላለህ”፡፡ገጽ 302፣ “ትምህርት ቤቶችህ የአገዛዝህን ሀይል እና ጥንካሬህን መግለጽ አለባቸው፡፡”ገጽ 303፣ “ለመላ ሀገሪቱ አንድ አይነት ስርዓተ-ትምህርት አብጅ፡፡የስነ-ጥበብ ትምህርቶች የሰዎችን አስተሳሰብ ስለነጻነት፣ ስለውበት እና ስለራሳቸው ህይወት ስለሚመሩት፣የስነ-ጥበብ ትምህርት ቤቶች እንዳይሰጡ አግድ”፡፡ገጽ 304፣ “ብሄራዊ ስርዓተ-ትምህርትህ በቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር ይፈጸም ዘንድ መምህራኑም ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡በተማሪዎቻቸው ውጤት ተመስርቶ ለመምህራን የድጎማ እና የዕድገት ተስፋዎችን ማቅረብ ይገባል፡፡አገርህ ባጸደቀችው ርዕዮተ ዓለም እና የፖለቲካ መስመር ህጻናቱን ማጥመቅ፡፡”ገጽ 306፣”እጅግ ታማኝና ተነሳሽ የሆኑትን ጥቂቶች መርጠህ በመውሰድ ስለአመራርህ ታላቅነት፣ለህዝብህ ስለ ሰነቅህለት ራዕይ ብሩህነት ወዘተ በተመለከተ በተራዘመና በጠለቀ ሁኔታ አሰልጥናቸው፣ አጥምቃቸው፡፡እነዚህ ርዕሳነ መምህራን፣አማካሪዎች በመሆን ያገልግሉህ፡፡ስለችሎታቸው አትጨነቅ-ምንም ይሁን-ሊያሳስብህ አይገባም፡፡ለመንግስትህ እና ለግቦችህ ፍጹም እና ቅን፣ታማኝ በመሆን ያገለግሉሃል፡፡” የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

> ከመምህራን እና ከምህንድስና ባለሙያዎች ቀጥሎ የሴራው ተቋዳሽ የሆኑት የህክምና ባለሙያዎች ናቸው፡፡በዋናነት ሀኪሞች፡፡በየሰፈሩ አንድ ቪላ ቤት ተከራይተው የህክምና ሳይንስ ኮሌጆች እንደ አሸን እንዲፈሉ ተደረገ


ከመምህራን እና ከምህንድስና ባለሙያዎች ቀጥሎ የሴራው ተቋዳሽ የሆኑት የህክምና ባለሙያዎች ናቸው፡፡በዋናነት ሀኪሞች፡፡በየሰፈሩ አንድ ቪላ ቤት ተከራይተው የህክምና ሳይንስ ኮሌጆች እንደ አሸን እንዲፈሉ ተደረገ፡፡10ኛ እና 12ኛ ክፍል የጨረሱ ተማሪዎች ሞሉት፡፡ታዲያ በገንዘብ ሀይል የተመረቁ ጥቂት ተማሪዎች በሚሰሩት የህክምና ስህተት ምክንያት እድሜ ልካቸውን በማንበብና በማጥናት፣ ከ1-12ኛ ክፍል ድረስ የደረጃ ተማሪ በመሆን፣12ኛ ክፍልን ሲያጠናቅቁ ደግሞ ከፍተኛ ነጥብ በማምጣት የህክምና ትምህርትን መቀላቀል የቻሉ፤ሰባት ዓመታትን አንገታቸውን ደፍተው የተማሩ፣ እንደወጣት የመዝናናትና የመጫወት ስሜታቸውን ገድበው፣በዓላማቸው ጸንተው፣ ትምህርታቸውን በብቃት ተወጥተው ሀኪም የሆኑትን (በነገራችን ላይ በህክምና ትምህርት በህመም ምክንያት ሶስት ሳምንትና አንድ ወር ከትምህርት ገበታቸው ቢርቁ አንድ ዓመት ሊደግሙ ይችላሉ፡፡ይህ ማለት ጎበዝ መሆን ብቻ ሳይሆን ዕድለኝነትም ይጠይቃል፡፡) ተገቢውን ጥቅማጥቅም ቀርቶ የሚመጥናቸውን ክብር እንዳያገኙ ሆኗል፡፡

አንድ ከአስረኛ ክፍል ወደ አስራ አንደኛ ክፍል መዘዋወር (ማለፍ) ያልቻለ(ች) ደረጃውን ካልጠበቀ የግል ኮሌጅ ‹በመመረቅ› የህክምና ስህተት ከፈጠረ(ች) በቃ ምን አለፋችሁ? በሃገሪቱ ያሉ ጎበዝ፣ ታታሪ፣ምስጉንና በሙያቸው አንቱ በተባሉት ሀኪሞች ላይ፤ ትንሹም ትልቁም፣ ከባንክ ፈርሞ ገንዘብ ማውጣት የማይችለው፣ ጋዜጠኛ ነን ተብዬዎች፣ የዐይን ጠብታ ተደርጎለት ሲያበቃ ‹መቼ መቼ ነው የምውጠው?› ብሎ የሚጠይቀው ሁሉ በድፍረት ተሞልቶ ጣቱን ይቀስራል፡፡በዚህም አብዘኛው የማሕበረሰብ ክፍል በሀኪሞች ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረው ሆነ፡፡

ይህ ሁሉ ችግር የመጣው በተሳሳተ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመሆኑ መፍትሄውም ፖሊሲዎችን ማስተካከል ነው፡፡የማስተካከል ስራውም ተጀምሯል፡፡ስራው ስኬታማ እንዲሆን ሁላችንም በመረባረብ እንደግፍ! በድጋፋችን ውስጥ ደግሞ አሁን መመለስ ያለባቸውንና ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን እንጠይቅ፡፡

በመጨረሻ፡- ፋሺስት ኢጣሊያ በድጋሚ በወረረችን ግዜ በመብራት እየፈለገች የተማሩ ሰዎቻችንን ስትገድል የነበረው ለምን ይመስላችኋል!?

# እራቱ እና ከተማዋ



ፍቅርተ ተሾመ



አቧራውን አልፈዋለሁ፤ አሻራዬን አኖራለሁ ታሪኬንም እሰራለሁ:: በማለት በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ መሪነት 300 የአዲስ አበባ ባለሀብቶች አውራ ጣታቸውን በሚመገቡበት ጠረጴዛ ላይ በማኖር አሻራቸውን አኑረዋል:: አዲስ አበባ ከተማን የማስዋቡ ስራ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃላፊነት የወሰዱበት ወሳኝ ስራ መሆኑን አጥብቀው ሲናገሩ ቆይተዋል። ይህንንም አሻራ ለማኖር ወደ ስራ የገቡ ሲሆን የቻይና መንግስት ከተማይቱን የማዘመን እና የማስዋብ ስራ ላይ ያለውን ድርሻ ዲዛይኑን በነፃ ሰርቶ በማስረከብ ዘመቻውን ቀድሶ አስረክቧል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ባላቸው የማስተባበር አቅም እና ተሰጥኦ በተለያዩ አካላት ገቢውን እንደሚያሸፍኑ አስረግጠው በተናገሩት መሰረት የሃገር ውስጥ እና የተለያዩ አለምአቀፍ ድርጅቶችን እና ተቋማትን መንግስታትና ግለሰቦችን በማስተባበር ወጪውን ለማሸፈን ጥረት ጀምረዋል። በዚህም ላይ ተንተርሶ የሃገር ውስጥ ባለሀብቶች የባለቤትነት ስሜቱን ከኛው ከኢትዮጵያዊያን እጅ ወጥቶ በሌሎች እጅ እንዳይሆን በሚል የተሳትፎ ጥሪ ባደረጉት መሰረት 5ሚሊዮን ብራቸውን ቸረው አለንልሽ ሸገር ብለዋል። አሻራቸውንም በቃል እና በገንዘብ አስደግፈው እሁድ ምሽት በእራት መርሃ ግብሩ አኑረዋል። ንፁህና የዘመነ ሁኔታ በሌለበት አከባቢ ውስጥ ሆኖ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ የስራ ፍላጎት እና ተጠያቂነትንም መፍጠር አዳጋች መሆኑን በፅኑ እንደሚያምኑ በተደጋጋሚ የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አያይዘውም እየሰሩ ያሉበት ሌላኛው በአዲስ አበባ የተያዘውን እቅድ፤ ቤተመንግስቱን የማስዋብ ስራ ላይ የመጠመዳቸው ጉዳይ ነው። የምኒልኩ ቤት የገቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ  በስራ በጣም የተጠመዱት የወረሱትን የመንግስቱን ቤት ብቻ ሳይሆን የወራሹን ግብር በሚመስል መልኩ ጠዋቱን 27 አመት የቆሸሸውን ከተማ እና ቤተ መንግስት በማስዋብ ስራ ላይ ጠዋቱን አሳልፈው ከዓመሻሹ እንግዶቻቸውን ተቀብለዋል።

ይህችን ለከተማነት ያጩዋትና ከተማነትዋን የፀነሱት የአጤ ምኒልክ አካል እቴጌ ጣይቱ ይህን ማዕረግ ቀድመው በስያሜዋ የተነበዩላት የምትመስለው አዲስ አበባ፤ "በዚህ ታሪካዊ ቦታ ታሪክ ለመሥራት የተሰበሰባችሁ፣ ክቡራትና ክቡራን፤ ዛሬ ለእናንተ የማነሳው አንድ ጉዳይ አለኝ። ስለ አቧራና አሻራ ጉዳይ። በትውልድ ጉዞ ውስጥ አቧራ ያነሡም፣ አሻራ ያተሙም ሰዎች ነበሩ፣ አሉ።" በማለት ወደ ፍሬ ንግግራቸው የገቡት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በታሪክ ወደ ኃላ መልሰው ታሪካቸውን ማሰናሰልን መርጠዋል። የአድዋው ጦርነት መነሻው ከዚህቹ ታሪከኛ ከተማ አዲስ አበባ ነበር። ወደ ኃላ ከመለሱን አይቀር ምኒልክ ወደ በተመሳሳይ አውድ እንቃኝ። አፄ ምኒልክ ወደ ዘመቻ ከመሄዳቸው በፊት ቀደም ብለው ከሙሴ ሽፍኔ ጋር በተለዋወጡት ደብዳቤ ውስጥ የተቀመጠችውን ተመሳሳይ የሃሳብ ልዕልናቸውን የሚያሳይ መልዕክት በአጤ ምኒሊክ መፅሃፍ እንዲህ ተቀንጭቦ ተቀምጧል። "... በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አረግኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም..."በማለት ሰዎችን ያውም በእምነት የሚመስሏቸውን መርታታቸውን እንደ ስኬት ባያዩትም ... እግዚአብሔር የወሰነልንን የባህር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬን ክብት ማለቅ የሰዉን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም ▶

እስካሁን አላስቀየምኸኝም።...” በማለት መደፈርን እንደማይፈቅዱ ነጋሪት አስጎስመው መለከቱንም አስነፍተው ከዚህችው አዲስ አበባ ከተማ ተነስተው ያንን ታሪካዊ አሻራ ፤ አድዋን ጥለው አልፈዋል። ጠቅላዩም ይህንን አሻራ ከታሪክ ጋር በማሰናሰል ዘመቻውን በአዲስ አበባ ሀ... ብለው መጀመራቸውን አሻራቸውን ከባለጊዜ በጎ ዘማች ፊታውራሪዎች ጋር ቃል ተገባብተው አውጀዋል።

አቧራ ለብሶ የኖረውን መለከት ከነፊው አፍ፤ ነጋሪቱን ከመቺው ጋር አገናኝተው በአዋጅ የተጠሩትን እንግዶች በወረሱት የንጉሡ ግብር ቤት በራፍ ቆመው መቀበላቸውን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፅ/ቤት እወቁልኝ ሲል በማህበራዊ መረቡ የእለቱን መልዕክት አዘምኗል። አጼ ምኒልክ ወደ አድዋ በዘመቱበት ወቅት የውጫሌውን ውል ያጣመመው አንቶሌኒ የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ከኢጣሊያ ጎን እንዲሰለፉ ማስከዳቱን ባስተናገዱበት መጠን ከአጼው ጋር ተጣልተው ሸፍተው የነበሩት ደጃዝማች ጓንጉል ከእርስዎ ተጣልቼ መሸፈቴ ቢታወቅም አሁን ግን የጋራ ጠላታችንን ከእርስዎ ከጌታዬ አጠገብዎ ሆኜ እንድዋጋ ምህረት አድርገው ይፍቀዱልኝ በማለት ህዝቡን እና ሰራዊቱን ያስደነቁ ጀግኖችንም በፍቅር ተቀብለው አስተናግደዋል። እንዲያው መርገጥ እና መረጋገጥ የሚበቃው አቧራ ከመቡነኑ አገሩን ሁሉ ስለሚያዳርስ በቀላሉ ለአይን ይታያል ሆኖም መዘዙም ብዙም ሳይዘገይ አብሮ ይመጣል የሚሉት ጠቅላዩ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ መጨረሻቸው ብዙም ሳይቆዩ ድል ሆነው ሚስትና ልጆቻቸውን ይዘው ከገዛ ሀገራቸው በማምለጣቸው እይታቸውን የጋረደውን አቧራ ውጤት ማሳያ ነው።

በዚያው ዘመን የጣሊያንን ፕሮፖጋንዳ እና ማለያየት ያሸበራቸው እና ተስፋቸው አልታይ ያላቸው መኳንንት የኢጣሊን ገናናት እና የጦር መሣሪያ ዘመናዊነት በመተንተን የጠላትን መደራደርያ እንቀበል የሚሉዋቸው መኳንንት ነበሩ። ልክ እንደአሁኑ ረባሾቹ አቧራውን በያለበት እያቦነኑ የስልጣን የፖለቲካ የበላይነት፣ የደጋፊ እና የአጀቡ ግርግር ብቻ አላማ ያደረጉ የሃሳብ ልዕልና ሳይሆን ጊዜያዊ ጥቅሞች እና አሻራ የሌለው ታሪክ በመስራት እንደተመጠዱት።

ምኒልክም መኳንንቱን ሰብስበው ... “አንፍራ። እኔ እንደሆንሁ መዘመቴን አልተውምና ስለ ኢጣሊያ ዘመናዊ መሣሪያና ገናነት እንገሩኝ” ኃይል የእግዚአብሔር ነውና እጋጠማለሁ። ብትዘምቱም ብትቀሩም ሬሣዬን ከሥር ሜዳ ፈልጉት። ጠላትን በኃላ አስቀምጦ መዝመት አይችልምና በየግዛታችሁ ያሉትን ኢጣሊያኖች አባሩ...” ብለው አዘዙ። በአንድ ሃገር ውስጥ የተከማቸ ታላቅ ሀብት ምሥጢሩ ደማቅ አሻራ አብዝቶ በመስጠት እንጂ በመቀበል የሚገኝ ፍሬ አይደለም። የጋራ ቤትን ተባብሮ ለመሥራት በቆረጥን ጊዜ ሁሉ በአብሮነትም በጋራ ለመቆም በተነሣን ጊዜ ድል ከፊትችን ትቀርባለች። አናሸንፋለን እንጂ ሽንፈት አጠገባችን አይቀርብም። በማለት የጠቢቡን ሰው ንግርት ጠቅሰው “መልካም ሥራ የመከወኛ ጊዜዋ ትናንት ነው... ጊዜ የለም” ዘመቻውን ይፍጠር መልዕክታቸውን በግብር ጊዜ አስተላልፈዋል።

ምኒልክ የየእለቱን ግብር በጧቱ 3 ሰዓት ይጀምራሉ ለምን ያሉ እንደሆነ ቤቱ የሚያስተናግደው በየቀኑ 3 ሺህ ያህል ሰዎችን በመሆኑ ነው። የምኒልክን ግብር ቤት ልዩ የሚያረገው በሰልፉ ቅድሚያውንን የሚወስዱት ድሆች በመሆናቸው ነው። አበላላቸውንም እንደቀደመው ጊዜ በሽሚያ ሳይሆን ሥርዓት ተበጅቶ ለእያንዳንዱ በአግባቡ እንዲዳረስ አድርገው ነበር። በማለት የታሪክ መፃሕፍት ያትታሉ። “ቀድሞም ጠቢቡ ነበር ሰለሞን አባቱ ምኒልክ ይበልጣል ሰው ይዞ መብላቱ” ተብሎም ተገጥሞላቸዋል።

የእሁዱ እራት በ5 ሚሊዮን ብር ተበልቷል። ይሄ የእራቱ ዋጋ እንዳይደለ የገለፁት ጠቅላዩ ድሆች በልተው ሊኖሩባት ላስቻለችው ስትፈልጋቸው ሲፈልጓት ለተራራቁት በሁለት ፅንፍ ላይ ሆነው የተሰደዱ ዜጎቿን የመሰብሰቢያ ግብር መሆኑን አሳውቀዋል።

## አዲስ አበባና ውሃዎቿ

አዲስ አበባ የምትፀዳው ወንዞቿን ተተርሳ ሲሆን ይህም የተለያዩ የአለም ሃገራትን ተሞክሮ በመውሰድ ነው። አዲስ አበባ በውስጧ የሚያልፉት ውሃዎች ድንቅ የቱሪስት መስህብ ከመሆን ባሻገር የከተማዋ የንፅህና እና የውበት ገፅታዎቿ ናቸው። አብዛኞቹ የአውሮፓ ከተሞች ለወንዞቻቸው ትልቅ ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆን አንዳንዶቹ እንደውም ከተሞቻቸውን በወንዞች ላይ መሰረት አድርገው መስርተዋል።

አዲስ አበባ ካላት የበዛ ቆሻሻ አንፃር ተመጣጣኝ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት የላትም። 25% የሚሆነው የከተማው ነዋሪ ሽንት ቤት የሌለው በመሆኑ ወንዞቹን እንደ ሽንት ቤት ይጠቀማቸዋል። ሽንት ቤት ተጠቃሚ ናቸው ተብለው የሚታመኑትም ነዋሪዎች ወንዞቹን እንደ ሽንት ቤት ይጠቀምባቸዋል። ሽንት ቤት ተጠቃሚ የሚባሉትም ቢሆኑ ከመኖሪያ ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚለቁት ፈሳሽ ቆሻሻ በከተማው ውስጥ ያሉት ወንዞች ተበክለዋል።

በአዲስ አበባ እና አከባቢዎቿ ያሉ ውሃዎች እና ወንዞች ብክለት እና የመፍትሔ ድርጊቶች ላይ በተሰራ አንድ ጥናት በኢትዮጵያ ካሉት የወንዝ ተፋሰሶች አንዱ አቃቂ ወንዝ ነው። ይህ ወንዝ ከአዲስ አበባ ከተማ የሚነሱ በርካታ ተፋሰሶች አሉት። ከነዚኅም እነፊንጫ፣ ቀበና እና ቡልቡላ ይገኙበታል። የአቃቂ ወንዝ ሁለት መነሻዎች አሉት። ትንሹ አቃቂ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን ከወጨጫ ተራራ ተነስቶ ሰሜኑን ይዞ ይሄዳል። ትልቁ አቃቂ ደግሞ ከምስራቁ አዲስ አበባ እንጦጦ ይነሳና ወደ አባ ሳሙኤል ገንዳ ያመራል። የአቃቂ ወንዝ በከተማው ከተበከሉ ወንዞች ሁሉ በብክለት መጠኑ በጣም ከፍተኛ ነው። ከትልቁ አቃቂ ይልቅም ደግሞ ትንሹ ይበልጡን የተበከለ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል።

በኢትዮጵያ ካለው የሰዎች ቁጥር መጨመር፣ ተመጣጣኝ የሆነ የንፅህና መጠበቂ ግንባታዎች አለመኖር እና የከተሜነት መስፋፋቱ የታቀደበት ባለመሆኑ አደገኛ የሆነ የውሃዎች ጥራት ችግር እንዳስከተ ማየት ተችሏል። በአቃቂ ወንዝ ዙሪያ መኖሪያዎች፣ የፋብሪካዎች እና ተመሳሳይ ህገወጥ ሰፈራዎች ተካሂደዋል። ቀበና ለአዋሽ አንዱ ገባር ሲሆን ምንም እንኳን ከአዋሽ አንፃር የብክለት መጠኑ አነስተኛ ቢሆንም የተቋማትና የነዋሪዎች፣ የግብርና እና የንግድ አካላት ፍሳሽ ቀበናን ይበክሉታል። ቀበና ወንዝም ይሁን ሌሎቹ ወንዞች ለከተማው የነበራቸውን ግርማ ማህበራዊ ፋይዳ የሚያውቁት የዛሬ 10 አመት እና ከዚያ በፊት በውስጡ ለመዋኘት የበቁት ናቸው።

ቡልቡላም ሌላኛው እንዲሁ ከተማው አቋርጦ የሚንገዋለል ወንዝ ነው። ፈርዶበት በመንገዱ የመኖሪያ ቤቶቹ፣ የህንፃ ግንባታዎች፣ የጋራጆች፣ የሆስፒታሎችን እና የብረት መሳሪያዎች ፋብሪካ ዝቃጮች ይመርዙታል።

ፊንጫ ወንዝ ደግሞ በረፒ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን ይሄንንም ከተለያዩ አካላት የሚወጡ ፍሳሾች ይበርዙታል። የመኖሪያ ቤቶች፣ አገልግሎት ሰጨዎችና ጥቃቅን አምራቾችም እንዲሁ ለመበከሉ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ከመኖሪያ ቤቶች በተለይ ደግሞ ሽንት ቤቶቻቸው በቀጥታ ከወንዙ ጋር ማገናኘታቸው ወንዙ በጊዜ ሂደት ከጥቅም ውጪ አድርጎታል።

ምንም እንኳን ኢንደስቱሪዎች የልማት አካል ሆነው የህብረተሰብን ህይወት ማላቅ እና ማሻሻል አላማው እንደሆነ ቢነገርም ቅሉ ባለፈው 10 እና 11 ዓመት ትልቅ የጤና እክል ፈጣሪ ሆነዋል። ከ65% በላይ የሚሆነው የሀገሪቷ ኢንደስቱሪዎች የሚገኙት በአዲስ አበባ ከተማ ነው።ዩኔስኮ በሰራው ጥናት አፍሪካ በውሃዎቿ መበከል እና ንፅህና ማጣት ምክንያት በጠቅላላ ጂዲፒው ላይ በ5% ተፅዕኖ ያሳድራል። የተደረገው ጥናት እንደሚጠቁመውም ውሃዎችን ለአገልግሎት ማዋል ወጪው ከፍተኛ ሲሆን ይህ ደግሞ ጥራትና መጠኑን ይቀንሰዋል።

አውሮፓውያን ሀገራት ከተሞቻቸው ከወንዞች ጋር ስራዬ ብለው ያቆራኙት ወንዞች የከተሞች በቱሪስት መስህብ ከመሆናቸው ባሻገር ተያያዥ የኢኮኖሚ ማህበራዊና የሀገር ገፅታ ግንባታ ሚናቸው ይህ ነው የማይባል በመሆኑ ነው።

ዛሬ እዚህ የተገናኘነው ለአባቶቻችን ክብር እና ለልጆቻችን ፍቅር ስንል ሁላችንም ለምንወዳት ቤታችን፤ የኢትዮጵያውያን የወል ካስማ የታላቂቱ አፍሪካ ዋና ከተማ እና የብዙ ታሪካችን ማማ ለሆነችው ለአዲስ አበባ አደይ አበባዋን እንመልስላት ዘንድ ነው። በማለት ከታሪክ ተወቃሽነት ትውልዱ ራሱ ያበላሸውን በራሱ አስተካክሎ እንዲስረክብ ጥሪያቸውን አቅርበዋል። ይህ የወንዞች መጽዳት ብቻ ሳይሆን ሃገር ጠብቆ ሲሆንም አልቆ ገንብቶ ለትውልድ የማስተላለፍ ጥሪ ነው።



ደረጀ ደምሴ ቡልቱ

# የጀነራል ደምሴ ቡልቶና የምርጦቹ አዋጊዎች መጨረሻ

## ከ30 አመት በኋላ ሲታሰብ!

የዛሬ ሰላሳ ዓመት ከሰዓት በኂላ ግንቦት 8 ቀን የኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ ጄቶችና ሔሊኮፕተሮች በአዲስ አበባ አየር ላይ ባለተለመደ ዝቅታ በአስደንጋጭ ድምጽ ሲያፈተልኩና ሲያንዣብቡ ገና የሐያ ዓመት ወጣት ነበርኩ።

ማንም ሳይነግረኝ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እየተደረገ መሆኑን በመገመት ወደ ቤት አመራሁ።ብዙም ሳይቆይ የአባቴ አጃቢ የነበሩ ወታደሮች ከሌሎች ሁለት ወታደሮች ጋር በመሆን ቤታችን ፊት ለፊት እነሱን ለማውረድ ከቆመው የከባድ የጭነት መኪና ወርደው የግቢውን በር አንኳኳኩ። የጭነቱ መኪና ፊቱን ወደመጣበት፣ የቦሌ መንገድ እዙሮ ከጀርባ የታጨቁትን ወታደሮች ይዞ መንገዱን ጀመረ።

ከጭነት መኪናው ለወረዱት ወታደሮች በሩን የከፈትኩላቸው እኔ ነበርኩ። ሙሉ ትጥቅ ታጥቀዋል። የአባቴ አጃቢ ከነበረው የአስር አለቃ ጌታቸው ጋር ሰላምታ ተለዋውጠን፣ ወደ ውስጥ እንዲገቡ ጋብዝኳቸው። ከአስመራ በአውሮፕላን ከብዙ ወታደሮች ጋር እንደመጡና እኛ ቤት ወርደው ጥበቃ እንዲያደርጉ በአባቴ መታዘዛቸውን ነገረኝ።

ከእርሱ ጋር ያሉት የማላውቃቸው ሁለቱ ወታደሮች የጄኔራል ሁሴን አህመድ አጃቢዎች አንደሆኑና እነሱም እንዲሁ እኛ ቤት እንዲቆዩ መታዛዛቸውን አስረዳኝ። አውሮፕላን ወስጥ እያሉ ጄኔራል ቁምላቸው መንግስቱ ኃይለማርያም ተገድሎ ከስልጣን እንደ ወረደ የሚገልጽ ወረቀት ማደላቸውን ሲነግረኝ የገመትነው ዕውነት መሆኑን አረጋገጥን።

ሁኔታው እስኪጣራ ድረስ እቤት ከመቀመጥ ወደ ማይጠረጠር ወዳጅ ቤት መሄድን መርጠን እቤት የነበረውን መሣሪያ ተከፋፍለን ቤታችንን ለቀን ወጣን። ታላቅ ወንድሜ ዮናስ ብሄራዊ ውትድርና አንደኛ ዙር ሄዶ ለሁለት አመት ተኩል ያገለገለ ነበር። ስለመሳሪያ አጠቃቀም ያውቃል። እኔ ደግሞ አባቴ በሚመራው የጦር ሰፈር በየመሳሪያ ግምጃ ቤቱ ጥይት በካርታ እንደጨዋታ ስሞላ፣ ክላሽንኮቭ መትረየስ እየፈታሁ እየገጠምኩ ስላደግሁ በደረሰኝ ለአባቴ በስጦታ የተሰጠ የጀርመን ሉጋር ሽጉጥ ቢያንስ አነጣጥሬ መተኮስ እንደምችል አልተጠራጠርኩም።



የመፈንቀለ መንግስቱ ሙከራ ከመጀመሩ መክሸፉን ማታ ብንሰማም ከአስመራ የሚተላለፈው ዜና ደግሞ ሙከራው እየቀጠለ መሆኑን ነበር የሚገልጸው። አባቴ ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ የሚመራውን የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አስፈላጊ ከሆነ አዲስ አበባ ድረስ በከፊል በማምጣት ሙከራውን እስከመጨረሻው እንደሚገፋበት በአስመራ ሬዲዮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መልዕክት አስተላለፈ።

ለሶስት ቀናት የተለያዩ ክፍሎች ሙከራውን እንዲደግፉ ለማስተባበር ሞከረ። አስመራ የተደራጀ የአየር ሃይልና የኢትዮጵየ አየር መንገድ አውሮፕላኖች የሚገኙበት ስለነበረ ሁኔታው ካልተሳካ አገሩን ለቆ ይሄዳል የሚል ተስፋ ነበረን። የቤተሰብ ተስፋ። አባቴ ግን ያስተባበራቸውን የጦር ጓዶቹንና የሚወደውን አገሩን ጥሎ እንደማይሄድ ልባችን ያውቅ ነበር። እጁን አንደማይሰጥ ደግሞ ግልጽ ነበር። “አንድ የጦር መኮንን የጄኔራል ማዕረግ ከደረሰ እጁን ለጠላት መስጠት አገርመማዋረድ ነው ፣ ከቻለ ራሱን ማጥፋት አለበት ይል ነበር።”

ይህን ደግሞ ብዙ የቀድሞ የጦር መኮንኖች የሚያምኑበት ነው። ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ፣ ጄኔራል አምሐ ደስታ በመፈንቅለ መንግስቱ በአዲስ አበባ ራሳቸውን በመሰዋት፣ ጄኔራል ለገሠ አበጀ በትግራይ ፣ኮሎኔል ካሳ ገብረማርያም በናቅፋ፣ ጀ/ል ተሾመ ተሰማ በምጽዋ ራሳቸውን መስዋእት በማድረግ ያለፉትን ነፍሳቸው ያለችበት ቦታ ስትሄዱ ጠይቁ።

ስለ መፈንቅለ መንግስት ሙከራው “አባቴ ያችን ሰዓት” በተሰኘው መጽሃፌ ዝርዝሩን ስለጻፍኩ እዚህ መድገም አልፈልግም። ከሰላሳ አመት በኂላ ማስታወስ ያለብን ሙከራውን ብቻ ሳይሆን በዛ ሙከራ ላይ የተሳተፉት የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ለአገራቸው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ፣ የከፈለኡትን መስዋእትነትና ከእነሱ ህይወት ይህ ትውልድ ሊቀስም የሚችለውን ትምህርት ነው። የመፈንቅለ መንግስቱን ሙከራ ከሰላሳ አመታት በኂ ሳስበው ጊዜው ምን ያህል እንደተቀየረና አገራችን ምን ያህል እንደተለወጠች አስተዋልኩ። አባቴና ጓደኞቹን የሚያስተሳስራቸው ለአገራቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነበራቸው ፍቅር ነበር። ▶

መንግስቱ ኃይለ ማርያም በፍርሃት ከመኮብለሉ ሁለት አመት በፊት ጀምሮ ከዛም በኂላ ለ27 አመት የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ስላደረጉት የጦር መሪዎች የተለያየ ውሸት ተነግሯል፡፡ ተጽፏልም፡፡ ዕውነቱን የሚያውቀው ብዙ ስለነበር ታሪካቸው አንዳንዶች እንደተፈለገው አልጎደፈም፡፡የመንግስቱ ኃይለማርያም ደጋፊና ተቆርቋሪ የሆኑ አንዳንድ ካድሬዎችና የወታደራዊ ደሕንነት አባላት ይህን ነው ለማድረግ የሞከሩት፡፡ ሁሉም አይደሉም ከመካከላቸው ዕውነቱን የጻፉ አሉ፡፡ “ትውልድ ያናወጠ ጦርነት “ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል፡፡

እነዚህን አንጋፋ የጦር መሪዎች እንደ ግል ጥቅም ወይም ስልጣን ፈላጊ፣ ከዛም አልፎ አልፎ አሻጥር እየሰሩ ጦሩን ሲያስጨርሱ እንደነበር አድርገው ሲጽፉ፡፡ ሌት ተቀን ስለ አገሩ ሲጨነቅና ሲቆረቆር ቢበዛ 4 ወይም 5 ሰዓት ብቻ እየተኛ ሌሊት ተነስቶ ወደ ተረኛ መኮንኖች ጋር እየደወለ የሰጠው ትዕዛዝ መፈጸሙን ሲከታተል የሚያነጋ ፣ ጦሩ ድል ሲያደርግ በደስታ የሚሞላ፣ጦሩ ችግር ሲገጥመውና ጓዶቹ ሲሰዉ በሐዘን የሚዘፈቀውን አባቴን እያስታወስኩ የእነዚያን ጀግኖች ታሪክ በወረፉ ዕጃቸውን ለወያኔዎች እየሰጡ ህይወታቸውን ባተረፉ ሰዎች እጅ ሲጎድፍ ሳይ ከማዘንም አልፎ ያበሳጨኛል፡፡

የኔ አባት ለ 38 አመታት አገሩን አገልግሏል፡፡ ኮርያ ዘምቷል፡፡ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ አየር ወለድ ጦር ካቋቋሙት ጥቂት መኮንኖች አንዱ ነው፡፡ ገና በአጼ ሃይለ ስላሴ ዘመን ሶማሊያ ኢትዮጵያን ስትወር በመጀመሪያው የኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት፣ በቶጎ ውጫሌ ጦርነት የአየር ወለዱን ጦር መርቶ ድል አድርጓል፡፡ ከዚያ በባሌ ዘመቻ በሌ/ጄነራል ጃጋማ ኬሎ ስር የአየር ወለድ ጦር መርቶ ተዋግቷል፡፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የወታደራዊ ትምሕርት ዳሬክተር ሆኖ በታወቀው የሐረር ጦር አካዳሚ ብዙ ምርጥ መኮንኖችን አፍርቷል፡፡ በ1970 የሶማሌ ጦር አዋሳ ለመድረስ 60 ኪሎሜትር ሲቀረው የደቡብ ዕዝ አዛዥ ሆኖ እንደ አንድ የመስመር ጦር መሪ ከጦሩ ጋር አብሮ እየተዋጋ የሶማሌ ጦር ከኢትዮጵያ ምድር እስከሚወጣ ድረስ ጦሩን መርቷል፡፡ የአባቴን የግል ማህደር እልፎ አልፎ እያነሳሁ አነባለሁ፡፡ በየቀኑ የሚያደርገውን ይጽፍ ነበር፡፡ ከ1000 ገጽ በላይ የሚሆን ማህደሩን በኮምፒውተር ስካን አሰደርጌ አስቀምጫለሁ፡፡ ለምሳሌ በኤርትራ ስለተደረገው የባህረ ነጋሽ ዘምቻ የጻፈውን ከመጽሃፌ ግርጌ አስገብቼ ነበር፡፡

ከታች የተቀመጠው በደቡብ ኢትዮጵያ ፊሉቱና ዶሎን ለማስለቀቅ የተደረገውን የሶስት ቀን ጦርነት የሚገልጽ ነው፡፡ የጀግናው የኢትዮጵያ አየር ሃይል ጄት አብራሪ የጀ/ል ለገሰ ተፈራ ጄት ተመቶ የወደቀው በዚህ ጦርነት ላይ ነበር፡፡ የግል ማህደሩ ከ400 በላይ ጸረ ታንክና ጸረ ሰው ፈንጂ እያነሱ ወደፊት ተጉዘው የሶማሊያን ወራሪ ጦር እንደደመሰሱ ያሳያል፡፡

ከሁሉ የገረመኝ ጽሁፉ ይህኛው ነው፡፡ “ በ 3/7/70- 08.00 ሰአት ከዶሎ 17 ኪ/ሜትር ላይ ዋናው ጦር እንዲቆም ተደርጎ በአንድ ሻምበል ጦር (ወደ 400 የሰው ሃይል) ወደ ዶሎ ተነቃንቆ ዶሎ ከተማ ስንደርስ የሶማሌ ወታደር ከቀድሞው የጦር ሰፈራችን በመኪና ለማምለጥ ሲበር ተከታትለን ከነመኪናው ማርክን ሌሎችም 5 ወታደሮች ተታኩሰው ወደ ጫካ ስለገቡ መደምሰስ አልተቻለም” ይላል፡፡

ከዚያ በኂላ ወደ ሐረር የምስራቅ ዕዝ አዛዥ ሆኖ በመሄድ የሶማሌን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር በጠቅላላ ያስወጣውን ዘመቻ መርቶ ድልን ተጎናጽፏል፡፡በመጨረሻም በኤርትራ ከረን ሊያዝ ሲል በአዛዥነት ተመድቦ የኢትዮጵያ ጦር ከረንን ተከላክሎ መልሶ በማጥቃት ወደ “አፋ ቤት” እንዲያመራ በማድረግ የነበረውን ሁኔታ ለመቀየር ችሎ ነበር፡፡

በተጨማሪም ሁለት የተቀነባበሩ ዘመቻዎችን ከሐረር በጊዜያዊ ምድባ ወደ ኤርትራ ተጉዞ በዘመቻ መሪነት አገልግሏል ፡፡ እነዚህ ሁለት ዘመቻዎች “የቀይ ባሕርና የባሕረ ነጋሽ ዘመቻ” የሚባሉ ባሬንቱን ከማስለቀቅ ባሻገር ናቅፋን ለመያዝ የተቃረቡበት ዘመቻዎች ነበሩ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አገሪቱ የነበረችበት አዘቅት በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ፖሊሲ ምክንያት የተፈጠሩ ብዙ ችግሮች በጣም ያሳስቡትና ያስጨንቁት ነበር፡፡ የፖሊሲ ለውጥ እንዲደረግ በተደጋጋሚ የሚቻለውን አድርጓል፡፡ ከቅርብ ጓደኛውና ከትግል አጋሩ ከጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ጋር ስለአገሪቱና ስለምትከተለው ፖሊሲ ብዙ ይወያዩ ነበር፡፡ የማይስማሙበት ፖሊሲ ብዙ ነበር፡፡ ለምሳሌ የሰፈራ ፖሊሲ፣ በሚሊተሪውና በሕዝቡ መሐል ብዙ ቅሬታን ፈጥሮ ነበር፡፡ በኤርትራና በትግራይ የሚደረጉት ጦርነቶች የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት በማጥፋት አገሪቱ ላይ ያመጣው ቀውስ እንቅልፍ ይነሳቸው ነበር፡፡

የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ውድቀት ለሰራዊቱ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ፣ ከምግብ ፣ ከውሃ ጀምሮ በተገቢው ማቅረብ አለመቻሉ ያበሳጫቸው ነበር፡፡ የሚሰማ መሪ ባለመኖሩ መፍትሄ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ጄኔራል ፋንታ ከታሰሩ በኂላ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተቀዳው ቃለ መጠይቅ መንግስቱ ኃይለማርያም ከሸሸ በኂላ ለህዝብ ተለቆ ነበር፡፡ እሳቸው እንዳሉት የመፈንቅለ መንግስቱ ዓላማ ለጦርነቱ መፍትሔ ለመስጠት “ከወንበዴው ጋር ጭምር በጠረጴዛ ዙርያ ለመነጋገር ነበር”፡፡ ታዲያ አሁን አንዳንዶች ሲጽፉ ለስልጣን ብለው ነው ሲሉ ይገርመኛል፡፡ ለመሆኑ ስንቱ ናቸው ሰልጣን የሚይዙት? የአገር መሪ የሚሆነው አንድ ሰው ነው፡፡ ከአስመራ ብቻ ከ 20 በላይ የሚሆኑ ጄኔራሎች ተሳትፈዋል፡፡ አዲስ አበባም እንዲሁ፡፡ መፈንቅለ መንግስት ያክል ለሕይወት ተቆርጦ የሚገባበት ሙከራ በእነዚህ ሰዎች ሁሉ ስምምነት ሲደረግ እንዴት ለስልጣን ነው ይባላል? ስልጣን ደግሞ ነበራቸው፡፡ እንዳልኩት ከአንድ ወይም ከሁለት ሰዎች ሌላ የቀሩት ከነበራቸው ስልጣን የሚጨምሩት ብዙም አልነበረም፡፡ ስልጣን መጨመር ከሆነ ዓላማው ለመንግስቱ ኂይለ ማርያም እያጎበደዱ ስልጣን መጨመር ይቀል ነበር፡፡ እዚህ ላይ መንግስቱ ኃ/ማርያምን ለምን በአክብሮት አንቱ እያልኩ እንደማልጽፍ ትንሽ ላስረዳ፡፡ በመጀመሪያ በታሪክ የተወሰኑ ግለሰቦች ሲነሱ አንተ ተብለው የሚጠሩ አሉ፡፡ የሰሩት አጸያፊ እና ጭካኔ የተሞላባቸው ተግባራት ምክንያት፡፡ ለምሳሌ ሙሶሎኒ፣ ሂትለር፣ ግራኝ አህመድ፣ በታሪክ ሲነሱ በእድሜም ይሁን በስራ የሚገኝ ከበሬታ አይሰጣቸውም፡፡

አንዳንድ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ደጋፊዎች ከ29 አመት በኂላም በአገራችን ላይ ያደረሰውን ጥፋት ረስተው ይሁን ወይንም ኣውቀው ለመሸፈን የሚናገሩትን ስሰማ ይገርመኛል፡፡ መንግስቱ ኃ/ማርያም አገራችን አሁን ለደረሰችበት ቀውስ ዋነኛ ተጠያቂ ግለሰብ ነው፡፡ በሀገራችን ታሪክ አገሪቷን ወደ ተሻለና ትልቅ ደረጃ እንዳትደርስ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱ ግለሰቦች መካከል በዋናነኝነት የሚመደብ ግለሰብ ነው፡፡ እውቆ አደረገው ለማለት ባይቻልም፡፡ አገር ለማጥፋት ሆን ብሎ አውቆ አደረገው አልልም፡፡ ያደረሰው ጥፋት በአብዛኛው የኢትዮጵያን የሩቅ ዘመን ጥቅም ማየት አለመቻሉ፣ የሚወስነው ውሳኔ ከአገሪቷ የሩቅ ዘመን ጥቅም ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን የራሱን ስልጣን ማጠናከር እና ማደላደል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ገና ሲጀመር የታሪክ ቅርጽ የሆኑትን፣ እሱ እንደገና ቢፈጠር የማይመጥናቸውን፣ እንደ ጸሃፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ እና ልጅ እንዳልካቸው መኮንን የመሳሰሉቱን ኢትዮጵያውያን ያለፍርድ በግፍ የገደለው፡፡ ከዚያም እነ ጀ/ል ተፈሪ ባንቲን የወደፊት የአገሪቷን ጥቅም በማየት ከተቃዋሚ ድርጅቶች ኢህአፓንም ጨምሮ እንወያይ ሲሉ በተቀነባበረ መንገድ ገደላቸው፡፡ ጀ/ል አማን አንዶም የኤርትራን ችግር ለመፍታት መንገድ ሲፈልጉ አርቆ ማስተዋል ስለተሳነው ገደላቸው፡፡ ደጋግሜ እንደተናገርኩት በእኔ ቆጠራ ብቻ 54 ጀነራሎችን ገድሎአል፡፡ ከሁሉ የሚያሳዝነው በመፈንቅለ መንግስቱ በመጨረሻው ደቂቃ ተስማምተው ተሳትፈዋል ተብለው የተከሰሱትን 18 ምርጥ ጀነራሎች ከአንድ አመት እስር በኂላ አገራቸውን እንዲያገለግሉ ከማድረግ ይልቅ በግፍ ገድሏቸዋል፡፡ ከኤርትራ ብቻ 435 መኮንኖችን እስር ቤት ወርውሮ ጦሩ ያለብቁ የስትራቴጂክና የፊልድ መሪዎች እርቃኑን እንዲጋለጥ አድርጎአል፡፡ ይህ በጦሩ ውስጥ ያደረገው በከፊል ነው፡፡

ሲቪሉን ህዝብ ደግሞ በሰፈራ፣ በብሄራዊ ውትድርና፣ በጸረ አብዮተኛነት፣ ውንጀላ ወዘተ ሲያጉላላና ሲያሰቃይ፣ ለ17 እመት በሰአት እላፊ ገደብ ህዝቡን ሲያሰቃይ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመቃወም መብቶች ተነፍጎ ይህ ሁሉ አልበቃ ሲለው የመንግስት ሰራተኛ የሚለብሰው ልብስ በሰሜን ኮሪያ ሞዴል የተሰራ ስማያዊ ካኪና የካኪ ቀለም ያለው በጣም የሚያስቀይም ጃኬትና ሱሪ እንዲሆን አዞ፣ ህዝብን መሳቂያ ያደረገ ሰው ነው፡፡

ያን ግዜ አይደለም አሁን ለብዙ አመት በኂላ እንኳን ኢትዮጵያን የሚያክል አገር ለማስተዳደር የሚችል አእምሮ፣ ተመክሮ፣ እንዲሁም ምንአልባት አስተዳደጉም ጭምር የነፈገው ሰብእና እንዳልነበረው ግልጽ ነው፡፡ እስካሁን የሰራውን ስህተት አንድ ቀን እንኳን በጸጸት ገልጾ አያውቅም፡፡ በቅርቡ ዶ/ር ዐቢይ “የኢትዮጵያን ህዝን ዝቅ ብዬ ይቅርታ እጠይቃለሁ” ሲሉ በመካከላቸው ያለው ትልቅ ልዩነት ጎልቶ ታየኝ፡፡ መግደል፣ ማሰር፣ ማሰቃየት ቀላል ነው፡፡ የጥሩ መሪ ባህሪ ግን አይደለም፡፡ ችግሮችን በህግ መፍታት፣ የዜጎችን መብት መጠበቅ፣ ለስልጣን ሳይሆን ለሀገር እና ለህዝብ አስቦ መወሰን ጥሩ አእምሮና ህሊና ይጠይቃል፡፡ መንግስቱ ትምህርቱም፣ እውቀቱም፣ ተመክሮ፣ ሰብእና፣ ስነምግባር፣ ራእይ፣ አስተዳደግ ወዘተ እንዳልነበረው ጭካኔዎቹ ይመሰክራሉ፡፡ አንድ አገር ተረክቦ

▶ለሁለት ክፍሎ፣ ህዝቡን አራቁቶ፣ እንደጠላት እንዲተያይ አድርጎ፣ ብዙዎችን አፈናቅሎ፣ ለስደት ዳርጎ፣ ብዙ ጀግኖችን ገድሎ እስከ" አንድ ሰውና አንድ ጥይት" የሚል የሞኝ መፈክር ሲያሰማ ከርሞ በመጨረሻ ቤተሰቡን አሸሸ፣ እሱም ፈረጠጠ።

በቅርቡ የታተመው የጄኔራል መርዕድ ንጉሴ መጽሐፍ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው ይህንኑ ሃቅ ነው። መጽሐፉ በልጆቻቸው ቢጻፍም በውስጡ የያዘው ሃሳብ በጄኔራል መርዕድ የዕለት ማስታወሻ ላይ የተመሠረተ ነው።

ጄኔራል መርዕድን እንደ አጎት ነበር የማየው፤ በጣምም ያቀርበኝ ነበር። ስለ አገሩ በጣም የሚጨነቅ ሰው እንደነበር አስታውሳለሁ። በአንድ ወቅት ከአባቴ ጋር ሐረር አንድ ቤት ውስጥ ለጥቂት ወራት ሲኖሩ እኔም ለክረምት ዕረፍት ሄጄ ብዙ ጊዜ አብረን አሳልፈናል። ነገር ግን መጽሐፉን ሳነብ በጣም ተደነቅሁ። የነበረውን አርቆ አስተዋይነት አሁን ባለሁበት የእውቀት ደረጃ መለስ ብዬ ሳየው በዚያን ዘመን በዛ ውጥረት ይህን አይነት አርቆ አስተዋይ አዕምሮ በመኖሩ ተገረምኩ። ብዙ በቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር አባላት የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቤያለሁ የዚህን አይነት የበሰለ የጦር ፣ ማሕበረ ሰብ፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የዲፕሎማሲ ዕሳቤዎች የያዘ ጽሑፍ አላየሁም።


አንብቤ ስጨርስ የተሰማኝ ስሜት "ትላልቆቹ አልቀዋል" የሚል ነበር። አገራችን በዚህ አልታደለችም። የጀግኖቹን ታሪክ የሚጽፉት ጀግኖቹ ሳይሆኑ የተረፉት ናቸው፤ ግማሾቹም የጀግኖቹ ገዳዮች።

ወደ ኋላ ልመለስ።

መፈንቅለ መንግስቱን የሞከሩት የጦር መሪዎችና ተከታዮቻቸውን ሳስብ አገራችን ምን ያህል እንደተቀየረች አስተዋልኩ ። ይህን ያልኩት ምክንያት እነዚያን ሰዎች ያገናኛቸው ብሔር ወይም ሃይማኖት ወይም የፖለቲካ አመለካከት ሳይሆን ለአገራቸው የነበራቸው ፍቅር በመሆኑ ነው። ከዛም አልፎ ምንም እንኳን በአገሪቱ ከፍተኛ አመራር ላይ ቢሆኑም አገራቸው በአንድ ሰው አምባገነን አመራር ስር እየማቀቀች በጦርነት ተወጥራ መኖርና መቀጠል እንደሌለባት ስለወሰኑ ነበር። ኦሮሞ ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ትግሬ ፣ ኤርትራ እንዲሁም ከሌሎች ብሔሮች የተውጣጡ ቢሆንም ያን እንደ ምክንያት፣ እንደ መሰብሰቢያ፣ እንደ ጥሩ ወይም እንደ መጥፎ ማሰብ ወይም ማንሳት ቀርቶ ከቁጥር ሳይከቱ ነገር ግን አንዱ የአንዱን ብሔር በማክበር ነበር የሚሰሩት። የብሔር ጭቆና አለ የለም የሚለው ጥያቄ ወደ ጦር ሠራዊቱ ውስጥ ስንገባ መልሱ የተለዩ ነበር። ከአባቴ ጋር ከከረን አልፌ ማሳህሊት ተራራ ላይ ሆነን ከጄኔራል በሃይሉ ክንዴ (ያኔ ኮሎኔል) በጦር ሜዳ ሬድዮ ጠርቶ በኦሮሚኛ ወታደራዊ ትዕዛዝ ሲሰጥ አይቻለሁ።

ከሁሉ በላይ የሚያቀርበውና በስራው የሚመካበት ረዳት መኮንን ኮ/ል ተስፋ የትግራይ ተወላጅ የሐረር አካዳሚ ምሩቅ ነበር። የደቡብ ዕዝ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ነበር። ከብዙ አመት በኋላ አባቴ ወደ ኤርትራ ሲመደብ ካለበት አስፈልጎ ኮ/ል ተስፋን ወደ ኤርትራ አዛወረው። ኮ/ል ተስፋ ከኤርትራ ተነስቶ አዲስ አበባ ዙሪያ ወረቀት አስበትኗል፡

በ3/7/70 0800 ሰአት ከዶሎ 17 ኪ/ሜትር ላይ ዋናው ጦር እንዲቆም ተደርጎ በአንዴ ሻምበሌ ጦር (ወደ 400 የሰው ሃይሌ) ወደ ድል ተነቃንቄ ድል ከተማ ስንደርስ የሶማሌ ወታደር ከቀድሞው የጦር ሰፈራችን በመኪና ለማምለጥ ሲበር ተከታትለን ከነመኪናው ማረከን ሌ.ሎችም 5 ወታደሮች ተታኩሰው ወደ ጫካ ስለገቡ መደምሰስ አልተቻለም።




፡በመፈንቅለ መንግሥቱ ጊዜ። መፈንቅለ መንግስቱ ሲከሽፍ በአስመራ አየር ሃይል ግቢ እንደተገደለ ሰምቻለሁ። አስመራ ከተገደሉት ጄኔራሎች መሃል ያኔ የኤርትራ ክፍለ ሀገር የነበረችው ተወላጅ የሆኑት ጄኔራል አፈወርቅም ወልደ ሚካኤል ይገኙበታል፡ ፡ ሁሉንም ያገናኛቸውና ለአንድ አላማ ያሰለፋቸው ኢትዮጵያዊነታቸውና ለአገራቸው የነበራቸው ፍቅር ነው።

በመጨረሻም ልጠቅሰው የምፈልገው በጄኔራል መርዕድ ንጉሴ አዲስ መጽሐፍ እንደተጠቀሰው የመፈንቅለ መንግስቱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ የጦር ክፍል የተውጣጡ እንደነበሩ ነው። ከከብር ዘበኛ ሁለት (አባቴና ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ) ከጦር ሠራዊት በጣም ብዙ (ጄኔራል ኃይሉ ገብረ ሚካኤል፣ ጄኔራል አበራ አበበ፣ ጄኔራል ቁምላቸው፣ ጀ/ል አለማየሁ ደስታ፣ ጀ/ል ነጋሽ ወልደየስ፣ ጀ/ል ወርቁ ቸርነት፣ የሃረር ጦር አካዳሚ ምሩቆች የነበሩት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው። ከሳንድረስት የእንግሊዝ የጦር አካዳሚ 1ኛ ወጥቶ ከእንግሊዝ ንግስት ከፍተኛውን ሽልማት የተቀበለለው ጀ/ል ተስፋዬ ትርፌ፣ ጀ/ል ደሳለኝ አበበ፣ ጀ/ል እርቅይሁን ባይሳ፣ ጀ/ል ታደሰ ተሰማ፣ ኮ/ል አርጋው ባንቲይርጉን ጨምሮ) በተጫማሪም ከአየር ኃይል (ጀ/ል ፋንታ በላይ፣ ጀ/ል አመሃ ደስታ፡ ጀ/ል ሰለሞን ደሳለኝ)፣ ከባሕር ኃይል (አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ) እንዲሁም ከፖሊስ (ጀ/ል ወርቁ ዘውዴ፣ ጀ/ል እንግዳ ወልደአምልክ) ሁሉ ተሳትፈውበታል።

የኢትዮጵያን ያንን ግዙፍና ስመጥሩ ጦር መሳቂያና ማፈሪያ ያደረገው መንግስቱ ኃይለ ማርያም ነው። እንደ ምስዕ ሆነው የተሸከሙትን የጦር አለቆች አስገድሎና ገሎ፤ የቀሩትንም አስሮ ጦሩን ባዶ ካደረገ በኋላ እንደ ክብሪት ሲያጠፋው የኖረውን የሌላውን ሕይወት የሱ ህይወት አደጋ ላይ ሲሆን ግን ህይወቱ አንገቱቶ በፍርሃት አገሩን ለቆ ጠፋ።

"ካለ መንግስቱ ኃይለማርያም አመራር ወደፊት መሄድ አትችልም" እየተባለ ሲነገረው የቀየው ጦር መንግስቱ ሄደ ሲሉት ለመንግስቱ ሲዋጋ እንደኖረ ሁሉ መሳሪያውን ቢችል እየሸጠ፣ ካልሆነም እየጣለ ወደ የቦታው ተበተነ።

ቀድሞውንም ኢትዮጵያን የምታክል በአፍሪካና በአለም ከፍተኛ ቦታ የነበራትን አገር ለመምራት ብቁ አዕምሮም፣ ተመክሮዎችም፣ አስተውሎም፣ ብቃቱም እንዳልነበረው ግልጽ ነው። አሁን ወደኋላ ዘወር ብለን ስናስብ መንግሥቱ በዚህ ሁኔታ ያን የሚያክል አገርና ሕዝብ እመራለሁ ብሎ ሲነሳ ማሰቡ ራሱ የሚገርም ነው።

ጭካኔውን መለስ ብዮ ሳየው ምን ያክል ስብእና የሌለው ሰው መሆኑ ይገርመኛል። አባቴ 38 አመት አገሩን አግልግሎ ሲያልፍ አስክሬኑን እንኳን ለቤተሰቡ ተልኮ የቀብር ስነስርአት እንዲደረግ አልፈቀደም። ወይም አላሰበውም። ከሁለት አመት በኋላ አገር ለቆ ሲሄድ እናቴ ኮሚቴ አቋቁማ የኢህአዴግን መንግስት አስፈቅዳ፣ አስመራ ድረስ በመሄድ በኤርትራ መንግስትና የአካባቢው ህዝብ ባደረጉት ከፍተኛ ትብብር፣ ፈቃድ አግኝታ ፣ ከጉዋደኞቹ ጋር በአንድ ላይ የተቀበሩበትን ቦታ በአገሬው ህዝብ ተመርታ፣ አስከሬናቸውን ቆማ አስቆፍራ፣ አስወጥታ፣ ለአካባባዊው ህዝብ ፍየልና እና በግ አሳርዳ ጋብዛ፣ በአካባቢዊው በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን አስቀድሳ፣ ተዝካር አብልታ፣ የጀግኖቹን አስክሬን ይዛ ተመልሳለች። በአገራችን ታሪክ የባለቤቷን አስከሬን ከወደቀበት አምጥታ በክብር ያስቀበረች የማውቀውን እናቴን ወ/ሮ አስቴር አዳሙን ብቻ ነው።

በቅርቡ ከአንድ የቀድሞ ጄኔራል ጋር በስልክ ሳወራ" ለሃያ ሰባት አመት የቀድሞ ሠራዊት አባላትና ቤተሰቦቻቸው አንገታቸውን እንዲደፋ ተደርጓል"" አሉኝ። አባባላቸው ቢገባኝም የእኔን ስሜት ግን እንደማይገልጸው ነገርኳቸው፡ ፡ አባቴ ዕጁን ሰጥቶ ተማርኮ በእስር ቤት እዚህ ሂድ፣ እዛ ቁጭ በል ፣ ና ! ተመለስ ! ሲባል ባይ ኖሮ እርግጥ አንገቴን ደፍቼ እኖር ነበር። አባቴ በሞትና በሕይወት ውስጥ ይኖር እንደነበር አብሬው ጦር ሜዳ ድረስ ሄጄ ያየሁት ስለነበር የሞትን ሐቅነት ከተቀበልኩ ቆይቼ ነበር። እንደ አንድ የጦር መሪ ለቆመለት አላማ ሲታገል ሕይወቱ አልፏል። እንደ አንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አገሩን አገልግሎ ለአገሩ ሲል የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአምባገነን አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በመረጠው መንገድ ተሰውቷል። የኢትዮጵያ ጦር የኢትዮጵያ እንጂ የደርግ እንዳልነበረ ከደርግ በፊት ያበረከተው 23 ዓመታት የውትድርና ዘመን ብቻ ሳይሆን በደቡብ በምስራቅና በሰሜን የከፈለው መስዋዕትነት፣ በመጨረሻም ለአገሩ ያፈሰሰው ደም ይመሰክራል። እኔ ብቻ ሳልሆን የ 12 እና የ15 አመት ልጆቹ ስለአያታቸው በኩራት አንገታቸውን ቀና አድርገው ነው የሚያወሩት።



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

# በጠ/ሚ/ር ዐቢይ ዘመን የተጀመረው የወንዝ ዳር ልማት ባለሥልጣን ቢቋቋምለትስ?

በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ የሥልጣን ዘመን ለተከናወኑ ተግባራት በግሌ አድናቂ ባልሆንም፤ አሁን ሊተገበር የታቀደውን የወንዝ ዳር ልማት ግን ሁላችንም ልንደግፈው የሚገባ ተግባር ነው፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ባለሐብቶች የቻሉትን ሁሉ አድርገው፣ የመንገድ ዳር ልማት ላይ ይሳተፋሉ እንጂ የወንዝ ዳር ልማት አሳስቧቸው አያውቅም፤ በመሆኑም ይህ ተግባር በመንግስት መተግበሩ በዕጅጉ ተገቢ ነው፡፡

አዲስ አበባ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ከመሆንዋ በተጨማሪ የመልክዓምድር አቀማመጡ ዘቅዛቃ በመሆኑ፣ ከከተማው ሕንፃዎችና መኖሪያ ቤቶች የሚለቀቀው ፈሳሽ ቆሻሻ ወንዝ ውስጥ በመግባት በግራቪቲ ሀይል ብቻ ከከተማው ስለሚወጣ ነው እንጂ፤ ውሃው ሜዳማ ቦታ ላይ ረግቶ ቢቀመጥ ኖሮ ሁላችንም እዚህ ከተማ ውስጥ መኖር ባልቻልን ነበር፤ በተለይ ዝናብ ሲዘንብ ሁሉንም ቆሻሻ ጠራርጎት ስለሚሄድ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ሰጥተነው አናውቅም፡፡

በአለማችን እጅግ በርካታ ከተሞች ከወንዝ ዳርቻ የተመሰረቱ ሲሆን፣ ከተሞቹ ግን እንደ አዲስ አበባ ዘቅዛቃ ሳይሆኑ ሜዳማ በመሆናቸው ወንዙ ለጀልባዎች መጓጓዣነት ሁሉ የሚያገለግልበት ሁኔታ አለ፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ግን ይህን ማድረግ አይቻልም፤ ሆኖም ግን እንደተባለው ለከተማ ውበትነት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የታሰበው እቅድ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ከመሆኑ አኳያ ይህንን ሥራ በቋሚነት የሚከታተል ባለበጀት መሥሪያ ቤት መመሥረቱ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ መሥሪያ ቤት ግንባታውን ማካሄድ ብቻ ሳይሆን ጥገና፣ ፅዳት፣ አስተዳደርን ጨምሮ በባለቤትነት መሥራት መቻል አለበት የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ ወንዞች እጅግ በርካታ ከመሆናቸውም በላይ አንዳንዶቹ ለከተማ ውበት ጥቅም መሥጠት የሚችሉ ሲሆን፣ የተቀሩት ግን ሸለቋቸው ጠባብ በመሆኑ ተደፍነው ለሌላ ልማት መዋል የሚችሉበት ሁኔታ ያለ ይመስለኛል፡፡ ውሀ በስር እንዲሄድ ተደርጎ መድፈን ከተቻለ፣ ከተማዋ ለሌሎች በርካታ ተግባራት ሊውል የሚችል የመሬት ሀብት አገኘች ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ለመኪና ማቆሚያ፣ ለመጋዘን፣ ለስፖርት ማዘውተሪያ ወዘተ አገልግሎቶች መሥጠት የሚችል አዲስ መሬት ተፈጠረ ማለት ነው፡፡

ምናልባትም ይህንን አዲስ የተፈጠረ መሬት በመሸጥ ማዘጋጃ ቤት ተጨማሪ ገቢ ሊያገኝም ይችላል፡፡ እነዚህ የተዳፈኑ ወንዞች በስራቸው የተለያዩ የኤሌትሪክ የስልክ ወይም ቱቦዎችን ማስተላለፊያ ሆነው ማገልገልም ይችላሉ፡፡ አዲስ አበባ ካላት አንዱና ዋና ችግር በሌሎች የሰለጠኑ አገሮች እንደሚታየው (under ground city) የሌላት በመሆኑ በየጊዜው ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸው መንገዶች ሲቆፈሩ ይስተዋላል፡፡ የሚቆፈረውም የተለያዩ መሥመሮችን ለመዘርጋት ተብሎ ነው፣ የምድር ሥር ዋሻ ካለ ግን በማንኛውም ጊዜ ዋሻ ውስጥ በመግባት የተፈለገውን ገመድ መዘርጋት ወይም መጠገን ስለሚቻል፤ ከተማውን በየጊዜው መቆፈር ብዙም ላያስፈልግ ይችላል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን የሥራ ሂደቶች በኃላፊነት ተረክቦ የሚያስተዳድር መስሪያ ቤት መኖሩ በኔ እምነት ተገቢ ይመሥለኛል፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ከሚስተዋለው ነገር አንዱ ዋና መንገድ ዳር ያለ ቦታ ወይም መሬት እጅግ ውድ ሲሆን፣ ወንዝ ዳር በቅርብ ርቀት ያለ መሬት ወይም ቤት ደግሞ ዋጋው እጅግ የወረደ ሆኖ ነው የሚገመተው፡፡ ነገር ግን ይህ አሁን የታሰበው የወንዝ ዳር ልማት ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ሲሆን እስከ አሁን የባለሐብቶችን ቀልብ መሳብ ያልቻሉ ገዳላማና ወንዝ ዳር ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛ ተፈላጊነት ማግኘታቸው አይቀርም፡፡ ይህ ደግሞ ለከተማው የገቢ መጨመር የራሱ የሆነ በጎ ገፅታ አለው፡፡ በሌላ አነጋገር (value add) የሚያደርግ ነው የሚሆነው፡፡

አዲስ አበባ ከእንጦጦ ተራራ ሥር የተመሰረተች ከተማ እንደመሆንዋ፣ ከተራራው የሚነሱት ወንዞች በከፍተኛ ደለል የተሞሉ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት እንጦጦ ተራራ ላይ በአመዛኙ ያለው የዛፍ አይነት ባህር ዛፍ በመሆኑ ነው፡፡ ባህር ዛፍ ደግሞ ሥሮቹ ፀጉር ስለሌላቸው አፈርን አጥብቆ የመያዝ ተፈጥሮአዊ ባህርይ ያጣሉ፡፡ በተጨማሪ የባህር ዛፍ ቅጠል እጅግ አሲዳማ በመሆኑ ከዛፍ ስር ሣር ስለማይበቅል አፈሩ በቀላሉ ይሸራሸራል፡፡ (በተለይ ቅጠሉ መሬት ላይ ሲወድቅ)

ለዚህ መፍትሄው በጉለሌ አካባቢ እንደተካሄደው ባህር ዛፍን ከእንጦጦ ተራራ ላይ አስወግዶ፣ በአገር በቀል ዛፎች መተካት ሲሆን፣ ይህን ማድረግ ከተቻለ ከእንጦጦ ተነስተው የሚወርዱ ወንዞች ሁሉ ደለል አልባ ይሆናሉ፡፡ ሌላው የባህር ዛፍ ልዩ ባህሪይ ቶሎ ለማደግ ሲል እጅግ በርካታ የከርሰ ምድር ውሃ የሚጠቀም ከመሆኑም በላይ፣ የከርሰ ምድር ውሃ በከፍተኛ መጠን ለትነትም እንዲዳርግ የሚያደርግ የዛፍ ዓይነት ነው፡፡ በተጨማሪም ስሮቹ ውሃ ፍለጋ ረጅም ርቀት ስለሚሄዱ፣ መሬትን በመሰንጠቅ እንዲሸረሽር ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ባህር ዛፍ የሚመከረው ሜዳማ በሆነ መሬት ላይ ብቻ እንዲበቅል ማድረግ ነው፡፡

የአዲስ አበባ የወንዝ ዳር ልማትና ተጓዳኝ ሥራዎች በተመለከተ፤ እኔ በግሌ ያለኝ ምልከታ ይህን ይመስላል፡፡ በዕርግጠኝነት ሌሎችም ባለሙያዎች ያላቸውን ሐሳብ ቢሰነዝሩ ለፕሮጀክቱ መሳካት ይረዳል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የግድ መለመድ ያለበት ነገር ቢኖር አንድ ፕሮጀክት ሲታሰብ ዲዛይኑ አንድ ሆቴል ወይም አዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ ዜጎች እንዲያዩትና ሐሳብ እንዲሰጡበት የማድረግ ልምድ ብዙም ሲተገበር አይታይም፡፡ ይህንን ማድረግ ምናልባት ሙያተኞቹ የዘነጉት ነገር ካለ ለማስታወስ ከመርዳቱም በላይ፤ የልማት ተነሺዎች ዲዛይኑን ሲያዩ ከቦታው ለመነሳት የሚያሳዩትን ቅሬታ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሰዋል፤ ለተማሪዎችም መልካም እውቀት እንዲቀስሙ ይረዳል፡፡

አንድ ፕሮጀክት ሲታሰብ ጥቅሙ ያልገባቸው ዜጎች ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ዲዛይኑን በሚመለከቱበት ጊዜ ሃሳባቸውን ሊቀይሩ የሚችሉበት ዕድል ሊፈጠር ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህኛውም ሆነ በሌሎች ፕሮጀክቶች ይህ ባህል ቢለመድ መልካም ነው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም ይህ የወንዝ ዳር ልማት ለሸገር ወይም (ለሸጋ አገር) አንድ ትልቅ ተጨማሪ ውበት በመሆኑ ሐሳቡ እውን ሆኖ በቅርቡ እንደምናየው ተስፋ እናደርጋለን፡፡